# የወልቃይት ጠገዴ ትግል የሁሉም ኢትዮጵያዊያን ጉዳይ ነው ***
# "የውርደት በትር" ገጽታ

አክሎግ ቢራራ (ዶ/ ር)

"በመጨረሻ እኛ የምናስታውሰው የጠላቶቻችን ቃላቶች ሳይሆን ድምጻቸውን ያጠፉትን የወዳጆቻችን ቸልተኛነት ነው"
ዶር ማርቲን ሉዘር ኪንግ

መግቢያ
ኢትዮጵያን ለማፈራረስና ሕዝቧን ለእርስ በርስ እልቂት የአመቻቸው የህወሓት፤ ኢህአዴግ አምባገነናዊ ስርአት የፈጠረውን መሰረታዊ ችግር አሁንም ገዢው ፓርቲ አግባብ ባለው ሁኔታ አላየውም፤ ቢያየውም ችግሩን ንቆ ትቶታል። ይህ የጥፋት ክስተት እንዳለ ሆኖ "ተቃዋሚ ነን" የምንለው ግለሰቦችና ስብስቦች በአበይት ብሄራዊ ችግሮች ላይ ምን አይነት አቋም እንወስዳለን? ጥፋቶችን እያየን ለምን ዝም እንላለን? የሚሉት ጥያቄዎች መልስ እንዲሰጥባቸው እጠይቃለሁ።
የእኔ መከራከሪያ ነጥብ እንዲህ የሚል ነው። አማራው፤ ኦሮሞው፤ ጉራጌው፤ አፋሩ፤ አኟኩ፤ ሲዳማው፤ ትግራዩና ሌላው በደሙ መስዋእት ከፍሎ፤ በብሄር፤ በገቢ፤ በጾታ፤ በኃይማኖት ሳይታገድ የኢትዮጵያን ነጻነት፤ ዘላቂ ጥቅምና ሉዐላዊነት ጠብቆ ከትውልድ ወደ ትውልድ ለእኛና ለተከታታይ ትውልድ ያሸጋገረልንን አገር፤ የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ራሱን አሁንም የትግራይ ነጻ አውጭ ግንባር (ህወሓት) ብሎ የሚጠራው ጠባብ ብሄርተኛና ፍጹም ጎጠኛ ቡድን ታሪክ ያላትን ኢትዮጵያችን እንድትበታተንና ሕዝቧ በእርስ በርስ ጦርነት እልቂት እንዲካሄድበት የሚፈቅድ አይመስለኝም የሚል ነው።
የኢትዮጵያ ሕዝብ ለአገሩ፤ ለነጻነቱ፤ ለመብቱና ለህይወቱ የታገለው ነጻነቱና ሰብአዊ መብቱ ተከብሮለት በመላው ኢትዮጵያ ለመንቀሳቀስ፤ ለመስራት፤ ለመኖር፤ ኃብት ለማካበት፤ መሪዎቹን ለመምረጥና ለመመረጥ እንዲችል ነው የሚል እምነት አለኝ። በጎሳና በቋንቋ ልዩነቶች ላይ የተመሰረተው የፌደራል ስርዓትና አስተዳደር ይኼን በዜግነት መብቶች አማካይነት ሊሰራ የሚችል የአገር ስርዓት አወቃቀር፤ መንግሥትና አስተዳደር ዋጋ-ቢስ አድርጎታል። ገዢው ፓርቲ፤ በተለይ ህወሓት የዜግነት መብትን ይፈራል፤ የተቀበለውና ስራ ላይ ያዋለው በብሄሮች ልዩነቶች ላይ የተመሰረተ ስርዓትን ነው። ታዲያ ምን ጎደለው?

የተማረከ ስርዓት
ይህ ስርዓት የሚያገለግለው ህወሓትንና ታማኞቹን ብቻ ሆኗል። ወደ ኋላ ዞር ብለን ስንመራመር፤ የኢትዮጵያን ነጻነትና ክብር ስኬታማ ያደረገው አንድ ብሄር አይደለም። ኢትዮጵያ በአንድ ብሄር ተገዝታ አታውቅም። እንዳለመሆኑ መጠን አሁንም አገሪቱን ከጥፋትና ከውርደት የሚነከባከባት አንድ ብሄር አይሆንም። ኢትዮጵያ የሁሉም ብሄረሰቦችና ኃይማኖቶች አገር ናት። በብሄር ተቃርኖ ስልጣን የሚሸምተውና የሚነግደው ህወሓት፤ በብሄረሰቦች እኩለነት አመካኝቶ፤ ሕዝቡን ከፋፍሎ የአንድን አናሳ ብሄር የበላይነት ተቋማዊ አድርጓል።

ለምሳሌ፤ የጋምቤላን ለም መሬት ከነዋሪዎቹ ነጥቆ፤ ለፈረንጆችና ለተመረጡ የትግራይ ተወላጆች አስተላልፎ "እድገት" አካሂዳለሁ ይላል። ይህ እድገት ሳይሆን ውርደት መሆኑን ታዛቢዎች ገምግመውታል። ህወሓት ይህ "ውርደት ነው! አፈና ነው! ኢ-ሰብአዊ መርህ ነው! የባስ ድህነት ነው! ብሎ ትችት የሚያቀርበውን ሁሉ እያደነ ያስራል፤ ይገድላል፤ እንዲሰወር ያደርጋል። የእድገት ትርጉም የተለየ ካልሆነ በስተቀር፤ በኢትዮጵያ ሲካሄድ የቆየው እድገት ለሌቦች፤ ለሙሰኞች፤ በተለይ ለህወሓቶት አመች ሆኖ ቆይቷል። ባለሥልጣናት ችግሩን አይክዱም፤ "ኪራይ ሰብሳቢነት አገር ያጠፋል" ይላሉ። ሌብነት ለማለት ግን አይችሉም፤ አይፈልጉም። "ኪራይ ሰብሳቢነት" እንደ ተራ ነገር ሁሉን አቀፍ የሆነ አባባል ሆኖ ትርጉመ ቢስ ሆኗል። ልክ እንደ "ተሃድሶ" ማለት ነው። እያሰሩና እየሰረቁ "ተሃድሶ" ምን ትርጉም አለው። "ተሃድሶ" ማንን አደሰ' ማንን አደኸየ? ቁም ነገሩ ግን፤ አንበሳውን የእድገት ውጤት ማርኮ ራሱን ሃብታም ያደረገው ህወሓት ነው። አዲስ አበባን ተረክቦ ለትግራይ ተወላጆት፤ በኢትዮጵያ ታሪክ ታይቶ በማይታወቅ ደረጃ፤ የከተማ መሬትና ሌላ ግዙፍ ኃብት ለአባላቱና ለደጋፊዎቹ ያስተላለፈው ህወሓት ነው። በአዲስ አበባ ቦሌ "መቀሌ" ተብሎ የሚጠራው አካባቢ የዚህ የመሬት ነጠቃ፤ የሰፈራና የኢኮኖሚ የበላይነት ውጤት ነው። መሬቱ ከማንና እንዴት እንድተነጠቀ የሚያሳዩ ብዙ መጻጽፍት፤ ምርምሮችና መጻህፍት ስላሉሉ አንባቢ ሊከታተላቸው ይገባል። ችግሩ የመረጃ እጥረት አይደለም። በተለይ፤ አስተማማኝ መረጃ ያለው፤ የዱሮው የኢህአዴግ የመገናኛ ባለሥልጣን የነበረው አቶ ኤርምያስ ለገሰ ያሳተመው "የመለስ ልቃቂት" የተባለው መጽሃፍ የህወሓትን ሙሰኛነት፤ ሌብነት፤ ባለጌነት፤ ጠባብ ዘረኛነት፤ ግፍ፤ በደል፤ ኢ-ሰብአዊነት፤ ጸረ-ኢትዮጵያዊነት፤ ጸረ-ሕዝብነት፤ ጸረ-ፍትህነት ወዘተርፈ ጥልቀት፤ ስፋትና አደጋ ቁልጭ አድርጎ አቅርቦታል። ህወሓት ከሕግ ውጭ የሰበሰበውን ግዙፍ ሃብት አካብቶም፤ እኔ የበላይነቱን ይዤ ካልቆየሁና አሁንም ድርጅታዊ ምዝበራ ለማካሄድ ካልቻኩ አገሪቱ "ትፈራርሳለች" ይለናል። አዲሱ በብሄር ልዩነቶች ላይ የተመሰረተው የፌደራል ስርዓት የቆየውን የሕዝብ ትሥስር አጥፍቶና ልዩነቶችን አጠናክሮ፤ ለአንድ በብሄርህ ለተዋቀረ ድርጅት የበላይነት መሳሪያ ሆኖታል፤ "ለአዲስ የስልጣን ከበርቴዎች" ዋና መሰረት ሆኖ ቆይቷል። ለማጠናከር የምፈልገው ጉዳይ በፖሊሲና በድርጊት ሲታይ፤ ህወሓት የበላይነቱን እስካልያዘ ድረስ ኢትዮጵያ

ብትፈራርስና ሕዝቧ እርስ በርሱ ቢተላለቅ ደንታ እንደሌለው ማወቅ የዜግነት ግዴታችን ነው። ይህን መሰረታዊ አስተያየት ለማጠናከር እፈልጋለሁ።

የህወሓት ጽንሰ ሃሳብ መሰረት ህወሓት የተመሰረተውና ስኬታማ ለማድረግ የወሰነው፤ የትግራይን ሕዝብ ለማገልገል ክልሉን “ከኢትዮጵያ ነጻ ማውጣት” ነበር። ምን ተይዞ? በምን የተፈጥሮ ኃብት? የሚለውን ጥያቄ ብናነሳ መልሱ ግልጽ ይሆናል። ከሌሎች የብሄር ስብስቦች ጋር ተመካክሮ ኢህአዴግ የተባለውን ጥምረት የፈጠረበት ዋና ምክንያት ያላሰበውን ኢትዮጵያን በሙሉ ለመግዛት እንዲያመቸው፤ የኢኮኖሚ ጥቅሞችን ለመሰብሰብ እንዲያስችለው፤ መሬቶችን ነጥቆ ለማጠቃለልና የመጨረሻ ግቡን ስኬታማ ለማድረግና ለማመቻቸት እንዲያስችለው ነው። የትግራይ ክልል ገና ባይገነጠልም፤ ይህ ህወሓት ሲመሰረት የጸነሰው የመሬት ነጠቃና የመስፋፋት እቅድ ተሳክቶለታል።

በአገር ደረጃ ሲታይ፤ ዘጠና ዘጠኝ በመቶ የሚገመተው ህገ ወጥ “ኪራይ” የተሰበሰበው ከትግራይ ክልል ውጭ ነው። ለምሳሌ ከአዲስ አበባ፤ ከኦሮሞያ፤ ከደቡብ፤ ከአማራ። ለም መሬቶቹና ወንዞቹ የተነጠቁት የሌላው ሕዝብ የተፈጥሮ ኃብት ነው። የፖለቲካ የበላይነቱ ለህወሓትና ለደጋፊዎቹ የጠቀመው ለዚህ “ኪራይ ሰብሳቤነትና” የግልና የቡድን ኃብት አካባችነት ሆኗል። ግዙፍ ስልጣን! ግዙፍ ኃብት! አስገኝቷል። ሌሎቻችን ይህን የፖለቲካ ስልጣን የበላይነት ከኢኮኖሚና ከተፈጥሮ ኃብት የበላይነት ጋር ማያያዝ አለብን የሚል እምነት አለኝ። ምክንያቱም፤ በክልሎች የሚካሄደው ግፍ፤ በደልና ድርጅታዊ ምዝበራ በአገር አቀፍ ከሚካሄደው እምብዛም አይለይም። የሚዘረፍበትን ቦታ የሚወሰነው የሚሰጠው ጥቅም ነው።

አማራጩ ምንድን ነው?

ለነጻነት፤ ለፍትህ-ርትእ፤ ለእውነተኛ እኩልነት፤ ለሕግ የበላይነትና ለእውነተኛ ዲሞክራሲ የቆምን ገልሰቦችና ስብስቦች ያለን አማራጭ አንድ ብቻ ነው። የህወሓትን ጨካኝነት፤ ጠባብ ዘረኛነት፤ ጎጠኛነት፤ ከፋፋይነት፤ “ኪራይ ሰብሳቢነት”፤ መሬት ነጣቂነትና ተስፋፊነት ጉዳትና አደጋዎች አይተን፤ ተባብረን፤ ተማምነን፤ ኃይላችን ሰብስበን፤ ይህን ጨካኝ ቡድን ከስልጣን ማውረድ ነው። ይህን ካላደረግን ግን በታሪክ ተጠያቂዎች እኛው ነን። ህወሓት የሚሰራውን ያውቃል። የተካነበትን “ከፋፍለህ ግዛውን” ከመቸውም በበለጠ ደረጃ ይቀጥልበታል። ህወሓት ለተከታታይ ትውልድ ደህንነት ደንታ የለውም፤ ከራሱ ጥቅምና ስልጣን በላይ አያስብም። ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍ ጥላቻን፤ ግጭትን አያስብም። ይህ በትግራይ አካባቢ ብቻ የሚወሰን ሳይሆን በአገር አቀፍ ደረጃም ተስፋፍቷል፤ ጥልቀት ይዟል።

ለምሳሌ፤ የኦጋዴን ኢትዮጵያ ሕዝብ በድርቅ ረሃብ እየተሰቃየ፤ ህወሓት አሜሪካኖችን ለመማጸን ብቻ በወር $250,00 ወጭ ያደርጋል። በውጭ የሚኖሩ ዲሞክራት ኢትዮጵያዊያንን ይከሳል። ይህ ጨካኝ ቡድን ነው ለብሄረሰቦች ፍትህ እቆረቆራለሁ የሚለን!! እንደገና፤ ወደ ኋላ ዘወር ብለን ብናይ፤ ዘመናዊዋ ኢትዮጵያ ከመመስረቷ በፊት ተራው ሕዝብ ተመካክሮና ተባብሮ የምንኮራባትን ኢትዮጵያን በነጻነት ጠብቋታል። ከአጼ ቴዎድሮስ በኋላ ደግሞ፤ ከሁሉም ብሄሮችና ኃይማኖቶች የተወጣጣው ብሄራዊ የመከላከያ ኃይሏ የአለምን ሕዝብ ባስደነቀ ደረጃ ነጻነቷን አስከብሮላታል። በኮሪያና በኮንጎ የፈጸመው ጀብዱ ለሁላችንም ኩራት ነው። ኢትዮጵያ ካላት ትንሽ ገቢ ተጠቅማ በቅኝ ገዢዎች ይሰቃዩ የነበሩትን የአፍሪካ አገሮች ነጻነት ደግፋለች። የአፍሪካን አንድነት ድርጅት መስርታለች። ዛሬ ለዚህች ሃገር የቆሙላት እንዲገለሉ፤ ከቀያቸው እንዲባረሩ፤ እንዲሰደዱ፤ እንዲምበረከኩ እየተደረገ ነው። ታሪካችን ካልካድን በስተቀር አገር ወዳድ ኢትዮጵያዋያን ለዚህች ታሪክ ላላት አገር በደማቸው ያልከፈሉት መስዋእት የለም። የአድዋ ድል የኢትዮጵያ ሕዝብ የህብረት ትግል ውጤት ነው። ይህ የመተባበር ብሄራዊ እሴት እንደሚቀጥል ሙሉ እምነት አለኝ። ከተባበርንና ከተቻቻልን እምቅ ኃይላችን ከህወሓቶች በብዙ እጥፍ ይበልጣል። ችግሩ የህወሓት ጥንክርናና ኃይል አይደለም። የኢትዮጵያዊያን ተቃዋሚዎች መበታተን፤ መከፋፈል፤ መጠላለፍ ነው።

የብሄር ፌደራሊዝም ከፈጠራቸው ክስተቶች መካከል “ከፋፍለህ ግዛው” ዋናው መሳሪያ ነው። ስርአቱ የህወሓት የበላይነት መሳሪያ ሆኗል። ለምሳሌ፤ የፌደራል ምክር ቤት የሚባለው የህወሓት መሳሪያ ነው። የምርጫ ቦርድ፤ የፌደራል ፖሊስ፤ የደህንነትና የመከላከያ ተቋማት፤ መገናኛ፤ ብሄራዊ ባንክ፤ ጉምሩክና ሊሎች ቁልፍ ተቋሞች የህወሓት መሳሪያዎች ናቸው። ህወሓት የማይቆጣጠረው መስሪያ ቤትና ባለሥልጣን ፈልጌ ለማግኘት አልቻልኩም። በሃያ አንደኛው ምእተ አመት፤ እንደዚህ ያለ የአንድ ብሄር የበላይነት የአገዛዝ ሁኔታ፤ የትም አገር ፈልጌ ለማግኘት አልቻልኩም።

የችግሩ እምብርት (The Core Problem)

ችግሩን በአጭሩ ላስቀምጠው። በአገር ደረጃ ሲመረመርና ሲገመገም ግልጽ መሆን ያለበት አበይቱ ጉዳይ ህወሓት የፖለቲካና የኢኮኖሚ የበላይነቱን ይዞ እስከቆየ ድረስ የኢትዮጵያ ዘላቂነት አስተማማኝ አይሆንም። የድርቅ ረሃብ አይቀረፍም። ዘላቂንትና ፍትሃዊነት ያለው፤ በራሱ ሊተማመን የሚችል (Reslient) እድገት ሊኖር አይችልም። ምክንያቱም፤ የውጭ ድጋፍም ቢቀጥልም፤ አብዛኛው የእድገት ውጤት በህወሓቶች ይማረካል። ካፒታሉ ይባክናል። ኃብት ይሸሻል። አሁን ያለው የተዛባ የነፍስ ወከፍ ገቢና ሕዝብን መአከል ያላደረገና የተዛባ የክሎሎች ልማት ይባባሳል። በተመሳሳይ፤ አብዛኛው ሕዝብ የማይሳተፍበት የእድገት ውጤት (የተማረከው ኢኮኖሚ) ሲቀጥል፤ የባሰ ግጭትን፤ ድህነትን፤ ረሃብን፤ ስደትን ይፈጥራል። የተዛባ ገቢና የክልሎች እድገት አለመረጋጋትን ያባብሰዋል። ሁኔታው እየተባባሰ ሲሄድ የሕዝብን አመጽ ያጠናክረዋል የሚል ግምት አለኝ።
የኢትዮጵያ ሕዝብ በሁለት አቅጣጫ እየተቀጣ፤ ህይወቱና ኑሮው እየተናጋ ነው።

አንድ፤ የህወሓት የፖለቲካ የበላይነት መዘዞች

የፖለቲካ ስልጣኑን የማረከው ህወሓት ከራሱ ጥቅም ባሻገር ለአብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ ኑሮ መሻሻል ምንም ደንታ የለውም የምልበት ዋና ምክንያት የኢትዮጵያን ኢኮኖሚና የተፈጥሮ ኃብት ምርኮኛ በማድረጉ ነው። ህወሓትና ደጋፊወቹ የሚያካሂዱት አደገኛ "የእድገት" መርህ ድህነትን፤ በተለይ ረሃብን መቅረፍ አልቻለም፤ አይችልም። የሚያካሂዱት አይን ያወጣ በጠባብ ብሄርተኝነት የተበከለ ድርጅታዊ ምዝበራን ነው። የወላቃይት ጠገዴን "የማንነትና የመሬት ባለቤትነት" ጥያቄ ለማየት የሚቻለው ከዚህ ህወሓቶች ለትግራይ ሕዝብ ቃል ኪዳን ከገቡበት የመሬት ነጠቃና ተስፋፊነት አንጻር ብቻ ነው። ለህወሓቶች ነጠቃውና ክልል አንድን ማስፋፋቱ የእደገት መሰረት ሆኗል። የምግብ ዋስትና፤ የኢንዱስትሪ፤ በተለይ የእርሻ ግብዓቶች የሚያስፈልጋቸው ኢንዱስትሪዎች ስኬታማና ውጤታማ ሊሆኑ የሚችሉት በተነጠቁት ለም መሬቶች የበላይነትና በሚያመርቱት ውጤት ነው።

በተመሳሳይ መሬቱ ለተነጠቀው ነዋሪዎች የመሬት ነጠቃውና መስፋፋቱ የህልውና ጥያቄ ሆኗል። የመሬት ነጠቃና ተስፋፊነት የፖለቲካ ውሳኔ ነው። የፖለቲካ የበላይነት ለኪራይ ሰብሳቢነት አመች ሁኔታዎችን እንደሚፈጥር "ድርጅታዊ ምዝበራ" በሚለው መጽሃፌ በመረጃ አሳይቻለሁ። አቶ ኤርምያስ ለገሰ በመጽሃፉ፤ "የመለስ ልቃቂት" ያሳየው ተመሳሳይ ሁኔታዎችን ነው። ህወሓቶች የሚሉት ግዙፍ ኃብት ለመያዝ የቻሉት በራሳቸው ጥረት እንጅ በኪራይ ሰብሳቢነት አይደለም ነው። በጥረት፤ በውድድር፤ በግልጽነት፤ ያለ ምንም ጎሳዊ አድልዎ የተገኘ ኃብት ነው ለሚለው መከራከሪያ መረጃዎቹስ የት አሉ? ተብለው ቢጠይቁ መልስ ይኖራል የሚል ግምትና እምነት የለኝም። መረጃዎች በፋብሪካ የሚመረቱ ይመስላሉ።

ለምሳሌ፤ የፖለቲካ ስልጣን የያዙትና ስልጣኑ እንዲቀጥል ያደረጉት "ሕዝብ ስለመረጣቸውና ስለሚያፈቅራቸው" ነው ይሉናል። የእኔ መከራከሪያ ነጥብ ከዚህ የተለየ ነው። በፖለቲካው ሲታይ፤ ህወሓት የምርጫ ውድድሮችን አግቦ፤ ተቃዋሚዎችን አስሮ፤ የመገናኛ ብዙሃንን ነጻነት አፍኖ፤ የአስቾኳይ አዋጅ አውጆ ሕዝብ "መርጦኛል" ማለት ሕዝብን መናቅ ነው እላለሁ። ኢህአዴግ በሕዝብ የሚተማመን ከሆነ የሕዝብን ነጻነት ተቀብሎ፤ የፖለቲካ እስረኞችን በሙሉ ፈትቶ፤ የመገናኛ ብዙሃንን ነጻነት አክብሮ፤ የምርጫ ቦርድ፤ ፍርድ ቤቶች፤ የፌደራል ፖሊው፤ ደህንነት፤ መከላከያና ሌሎች ብሄራዊ ተቋሞች ከህወሓት መንጋጋ ነጻ እንዲሆኑና ብሄራዊ አገልግሎት እንዲሰጡ አድርጎ ነጻና ፍትሃዊ ምርጫ እንዲካሄድ ሊያደርግ ይችላል። ግን አያደርገውም። በሕዝብ እምነት የለውም። ሕዝብን አፍኖ "ሕዝብ መርጦኛል፤ ሕዝብ ያፈቅረኛል" የሚለው ብሂል ተቀባይነት እንደሌለው ሕዝቡ ወስኗል። ድምጹን አሰምቷል። ልጆቹን መስዋእት አድርጓል። ሕዝብ ገዢውን ፓርቲ ባይቃወም ኖሮ፤ የአስቾኳይ አዋጅ አያስፈልግም ነበር። ህወሓት የኢትዮጵያን ሕዝብ አያምንም!!!

ሁለት፤ የኢትዮጵያ ዘመናዊ ኢኮኖሚው ምርኮኛነት/በህወሓት መማረክ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚና የተፈጥሮ ኃብት በህወሓቶች ተማርኳል። "መቀሌ በአዲስ አበባ" የተመሰረተው የአዲስ አበባ ከተማ መሬቶች በህወሓት ስለተማረኩ ነው። ህወሓቶችና ደጋፊዎቹ ይህንንም ይክዳሉ። "ኃብት ያካበትነው በራሳችን ችሎታና ጥረት ነው" ይሉናል። ኦሮሞው፤ ጉራጌው፤ አማራው፤ አኗኩ፤ አፋሩ ወዘተ ችሎታ የለውም፤ ጥረት አያደርግም ለማለት ነው? ህወሓት ይህን የተሳሳተ "እኔ ምርጥ ብሄር ነኝ፤ የፈለግኹትን ለማድረግ እችላለሁ" የሚል እምነት የሚቀበል ከሆነ ኢትዮጵያዊ ነኝ የሚያስብለው ምንም ነገር የለም ማለት ነው።

እኔ እስከማውቀው ድረስ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ታታሪ ነው። ሆኖም፤ ለማምረትና ወደ ገበያ ለማቅረብ፤ ስርአቱ አመች መሆን አለበት። ላሰምርበት የምፈልገው ጉዳይ አንድ ነው። ሌብነት "ኪራይ ሰብሳቢነት" ተብሎ የሚጠራው ችሎታ አይጠይቅም። የሚጠይቀው የፖለቲካ የበላይነትን፤ የመሳሪያ ኃይልና የተቀነባበረ ፕሮፓጋንዳን ነው።

በሁሉም ነገር ትችት የሚሰጡት አቦይ ስብሃት ምን አይነት ሞያ እንዳላቸው አላውቅም። በፖለቲካውም፤ በኃይማኖቱም፤ በኤርትራም፤ በሙስናውም፤ በኢኮኖሚውም፤ በመሬት ነጠቃውም፤ በመስፋፋቱም የሚናገሩት ሁሉ በመረጃ የተደገፈ አለመሆኑን እኔም ሆንኩ ሌሎች ተችተውታል። በመሳሪያ የተደገፈ የፖለቲካ ስልጣን የበላይነት የፈለጉትን ለመናገር፤ የፈለጉትን ለመስደብ፤ የፈለጉትን ለማሰርና ለመክሰስ እንደሚያስችል እኒህ የእድሜና የቤተሰብ ኃብት ባለጸጋ አስመስክረዋል።

የሕግ የበላይነት አለመኖር አደጋዎች

ህወሓት በሕግ የበላይነት አያምንም። የሕግ የበላይነት በማይከበርባት ኢትዮጵያ ዘላቂና ፍትሃዊ እድገት ሊኖር አይችልም። ስለሆነም፤ የሕግ የበላይነት የማይከበርበት ስልጣን የተራ ሌብነት "የኪራይ ስብሳቢነትና" የሙስና ሁኔታ እንደሚፈጥር፤ በተለይ፤ የህወሓት አባቶች፤ በኢኮኖሚው የበላይነት ዙሪያ የሚናገሩት ሁሉ ያስደነግጣል፤ ያስፈራል፤ ያሳፍራል፤ ነውረኛ ያስብላል። ሳራ ሄይስ እንደዚህ ያለውን በፖለቲካ ስልጣን መባለግ የሚከሰት የፓርቲና የመንግሥት ባለሥልጣናት ምዝበራ Thieves of State በተባለው መጽሃፏ አቅርባዋለች። በኢትዮጵያ ሲካሄድ የቆየውን "ድርጅታዊ ምዝበራ" ይህች ተመራማሪ በመረጃ ካቀረበችው አይለይም። አቦይ ስብሃት መጽሃፉን ቢያነቡት ሊማሩ ይችላሉ፤ የእኔንም መጽሃፍ- "ድርጅታዊ ምዝበራን"- በኢትዮጵያ እንዲታተም ቢያመቻቹት የኢትዮጵያ ሕዝብ አንብቦ ፍርድ ሊሰጥበት ይችላል።

የሔይስንም ሆነ የእኔን መጽሃፍ ለማንበብ "ፈቃደኛ አይደለሁም" ካሉም ቢያንስ የትግራዩ ተወላጅ፤ አገር ወዳዱ ሠዓሊ አምሳሉ ገ/ኪዳን አርጋው የተናገረውን አግባብ እንዳለው ተረድተው እንዲያስቡበት እጠይቃለሁ። አንድም የትግራይ ተወላጅ ቢሆን፤ በኢትዮጵያዊነቱ አምኖ የመሬቱን ነጠቃና የትግራይን መስፋፋት መተቸቱ አስደናቂ ነው።

ለምሳሌ፤ እንዲህ ብሏል።

"የህወሓት የግታል ኃብት የሆነው ኤፈርት በሀገሪቱ ተወዳዳሪ በሌለው ካፒታል (አቅመ ንዋይ)" ተንቀሳቅሷል።" ምን ማለት ነው? አምሳሉ ገ/ኪዳንን ልጥቀስ። "ኤፈርት እንደ ፋብሪካዎች (መምረቶች) እና ኢንዱስትሪዎች (ምግንባቦች) ያሉ ቋሚ ንብረቶቹን መቀመጫቸውን ትግራይ ላይ ሲያደርግ ሌሎች ገቢ የሚያገኝባቸውን እንደ ባንክ (ቤተ ንዋይ) ፣ ኢንሹራንስ (ዋስትና) ፣

ትራንስፖርት (መጓጓዣ) ፣ የብዙኃን መገናኛ (ማስ ሚዲያ) ፣ ገቢና ወጪ (ኢንፖርት ኤክስፖርት) ንግድ፣ ግብርናና ማዕድን፣ ኮንስትራክሽን (ግንባታ) ወዘተረፈ እንቅስቃሴውን ደግሞ በመላ ሀገሪቱ አንሰራፍቶ ፍርፋሪውን ብቻ በመተው በሕገወጥ መንገድ በብቸኝነት ተቆጣጥሮ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል፡፡”

ህወሓት ይህን ግዙፍ ኃብት አገር አቀፍ በሆነ ደረጃ ለማከማቸት የቻለው በራሱ የማምረት፤ የመፍጠር ችሎታ አይደለም። አምሳሉ ገ/ኪዳን ቁልጭ አድርጎ እንዳስቀመጠው ህወሓት የኢትዮጵያን ዘመናዊ የኢኮኖሚ ክፍሎች ሁሉ ሙሉ በሙሉ ስለተቆጣጠራቸው ብቻ ነው። ሁሉንም ኢትዮጵያዊያን የሚያሳትፍ ተወዳዳሪ የግል ክፍል እንዳይኖር ህወሓቶችና ደጋፊዎቹ የሚቆጣጠሩት ሞኖፖሊ አፍኖታል። ውድድር የሌለበት ኢኮኖሚ ግልጽነት ሊኖረው አይችልም። ግልጽነት ከሌለ ነጻነትና ፍትህ የለም ማለት ነው።

የፖለቲካውና የኢኮኖሚው ክፍሎች በህወሓት መማረክ ምን ችግር ይኖረዋል? ብዙ ዘርፎች የያዙ ችግሮችን ፈጥሯል። ከእነዚህ መካከል የእርስ በርስ እልቂት የመከሰት ሁኔታው እየተባባሰ መሄዱ አንዱ ነው። ብንቀበልም፤ ብንክድም፤ ብዙ ፈተና ይጠብቀናል። ስርአቱን ቀረብ ብለን እንዳስስ! አንቀጽ ሰላሳ ዘጠኝ የሕገ-መንግሥቱ መሰረት የሆነበት ዋና ምክንያት አገር አቀፍ ሁኔታዎች አመች ካልሆኑ ህወሓት፤ ተመሳሳይና ተደጋጋፊ የብሄር ድርጅቶች ለመገንጠል ያላቸው ምኞትና እቅድ ስኬታማ እንዲሆን ታስቦ ነው። ኢትዮጵያን ለአንድ ብሄር ጥቅም ብቻ እንደ ላም ጥገት ለማለብ እስከተቻለ ድረስ ህወሓት ሰላምን፤ እርጋታን፤ ብሄራዊ አንድነትን ይፈልጋል። መብቶችን አፍኖ ለዘላለም ለመግዛት ካልተቻለ ግን ኢትዮጵያ ብትፈራርስ ደንታ የለውም። ለኢትዮጵያ ዘላቂነትና ለመላው ሕዝቧ ጥቅም የቆመ ፓርቲ ራሱን ህወሓት ብሎ አይሰይምም። አገሩ እንድትፈራርስ አይፈቅድም። ራሱን “ነጻ አውጭ ግንባር” ብሎ ከሰየመም፤ አገር አቀፍ በሆነ ደረጃ፤ ከ25 ዓመታት የፖለቲካ የበላይነትና የኢኮኖሚ ድርጅታዊ ምዝበራ በኋላ፤ ስሙን ለማስተካከልና እውነተኛ ኢትዮጵያዊ የመሆን እድል ነበረው። ግልጽ መሆን ያለበት፤ ህወሓት ስሙንም ሆነ የቆመበትን መርህ አልለወጠም። ይህ የህወሓት አቋም ይለወጣል ብሎ የሚያስብ ኢትዮጵያዊ ተሳስቷል እላለሁ። በኢትዮጵያ ዘላቂነትና በመላው ሕዝቧ ደህንነት ሙሉ እምነት ያለን ኢትዮጵያዊያን ያለን አማራጭ አንድ ብቻ ነው።

ይኸውም አማራጭ፤ ልዩነታችን ወገ ጎን ትተን አፋኙን ስርዓት ማስወገድና ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚያገለግል፤ ለሕዝብ ተገዢና ተጠያቂ የሆነ፤ በሕግ የበላይነት የተመሰረተ ዲሞክራሳዊ መንግሥት መመስረት ነው። ይህ ከሆነ የብሄርም ሆነ የኃይማኖት ልዩነቶች በውይይት ሊፈቱ ይችላሉ። ያለፉት 25 ዓመታት ታሪክ የሚያስተምረኝ፤ ህወሓቶችና ሌሎች ጠባብና ጎጠኛ ብሄርተኞች የኢትዮጵያን ሕዝብ ወደ ጎን ትተውና መብቱን አፍነው፤ የፖለቲካውን ስልጣን ማርከው እና የኢኮኖሚውን መዋቅር ሙሉ በሙሉ ተቆጣጥረው አገራችን እንድትፈራርስ አመች ሁኔታዎችን ፈጥረዋል። ህወሓት ችግር ፈጣሪ ሆኖ ለኢትዮጵያ ዘላቂነት፤ ለመላው ሕዝቧ ዲሞክራሳዊ ነጻነት በማሰብ፤ ጠባብ ብሄርተኝነት/ጎጠኝነት የሚያስከተለውን አደገኛ ሁኔታ በማመዛዝን አግባብ ያለው አማራጭ ሊያቀርብልን አይችልም። ያቀርብልናል ብለን የምናስብ ከሆነ የምናስበው ሁሉ ከምኞት በላይ አያልፍም የሚል የማያወላውል እምነት አለኝ። ለምን?

ህወሓት ለኢትዮጵያ ዘላቂነትና ለመላው ሕዝቧ አብሮና ተደጋግፎ ማደግ የሚያስብ ቢሆን ኖሮ የተከዜን ድንበር አቋርጦ፤ አዲስ ካርት ቀርጾ፤ ተከታታይ ታሪክን አልቀበልም ብሎ፤ የወሎን፤ የጎንደርን፤ የአፋርንና የጎጃምን ለም መሬቶችና ወንዞች ወደ ትግራይ ለማጠቃለል ባልሞከረም ነበር! ሌላው ቀርቶ ሌሎችም ተቃዋሚ ነን የሚሉ የትግራይ ስብስቦች በመሬት ነጠቃና በኢኮኖሚ የበላይነት ዙሪያ ከህወሓት የተለየ አቋም ያላቸውም። ነዋሪው ሕዝብ ሳይጠየቅና ሳይፈቅድ፤ የሚኖርበትንና ለህይወቱ የሚመካበትን መሬትና ሌላ የተፈጥሮ ኃብት ነጥቆ ኃብት ማካበት፤ ነዋሪዎችን አስወግዶ የትግራይ ተወላጆችን ማስፈር፤ ለትግራይ ሕዝብ የማይረሳ ጥላቻንና ቂምን ፈጥሯል። ይህ በህወሓት ግፍና በደል የተፈጠረ ጥላቻ ሊወገድ ይችል ነበር፤ አልተቻለም። ስላልተቻለ፤ ጎንደሬው፤ ወሎየው፤ ጎጃሜው፤ አፋሩና ሌላው ከቀዬ የተባረረ ሕዝብ ያለው ምርጫ መብቱንና ማንነቱን ለማስከበር፤ መሬቱን ለማስመለስ አብሮና ተባብሮ መታገል ይሆናል፡፡ ሕዝቡ በየአካባቢው ካልተደራጀና በጋራ ሊሰሩ የሚችሉትን ተግባሮች ተደጋግፎ ለመስራት ካልወሰነ የህወሓት አልሞ ተኳሾች ሰለባ ይሆናል። የአካባቢና የብሄራዊ ትግሎች መደጋገፍ ይኖርባቸዋል የሚል እምነት አለኝ።

ይሉኝታ ቢሱ ህወሓት የነጠቀውን መሬት በቀላሉ አይለቅም። ያገኘውኝ የፖለቲካ ስልጣን የበላይነት በቀላሉ አይለቅም። ሊለቅ የሚችለው በተቀነባበረ የሕዝብ አመጽና እምቢተኛነት ነው። በኢትዮጵያ ዘላቂነትና በህዝቦቿ አብሮ መኖር የሚያምኑ ተቃዋሚዎች ከህወሓት የተለየ አቋም ካላቸው አቋማቸውን ለኢትዮጵያ ሕዝብ የማቅረብ ግዴታ አለባቸው የምልበት ምክንያት የችግሩን አደገኛነት በማመዛዘን ነው። እኔ የምከራከርበት ምክንያት ከላይ ከጠቀስኩት ከአምሳሉ ዘገባ ጋርና ከዚህ በታች ከጠቀስኩት ከአብርሃም በየነ ግጥም ጋር የተቀራረበ ነው። እንዲህ ይላል አቶ አብርሃም።

“ዕዘኑ ለቀሪ”
ለጎንደሮች መከራ ለባለ ጊዜው ጮራ ያብርሆት ነገን ሲዘራ ጊዜ በይኖ ሁሉንም 10
ሲያበራና ሲያጨልም ኩራት ለሚሰማት ለባለጊዜዋ ለእልቂት ዘማሪዋ ሞቷን በቂም ቋጥራ
መቃብሯን ቆፍራ
ባለቀ ቀን ኗሪ ልጡ ለተራሰው በዕዳዋ ተጧሪ ለወራሿ ትውልድ እዘኑ ለቀሪ።”
ጥር 1998 ከአብርሃም በየነ
“ተከዜን አልፎ እስከ ደባርቅ የተዘረጋው የውርደት በትር”
የህወሓቶች የመሬት ነጠቃና በግልጽ የሚታየው የትግራይ መስፋፋት፤ መለጠጥ ከአሁኑ ትውልድ በበለጠ የሚጎዳው ተከታታይ ትውልድን ነው። ከላይ ደራሲው ጥራት ባለውና በሚቀሰቅስ መልኩ እንዳስቀመጠው፤ እኛ “ማዘንና” መተከዝም ያለብን “ለወራሹ/ለቀሪው” ትውልድ ነው። ይህን ተከታታይ ትውልድ ምን አውርሰነው አለፍን? ብለን ራሳችን እንጠይቅ!! ስመ ጥሩ

ጎንደሬዎች "የውርደት በትር" የሚል ስም ሰጥተውታል። ይሆናል ተብሎ ያልተገመተውና ያልተጠበቀው በመሳሪያ ኃይል ሆነ ማለት ነው።

ታሪክ የሚነግረንና የሚያስተምረን አንድ መሰረታዊ ሃቅ አለ። ትግሬዎች ወልቃይትን ለመጀመሪያ ጊዜ ያወቁት በ1800s ራስ ወልደ ሥላሴ ተከዜን ተሻግረው አካባቢውን በወረሩበት ዘመን ነው። እሳቸው አካባቢውን ወርረው ነዋሪው ሕዝብ፤ ማለትም፤ ጎንደሬው ተከላክሎ መሬቱን በኃይል እንዲነጥቁትና የትግራይ አካል እንዲያደርጉት አልፈቀደላቸውም። "የአገር ውስጥ ወራሪዎቹ" ወደመጡበት ወደ ትግራይ እንደተመለሱ ታሪክ ይናገራል። በዚያ የታሪክ ወቅት፤ ትግሬዎች በጎንደር ክፍል ነዋሪዎች አልነበሩም። ይህ ታሪክ የሚያመለክተው ህወሓት መስሎች የጎንደርን ለም መሬቶች ለመንጠቅ የነበራቸው ፍላጎት ከብዙ መቶ አመታት በፊት እንደጀመረ አይካድም ማለት ነው።

መለስ ዜናዊ የፌደራሉ የሽግግር መንግሥት ፕሬዝደንት በነበሩበት ወቅት የህወሓት የመሬት ነጠቃና የትግራይ ተስፋፊነት እቅድ ግልጽ ስለሆነና ህጋዊ እንዲሆን ስለታሰበ፤ ጎንደርን በኃላፊነት የመሩና ሌሎች ጎንደሬዎች በመተባበር ለፕሬዝደንቱ ጠንካራ የአቋም አቤቱታ ደብዳቤ ጽፈው ነበር። ይህ ጠንካራ የአቋም ደብዳቤ፤ ነጠቃና መስፋፋት ህገ-ወጥ መሆኑን ያሰመረበት ሲሆን፤ ከኋላ ሆኖ የጎተጎተው የጎንደር ሕዝብ ነው። ሕዝቡ ጉዳዩ የህልውና ጉዳይ መሆኑን ጠቁሞ ነበር። ብዙ የሰው ህይወት እንዳለፈም አስምሮበት ነበር። ለምሳሌ፤ በከፊልም ቢሆን የተሰበሰበው መረጃ እንዲህ የሚል ነው። ከ1980-1993 ባለው ጊዜ ውስጥ ብቻ በህወሓት የተጨፈጨፉት፤ ታስረው የሞቱት፤ የደረሱበት የማይታወቀው የስም ዝርዝር ያሳየው በጠቅላላ የ509 አባውራዎችን ስም ዝርዝር ነው። ከእነዚህ መካከል ሶስት ግለሰቦች ብቻ ታስረው ተፈተዋል። በዚህ ዓመት፤ በ01/28/17 በህወሓት ቤታቸውና ንብረታቸው የተቃጠለው፤ የተጨፈጨፉትና እንዲሰወሩ የተገደዱት ጎንደሬዎች ስም ዝርዝር በከፊል ለዋቢነት ቢገኝም፤ ቁጥሩ ከዚህ በላይ እንደሚሆን ይነገራል። አንድ የቤተሰብ አባውራ ሲገደል ወይንም እንዲሰወር ሲደረግ ወይንም ቤቱና ንብረቱ ሲቃጠል መላው ቤተሰቡ እንደ ተጎዳ መቁጠር አለብን። በአማካይ አንድ ቤተሰብ ስድስት አባላት ይኖሩታል ብለን ብንገምት ብዙ ሽህ ጎንደሬዎች ህይወታቸው አልፏል ማለት ነው። ይህን ዝርዝር በመጽሃፌ አባሪ አድርጌ አወጣዋለሁ።

በክቡር አቶ ዳኘው ወልደ ሥላሴና በአቶ ፍትህአየ አሰጉ ሕዳር 11 ቀን, 1984 ዓ. ም. የተጻፈ ደብዳቤ እልቂቱን ባይጠቅስም፤ የተከሰተውንና ወደፊት የሚከሰተውን ችግር አስምሮበታል። እንዲህ ይላል።
"ለአቶ መለስ ዜናዊ፤ የኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት ፕሬዝደንት፤ አዲስ አበባ፡-
...ለጎንደር ታሪክና ቅርስ ቀዳሚ ባለቤት የሆኑትን ለም ቦታዎች፤ ማለትም፤ ሰቲት ሁመራን፤ ወልቃይትን፤ ጠገዴንና ጠለምትን ከተፈጥሮና ከታሪክ አካላቸው ከጎንደር ለይቶ የተከዜን ድንበር በመጣስ የትግራይ አስተዳደር አካል በማድረግ ቦታዊዎቹን የትግራይ ልማት ማዳበሪያ፤ ሕዝቡን (ነዋሪውን፤ ጎንደሬውን ማለት ነው) 2ኛ ደረጃ የትግራይ ዜጋ ለማድረግ መታቀዱን ስለተረዳን በተቃጣብን የውርደት በትር እጅግ በጣም ተደናግጠናል፤ አዝነናል።" ይህን ውሳኔ በምንም አንቀበልም ካሉ በኋላ የዚህ የመሬት ነጠቃና የትግራይ መስፋፋት አደጋ ለተከታይ ትውልድ የሚተላለፍ መሆኑን አስጠንቅቀዋል።

ይህ ለተከታታይ ትውልድ መረጃ የሚሆን የአቤቱታ ሰነድ፤ ሌሎችንም ጥቃቶች አብሮ ጠቁሟል። "በተጨማሪም፤ ቴዎድሮስ የተወለደበትን ቋራን፤ አፅሙ ያረፈበትን ማህበረ ሥላሴን፤ ዮሃንስ የተሰዋበትን መተማን አስመልክቶ፤ ቆላውን አገር በሙሉ ዘሩንና ስሙን አካባቢው ሰምቶት ለማያውቀው "ቤኒሻንጉል" ለተባለ በዚያ አካባቢ ለማይኖር ጎሳ ለመስጠት መታቀዱን ካርታው (አዲሱ) አሳይቷል።" በነገራችን ላይ ይህን እንደ ምስጢር ተይዞ የነበረውን የታሪክ ግድፈት ካርታ ይፋ ያደረገው አፍሪካ ኮንፊደንሻል የተባለው መጽሄት ነው። የመጽሄቱ ዘገባ የጠቆመው አዲሶቹ የኢትዮጵያ ገዢዎች (See Africa Confidential, From Rebels to Rulers) የአማራውን ሕዝብ የኢኮኖሚ መሰረት ለመንጠቅ የወሰኑበት አንዱ ምክንያት ይህን ሕዝብ ለማደህየት፤ ከቀዬ ለማባረርና ለማዋረድ እንደሆነ ያመለክታል። አንድ ተቆርቋሪ ምሁር እንዲህ ሲል ገልጾልኛል። "This massive land annexation and incorporation into Tigray is essentially socioeconomic and political strangulation that is akin to ethnic cleansing and genocide." እነ አቶ ዳኘው ወልደ ሥላሴ ለመለስ የላኩት የአቤቱታ ሰነድ የነጠቃውን ስፋትና ጥልቀት በመረጃ አቅርበውታል። "ይህ እቅድ ከአሜድላ እስከ መተማ ባለው ቆላማ መሬት ላይ ከዝንተ ዓለም ጀምሮ ከብቱን እንደ ልቡ ከቦታ ቦታ እያዘዋወረ የሚያሰማራውን ደገኛ የቋራ፤ የአለፋ፤ የጣቁሳ፤ የተንከል፤ የጭልጋ፤ የጫቶና የአዳኝ አገር ሕዝብ፤ እስከ አሁን ጸንቶ የኖረበትን ሕጋዊ መብቱን መጣስ ነው።" ይህ ሁሉ ህገ-ወጥ ግፍ ከስራ ላይ ከዋለ ግን "እነዚህን የትግራይና የጎንደር ሕዝቦች ከአሁን ጀምረው ለፍጅት እንዲሰላለፉ መጋበዝ ነው ከሚባል በቀር ሌላ ምክንያትና ትሩጉም አይኖረውም።"

በአሁኑ ወቅት የሚታየው ስእል ህወሓት ከዋልድባ እስከ አብደራፊ የተዘረጋ የጎንደርን ሰፊ ለም መሬት መንጠቁና የበላይነትን መያዙ ነው። ይህ ሲሆን የነዋሪው ሕዝብ ህይወት ሙሉ በሙሉ አደጋ ውስጥ መግባቱ አያከራክርም። በተነጠቁት ለም መሬቶች ላይ የሚታየው የብሄር ስርጭት ለውጥ ማን የበላይነቱን እንደ ያዘ ያሳያል። በሰቲት ሁመራና በሌሎች በተነጠቁ አካባቢዎች ህወሓት ያሰፈረው የትግራይ ተወላጆች ቁጥር ስለበዛ፤ በአካባቢው ይኖሩ የነበሩ ጎንደሬዎች ቁጥር አሳሳቢ ደረጃ ላይ መድረሱን አካባቢውን የሚያውቁ ተመልካቾች ተችተውታል። አዲሶቹ የለም መሬት ባለቤቶችና ባለ ኃብቶች (The new Tigrean landlords) ምርት የሚሰበስቡት ከተነጠቀው መሬት ሲሆን፤ ብዙዎቹ የሚኖሩት በመቀሌ ነው። ይህ ሁኔታ የሚያስታውሰኝ፤ የደርግ የመሬት አዋጅ ከመታወጁ በፊት የነበረውን ሁኔታ ነው። የመሬት ባለቤቶችና ባለ ኃብቶች በአዲስ አበባ እየኖሩ የኃብታቸው ምንጭ የገጠሩ መሬትና ገባሪው የአካባቢ ነዋሪው ነበር። የጎንደሬው መሬት ስለተነጠቀና ሕዝቡ በኃይል እየተገደደና እየተገደለ ከአካባቢው ስለተወገደ፤ ቢወድም ኖሮ ገባርም የመሆን እድል የለውም። ፍጹም መሬት አልባ ሆኗል ማለት ነው። መሬት አልባ መሆን፤ ህይወት

አልባ መሆን ነው።

ህያው ምስክሮች ለምን ይካዳሉ?

የእነ አቶ ዳኘው ወልደ ሥላሴ የአቤቱታ ሰነድ ድምዳሜ አሁን ያለውን አደገኛ የአካባቢ ሁኔታዎች አስቀድሞ አስምሮበት ነበር። ሆኖም፤ የእነ መለስ ቅድመ ዝግጅት አብሮ መኖርን የሚያጠናክር ሳይሆን የተለመው ምስጢራዊ እቅድ የጎንደሬውንና የሌላውን ኢትዮጵያዊ ተፈጥሯዊና ታሪካዊ ለም ቦታዎች መንጠቅና ማጣቃለል ነበር። ከጥቂት አገር ወዳድና ሃቀኛ የትግራይ ተወላጆች በስተቀር፤ ህወሓትና የህወሓት ደጋፊዎች የተነጥቁት ለም ቦታዎች ከጥንት ጀምሮ "የትግራይ አካል ነበሩ" ይላሉ። ጥንትማ አክሱም የመንን ትገዛ ነበር፤ ኤርትራም የኢትዮጵያ አካል ነበረች ወዘተርፈ። የመሬት ነጠቃው ግን የባሰ ሰው ሰራሽ ታሪክ አለው። የተነጠቀው ለም መሬት የተደገፈው በሰው ሰራሽ መረጃና ታሪክ ነው። መረጃውን በማያሻማ ደረጃ ለማቅረብ የቻለ አንድም ባለሞያ ለማግኘት አልተቻለም። የሚቀርበው መረጃ የፖለቲካ ውሳኔ እንጅ ታሪክን፤ የተፈጥሮ ባለቤትነትንና የነዋሪውን ቀደምት ስርጭት የሚደግፍ ሆኖ አይታይም። እንግሊዞች የራሳቸውን ዘር በዝምባብዌ አስፍረው "ለሙ መሬት የእኛ ነው" ማለታቸውን እንስታውስ። ኃይል ያለው የአገሪቱን ነዋሪዎች አስወግዶ በምትካቸው ነጮችን ስላሰፈረበት የጥቁሮች መሬት የነጮች ሆነ ማለት ነው። ደቡብ አፍሪካም የሆነው ተመሳሳይ ነው። ሌሎችም ብዙ ማሳሌዎች ለመጥቀስ ይቻላል።

ስለ ጎንደሩ የመሬት ነጠቃ፤ አንዳንድ የተካሄዱ ቃለ መጠይቆችና ምልልሶች ተጻራሪ አመለካከቶችንና መረጃዎችን ያሳያሉ። ለምሳሌ በዚሁ ነጥብ ዙሪያ ዶ/ር ገላውዲዎስ አራያ በአሜሪካ ድምጽ ሬዲዮ ፕሮግራም ባለሞያዎች የጻፉትን መረጃ ሁሉ ወደ ጎን ትቶ "በአጼ ዮሃንስ ዘመነ መንግሥት ወልቃይት የትግራይ አካል ነበር" ብሎ ዋሽቷል። የተናገረው የፖለቲካ ውሳኔ እንጅ ወልቃይት-ጠገዴ፤ ሰቲት ሁመራና ሌሎች የተነጠቁ ለም ቦታዎች በኢትዮጵያ ረዢም ታሪክ የትግራይ አካል ሆነው አያውቁም። ሊታመን የሚችል ምስክር የትግራይና የጎንደር ድንበር ተከዜ መሆኑን በሞያውና በስራው የሚያውቅ ወይንም ሙሉ ምርምር አድርጎ የሚናገረውን በመረጃ ለመደገፍ የሚችል ተመራማሪ፤ ምሁር ወይንም ግለሰብ ነው። ለዚህ ከልዑል ራስ መንገሻ የበለጠ የአይን ምስክር ይኖራል ብየ አልገምትም። ምክንያቱም፤ አባታቸው፤ አያታቸውና እሳቸው ትግራይን በበላይነት ገዝተዋል፤ ከጎንደር የበላዮች ጋር ተወያይተዋል፤ ተዋውቀዋል። የጎንደሬውንና የትግራዩን ሕዝብ የቆየ ግንኙነት አበጥረው ያውቁታል። እሳቸው በህይወት ያሉ ግለሰብ ናቸው። የአይን ምስክር ናቸው። ልዑልነታቸው ከኢሳት ለቀረበላቸው የማያሻማ ጥያቄ የሰጡት የማያሻማ መልስ እንዲህ የሚል ነው። "በኔም በአባቴም በአያቴም ዘመን ወልቃይት የጎንደር እንጂ የትግራይ ሆኖ አያውቅም።" የተናገሩትን ልብ እንበለው፤ "በኔም፤ በአባቴም፤ በአያቴም ወልቃይት የጎንደር እንጅ የትግራይ ሆኖ አያውቅም።" እኒህ ግለሰብ ለህሊናቸው የተገዙ መሆናቸው ነው። እኒህ ግለሰብ በወንድማማች ሕዝቦች መካከል ፍጅት እንዳይመጣ እንጠንቀቅ ማለታቸው ነው። እኒህ ግለሰብ "ለአንድ አገር፤ ለአንድ ሕዝብ እናስብ ማለታቸው ነው። የተናገሩት ሊካድ አይችልም።

ህወሓቶችና ደጋፊዎች መጀመሪያ አቋም ይዘው፤ ከዚያ በኋላ ታሪክ ለመፍጠር ይሞክራሉ። ሌላ ተመሳሳይ ምሳሌ ላቅርብ። የኢትዮጵያንና የሱዳንን ድንበር በሚመለከት ሁል ጊዜ ክህደት የሚሰበው ህወሓት ተከታታይ የኢትዮጵያ መንግሥታት የተስማሙበትን የእንግሊዙን "የግዊንን መስመርና ችካል ነው" ለማጽደቅ የሞከርኩት ብሎ ነበር። በህይወት የሚገኙት የቀድሞው የኢትዮጵያ ፕሬዝደንት መንግሥቱ ኃይለ ማሪያም ተጠይቀው "ከሳቸው በፊት የነበሩት የኢትዮጵያ መንግሥታትና የሳቸው መንግሥት" የኢትዮጵያ ተወካዮች ያልተሳተፉበትን መስመርና ችካል አልተቀበልንም፤ እንድንቀበልም አልተገደድንም" ብለዋል። ይህን ሲሉ የህወሓትን ሴራ ባዶ ለማድረግ ጥረዋል ማለት ነው። የድንበር ኮሚቴውን አቋም ደግፈዋል ማለት ነው።

በመሬት ነጠቃውም ጉዳይ ላይ ቢጠየቁ ከዚህ የተለየ አቋም ይዘው የሚቀርቡ አይመስለኝም። ልዑልነታቸው የተናገሩትን ከተቀበልን፤ እኔ እቀበላለሁ፤ ችግሩ በውይይትና በድርድር ሊፈታ ይችላል። ሆኖም፤ ህወሓትና ደጋፊዎቹ ችግሩን ለመፍታት የሚቻለው መሬቱን የተቀማው ሕዝብ ሰጥ ለጥ ብሎ የህወሓትን ውሳኔ ሲቀበል ነው የሚል እምነት ስላላቸው ጉዳዩ በሰላም ይፈታል የሚል ግምት የለኝም።

አንድ ተመራማሪ ጎንደሬ እንዳለው "የሆነው ሁሉ ሆኖ ግን የወልቃይት ጎንደሬነት ወይም ትግሬነት በታሪክ ማስረጃ በፍርድ ቤት እሰጥ አገባ የሚወሰን ክርክር አይደለም። አሁን እንደ ተወሰነው (ህወሓት እንደ ወሰነው ማለቱ ነው) ወደፊትም የሚወሰነው በጉልበት ነው።" እንዳለውም የአካባቢው ሕዝብ ጉዳዩን "የህልውና ጉዳይ ነው" ብሎ ሕዝባዊ ትግሉን ጀምሮታል። ጎንደሬው ራሱን የሚያከብርና ሌላውንም የሚያከብር ሕዝብ ስለሆነ የራሱን ህልውና በሁለተኛ የዜግነት ደረጃ ይቀበላል የሚል ግምት የለኝም። ከላይ የጠቀስኩት ሰነድ ያጠናከረው መልእክትም ይኼንኑ ነው። ሠዓሊ አምሳሉ ገ/ኪዳን አርጋው ያሰመረበትና ያረጋገጠው ይኼን በታሪክ የተደገፈ ሃቅ ነው። እሱና ልዑሉ የሚሉት ተመሳሳይ ነው።

ሠዓሊ አምሳሉ ገ/ኪዳን አርጋው አረናን በሚመለለት በግልጽና በደፋርነት እንዳስቀመጠው፤ "አረና ትግራይ ከጎሳ ተኮርነት ወጥቶ ወይም ጎሳተኮርነቱን (ዘውገኝነቱን) ትቶ ተመሳሳይ የአንድነት አቋም ካላቸው ጋር በመሆን ሀገር አቀፍ የአንድነት ፓርቲ ለመመሥረት እንደሚንቀሳቀስ የተነገረው ሲሆን 2ኛውና ከላይ ከተናገሩት ነጥብ ጋር በቀጥታ የሚጣረሰው ነጥብ ደግሞ "ፓርቲው ወደፊት ተመርጦ ሥልጣን ቢይዝ የሕወሓት ባለሥልጣናት መጠቀሚያ የሆነውን የትእምትን (EFFORT) ሀብት በትክክል የትግራይ ሕዝብ ሀብት አደርጋለሁ!" ማለቱ ነው፡፡

በተጨማሪ ያሰመረበት አስኳል ጉዳይ የመሬት ነጠቃንና የትግራይን ክልል ተስፋፊነት በቀጥታ የሚመለከት ነው። እንዲህ ብሏል።

“እነሱ በተደጋጋሚ እንደተናገሩት ከወያኔ ተለይተው የተጀራጁበት ምክንያት “ሕወሓት በረሃ እያለ ለትግራይ ሕዝብ የገባውን ቃል ሊፈጽም አልቻለም! የትግራይ ሕዝብ በሕወሓት ተከዷል!” በሚል ቅሬታ በመነሣሣትና ያንን ቃል ተፈጻሚ ለማድረግ እንደሆነ ተናግረዋል፡፡ የፓርቲዎቻቸውን ሥያሜ ትግራይን ማዕከል እንዲያደርግ ያደረጉበትም ምክንያት ይሄው ነው፡፡ እነኝህ ቡድኖች “ሕወሓት ተፈጻሚ አላደረገውም!” ከሚሉት ቃል የተገቡ ጥቅሞች አንዱ “ትግራይን በጎንደር በኩል ሌላው ቢቀር እስከ ደባርቅ ድረስ፣ በወሎ በኩል እስከ አለውኃና ከነባ ድረስ ማስፋት የሚለው አንዱ ሲሆን ሌላው ደግሞ የተለየ የኢኮኖሚ (የጥሪት) ተጠቃሚነት ነው፡፡”

እኔም የምከራከርበት ነጥብ ይኼው ነው። ህወሓትና የህወሓትን መሰረታዊ ዓላማ የሚደግፉ “ተቃዋሚ” ነን የሚሉ ትግራይ ነክ ድርጅቶች በመሬት ነጠቃና በትግራይ መስፋፋት ጉዳይ ተመሳሳይ የሆነ አቋም አላቸው። ኢኮኖሚውን በሚመለከትም ኤፈርትና ሌሎች ሞኖፖሊዎች የያዙት አገር አቀፍ ኃብት ሳይሆን ያስቸገራቸው፤ እነዚህ ተቋሞች ለትግራይ ሕዝብ ጥቅም አልዋሉም የሚል ነው። ጥያቄው ቀላል ነው። ኃብቱ የተሰበሰበው ከኢትዮጵያ ሕዝብ ከሆነ፤ ነውም፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ያገባዋል ወይንስ አያገባውም? እኔ ያገባዋል የሚል ሙሉ እምነት አለኝ፤ እነዚህ ተቋሞች አያገባውም የሚል አቋም አላቸው። ወደ መሬት ነጠቃውና የትግራይ ክልል መስፋፋት ስንመለስ አሁንም አምሳሉ ገብረ-ኪዳን የተናገረው አግባብ አለው። “እነኝህ ፓርቲዎች (ቡድኖች) ወያኔ ከጎንደርና ወሎ ቆርሶ የወሰዳቸው ለምና ሰፋፊ መሬቶችና ከመጀመሪያው ጀምሮ ከኢትዮጵያ ሕዝብ እየተዘረፈ በሕገወጡ ኤፈርትና በሌላም አማካኝነት ትግራይ ላይ የሚፈሰው የግፍ የሀገሪቱ ሀብት እንዲሁም በመላ ሀገሪቱ ትግሬን ብቻ ተጠቃሚ ያደረገው የንግድ እንቅስቃሴና የሥራ ዕድል በጭራሽ በቂ አይደለም፡፡ በቂ ባለመሆኑም ከዚህ በላይ በሚፈልጉት መጠን ተጠቃሚ ለማድረግ በማሰብ እየታገሉ ይገኛሉ፡፡ በሌላ አገላለጽ ሰዎቹ የሚፈልጉት እያንዳንዳችንን በቁማችን ሥጋችንን ግጠው መብላት ነው የሚፈልጉት፡፡ የለየላቸው ጭራቆች ናቸው! ሰዎች አይደሉም፡፡ እየታገሉ ያሉት በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ከወያኔ እጅግ የከፋ ወያኔ ሆኖ ለመምጣት ነው፡፡ የወያኔን ኢሰብአዊ መራር ግፍ ምን ያህል መሸከም እንዳቃተንና በፍጹም እንዳልቻልን፣ በአፍጢማችን እንደደፋን አስቡና ከወያኔ የከፋን ሌላ ወያኔን አስቡ! መቋቋም እንችላለን? ታዲያ እነኝህ ሰዎች ናቸው?”

አስኳሉ የፖሊሲ ግድፈት

እኔም የምከራከረው የኢትዮጵያ ሕዝብ፤ በተለይ ወጣቱ ትውልድ ራሱን መስዋእት ያደረገው ወያኔን አስወግዶ በሌላ ወያኔ ለመተካት አይደለም የሚል ነው። ህወሓትን “እቃወማለሁ!” ሆኖም፤ የመሬት ነጠቃውና የትግራይ መስፋፋት “ለትግራይ ሕዝብ ወሳኝ አቋም ስለሆነ እደግፈዋለሁ” የሚል አቋም ከህወሓት አቋም የተለየ ሊሆን አይችልም። ልዩነቱ የስልጣን እንጅ የፖሊሲ አይደለም የምለው ለዚህ ነው። ዛሬ ህወሓት የቀመለትን ፖሊሲ ነገ ህወሓትን የሚተካው ፓርቲ ቆሞ ይከራከርበታል፤ ለማስከበር ይጥራል ማለት ነው። ሕዝብን ይጨፈጭፍበታል ማለት ነው።

መከራከሪያ ነጥቤን ለማጠናከር እፈልጋለሁ። መሬቱ ከተነጠቀው ከጎንደሬው፤ ከወሎየው፤ ከጎጃሜው፤ ከአፋሩ፤ ከአፏኩ፤ ከኦሮምውና ከሌላው ኢትዮጵያዊ ሕዝብ አንጻር ሲመረመር የህወሓት የመስፋፋትና የበላይነት ፖሊሲ ጸረ-ሕዝብ፤ ጸረ-ፍትህ-ርትእ፤ ጸረ-ዲሞክራሲና ጸረ-አብሮ መኖር ነው። ስለሆነም፤ ህገ-ወጥ ነው። ህገ-ወጥ ከሆነ “ተቃዋሚ ነኝ” የሚል ስብስብ ሊኖረው የሚገባው አቋም ከህወሓት አቋም የተለየ መሆን አለበት። ስብስቡን ከህወሓት የሚለየው ስልጣን ሳይሆን ፖሊሲ ነው። ከጠባብ ብሄርተኝነትና ከጎጠኝነት የሚለየውም ይኼው ኢትዮጵያዊ አቋም ይሆናል።

ከላይ የጠቀስኩት የትግራይ ብሄር አባል ኢትዮጵያዊ ትንተናና ድምዳሜ እንከን የለውም፤ የተናገረው ሃቁን ነው። እኔ ይህ አገር ወዳድ በተናገረው የምጨምረው የለም፤ አሉታዊ ወይንም አወንታዊ ትችት መሰጠት ያለባቸው ይህን የሚክዱት ናቸው። ቁም ነገሩ የመሬት ነጠቃና የትግራይ ክልል መስፋፋት ጽንሰ-ሃሳብ የተጸነሰው ህወሓት ስልጣን ከመያዙ በፊት ነው። ህወሓት ይኼን ቀደም ብሎ ያሰበበት እቅድ ስኬታማ ሲያደርግ የመጨረሻ አላማው ምንድን ነው? ብሎ መጠየቅ የእያንዳዳችን ሃላፊነት ነው፤ በተለይ የትግራይ ምሁራን፤ የሕዝብና የተቋማት። አብሮና ተባብሮ የሚኖር ሕዝብ አንዱ በሌላው ጀርባ ላይ ራሱን ጭኖ፤ የመሬት ነጠቃና ተስፋፊነት አካሂዶ የራሱን ሕይወት ብቻ ለማሻሻል አይሞክርም። እኔንና ሌሎችን አገር ወዳዶችና ዲሞክራቶች ከሚያስጨንቁት አስኳል ጉዳዮች መካከል ዋናው የህወሓት የመሬት ነጠቃና የትግራይ ክልል ተስፋፊነት ሆኗል።

ይህ የመሬት ነጠቃና ተስፋፊነት ዙሮ ዙሮ የተጠቃውን ሕዝብ መቀስቀሱ እንደማይቀር የወልቃይት-ጠገዴ ሕዝብ እንቅስቃሴ በግልጽ ያሳያል። ይህ እንቅስቃሴ ህወሓት ትግራይን ለይቶ ቢገነጥልም እንደማያቆም መገመት አስቸጋሪ አይሆንም። ምክንያቱም፤ ግፍ የደረሰበት ሕዝብ ጉረሮው እንዲታነቅ አይፈቅድም። የኦሮሞው ሕዝብ የአዲስ አበባን ማስተር ፕላን የተቃወመበት ዋና ምክንያት ተመሳሳይ ነው።

ህወሓቶች፤ ትግሬዎች የሰፈሩበት፤ የሚኖሩበት፤ ቤት የሰሩበት፤ ኢንቬስት ያደረጉበትት መሬት ሁሉ የትግራይ ክልል፤ የትግራይ ሕዝብ፤ የህወሓት ሆኗል ማለታቸው ነው። ለምሳሌ በብዙ ሽህ የሚገመተው ልዩ መብት ተሰጥቶት በጋምቤላ የመሬት ኃብት የተሰጠው የትግራይ ተወላጅ ሁሉ “የመሬቱ ባለቤት እኔ ነኝ፤ አኞኮች አይደሉም፤ ማንነቴ አይነካ፤ መንግሥት ከእኔ ጋር ይሁን” ለማለት ልዩ መብት ተለግሶታል ማለት ነው። በተመሳሳይ፤ ህወሓት የአዲስ አበባን (ማስተር ፕላን) ስኬታማ ለማድረግ ቢችል ኖሮ የኦሮሞን ሕዝብ አስወግዶ፤ አዲስ የትግራይ ባለ ኃብቶችን አስፍሮ መሬቱ የትግራይ ተወላጆች ነው ለማለት ይችል ነበር ማለት ነው። ጎንደሬው ከመንቀሳቀሱ በፊት ህወሓት የራስ ዳሸንን (ደጀንን) ተራራ የትግራይ ክልል አካል አድድርጎት ነበር።
እንደማስታውሰው ከሆነ፤ ህወሓት ያጸደቀው ካሪኩለምና ካርታ ቢፈጸም ኖሮ ጎንደር የሚባል ክፍለ ሃገር ይጠፋ ነበር። የችግሩ

ጥልቀትና ስፋት ይህን ይመስላል። አሁንም የጎንደር ህልውና አከራካሪ ሆኗል። ሌሎች ብዙ ተመሳሳይ ምሳሌዎች ለመስጠት ይቻላል።

የመሬት ነጠቃ፤ የህወሓት እብሪተኛነትና የስልጣን ስካር

በማንኛውም አገር የመንግሥት ተቀዳሚ ሃላፊነት የሕዝቡን ፍላጎት ማሟላት ነው። የምግብ ዋስትና የሌለው ሕዝብ የራሱን መንግሥት ይበላል የሚባለው ለዚህ ነው። ህወሓቶች ለትግራይ ሕዝብ "ቃል ኪዳን" ገብተናል የሚሉት ትክክል ነው። ይህን "ቃል ኪዳን" ከሳቡት መሸሸጊያ፤ መጠጊያ የላቸውም! ትግራይ የሚታወቀው በመሬቱ መበላት፤ የማምረት አቅሙ ዝቅተኛ መሆኑ፤ በድርቅ ረሃብ፤ በስደትና በተመሳሳይ የተፈጥሮ መሰናክሎች መበከሉ ጭምር ነው። ይህንም ችግር ኢትዮጵያ ልትወጣው ትችላለች፤ በሕዝብ መተባበርና አብሮ በመኖር። የህወሓት መርህ ይህን የመተባበር አስፈላጊነት ይጻረራል!!! ቡድኑ በስልጣን የበላይነት ስለሰከረ፤ ማንንም "አልፈራም" ይላል።

በድርቅና በሌላ ረሃብ ይሰቃዩ የነበሩ አገሮች፤ ለምሳሌ፤ ሕንድ፤ ቻይናና ሌሎች የእድገት ተቀዳሚነት የሰጡት የሕዝቡን መሰረታዊ ፍላጎት ለማሟላት መሆኑን ጥናቶች ያሳያሉ። ዛሬ እነዚህ አገሮች በድርቅ ምክንያት አይራቡም። መንግሥቶቻቸው ለሕዝብ ጥቅም የቆሙ ናቸው። አስደናቂ እድገት አሳይታለች በምትባለው ኢትዮጵያ ባለፈው አመት እስከ 20 ሚሊየን ሕዝብ በረሃብ ተሰቃይቷል፤ ከ 300,000 በላይ የሚገመቱ ህጻናት በረሃብ ምክንያት ለሞት ተዳርገዋል። ከእነዚህ መካከል ብዙ ሽህዎቹ የአማራ ህጻናት ናቸው። በአሁኑ ወቅት በኦጋዴን፤ በኦሮምያ፤ በደቡብና በሌሎች ክልሎች ከ5 ሚሊየን በላይ የሚገመት ሕዝብ በድርቅ ረሃብ ይሰቃያል፤ ብዙ ሽህ እንስሳዎች ወድመዋል። ህወሓት ቤት፤ ንብረትና ጎተራዎችን ሲያቃጥል በተከታታይ ዓመታት በጎንደር ረሃብ እንደሚከሰት ለመገመት አስቸጋሪ አይሆንም። በተጨማሪ፤ ድርቅ ቢከሰት ብዙ ሕዝብ እንደሚያልቅ እገምታለሁ።

የማይካደው ማህበረሰባዊ ሃቅ እንዲህ የሚል ነው። ባለፉት ሃያ አምስት አመታት ኢትዮጵያ የምግብ ጥገኛ ሆናለች። በድርቅ ምክንያት የሚሰቃየው ሕዝብ ቁጥር እያደገ ሄዷል። ትላንት አማራው፤ አፋሩ ወዘተ፤ ዛሬ የኦጋዴን ሶማሌው፤ ኦሮሞው ወዘተ። ይህ ሕዝብ የሚያልፍለት መቼ ይሆን? ብለን እንጠይቅ። ህወሓት የሚያሽከረክረው መንግሥት ለኦጋዴን ሶማሌው አልደረሰለትም፤ ትላንትም ለአፋሩ አልደረሰለትም። ነገም ለሚራበውም አይደርስለትም። ሆኖም፤ ለውጭ ጠበቃዎችና ሎቢስቶች በወር ብዙ መቶ ሽህ ዶላር ያፈሳል። ለረሃብተኞች ድጎማ ይለምናል!!! እድገቱን "እንቀቅልሽ" ነው የሚያስብለው ይኼው የምግብ ዋስትና አለመኖር ነው።

ይህ ሊወገድ የሚችል ረሃብ ካልቆመ በማህበራዊ ኑሮና በኢኮኖሚው ላይ የሚኖረው አሉታዊ ውጤት የሚዘገንን እንደሚሆን እገምታለሁ። የኑሮ ውድነቱ እየተባባሰ ይሄዳል፤ የምግብ ጥገኝነት ይባባሳል። ስደተኛው የሚልከው ገንዘብ የሚገዛው ነገር አይኖርም። ለማጠናከር የምፈልገው ነጥብ ሶስት መቶ ሽህ ህጻናት ቢሞቱ፤ የኦጋዴን ወንድሞቻችን፤ እህቶቻችን፤ እናቶቻችን ቢሞቱ ለህወሓቶች ትርጉም የለውም። ያላቸው ይበላሉ፤ ይጠጣሉ፤ ሕዝብ ይፈጃሉ፤ ያፍናሉ፤ እንዲሰወር ያደርጋሉ፤ ያስራሉ፤ ያሳድዳሉ፤ ወጣቱን ይገድላሉ፤ ይገዛሉ፤ ኃብት ያሸሻሉ። በአጭሩ ህወሓቶች በድህነት ኃብታም ሆነዋል። ልመና አያሳፍራቸውም!!!! ጠባብ ብሄርተኛውና ጎጠኛው ኢኮኖሚ ኢ-ፍትሃዊ ውጤት አስከትሏል። ይህ ምን ማለት ነው?

ህወሓት የተከተለው የእድገት መርህ ከሕዝብ ኑሮና ደህንነት ጋር ምንም ግንኙነት የለውም። የሌብነት ("የኪራይ ሰብሳቢነት"" ባህሪው ስለሚዳኘው፤ በኦሞ ሸለቆ፤ በጣና በለስ፤ በኦሮሚያና በሌሎች ቦታዎች ነዋሪውን ሕዝብ ከቀዬ አስወግዶ የስኳር ፋብሪካ እሰራለሁ ይላል። ብዙ ቢልየን ብር ሲጠፋ የሰረቁትን ወይንም ኃብት ያባከኑትን የህወሓት ባለሥልጣናት ማንም የሚጠይቃቸው ኃይል የለም። ከቀዬ የተወገደው ሕዝብ ይደኸያል፤ ይሰደዳል። የስኳሩ ፋብሪካ "ለኪራይ ሰብሳቢዎች" ትርፍ ያስገኛል። ይሰራል የተባለው ፋብሪካ ሳይሰራ ብዙ ቢሊየን ብር ካፒታል ይሰረቃል፤ ይባክናል። ማንም ባለሥልጣን በሃላፊነት አይጠየቅም ሲባል ለምን? ብሎ መጠየቅ ተገቢ ነው።

ምክንያቱም፤ ኢንቬስተሮቹም እንሱ፤ ኪራይ ሰብሳቢዎቹም እነሱ፤ ውሳኔ የሚያደርጉትም እንሱ፤ ፍርድ የሚሰጡት እነሱ፤ ፍርድ የሚያስፈጽሙት እነሱ ስለሆኑ ነው። በእድገት ስም የተጎዳውና የሚጎዳው ግን ተራው ገበሬና ቤተሰቡ ነው። ይህ የሚዘገንን ድርጅታዊ ምዝበራና ሙሰኛነት ከቀጠለ ድህነት ሊቀረፍ አይችልም፤ ስደቱ ይቀጥላል። ሰላምና እርጋታ አይኖርም። እንዲያውም ድህነት እየተባባሰ ይሄዳል። የአሜሪካን ስንዴ መለመኑ ይቀጥላል። ህወሓት በድህነት ሲነግድና ሲከብር ይኖራል!!! የሕግ የበላይነት አለመኖሩ ያስከተለውን አሉታዊ ውጤት በቀጥታ ቀን በቀን ሊያየው የሚችለው በኢትዮጵያ የሚኖረው 102 ሚሊየን ሕዝብ ነው፤ በአፍሪካ ሁለተኛውን፤ በዓለም አስራ ሶስተኛውን ደረጃ የያዘው።

በአገር ደረጃ ያለው ሁኔታ ይህን ሲመስል፤ የመሬት ነጠቃው የተባባሰ ሁኔታን የፈጠረው በጎንደር፤ በወሎ፤ በጎጃም፤ በአፋርና፤ በሌሎችም የአማራ ሕዝብ አካባቢዎች ነው። ይህን አሰቃቂ የድህነት ሁኔታ በመረጃ ያቀረበው አልጀዚራ "የአማራው ሕዝብ በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በአፍሪካ ደረጃ የመጨረሻ ድሃና ኋላ ቀር ነው" በሚል ዘግቦታል። ይህ ድምዳሜ ያሳየው ወያኔዎች ከጅምሩ "በጠላትነት" ያወገዙት፤ የአማራው ሕዝብ በራሱ የተፈጥሮ ኃብትም ለመጠቀም አለመቻሉን ነው። የአማራው ሕዝብ በፌደራል ሆነ በክልል ውሳኔዎች እንዳይሳተፍ ታግዷል። የአስተማሪዎችን የኑሮ ሁኔታ ብናይ የትግራይ አስተማሪዎች አበል ይሰጣቸዋል፤ አማራዎችና ኦሮሞዎች ለደሞዛቸው አቤቱታ ይጠየቃሉ። አማራውን እንወክላለን የሚሉት ስብስቦች ከጥቅማቸው ጉዳታቸው የሚያመዝን መሆኑ ግልጽ ነው። ይህ ሕዝብ ከድህነት ነጻ ለመውጣት የሚችለው ተቆርቋሪ የክልል አመራር ሲኖረው፤ የራሱን ለም መሬትና ወንዞች በባለቤትነት ለመያዝ ሲችል፤ የተነጠቁት ለም መሬቶች ሲመለሱለት ፤ የፌደራሉ መንግሥት ግብአቶችን ሲያቀርብለትና አቅሙን ሲገነባለት፤ በጣና በለስ ሆነ በሌላ ቦታ የመስኖ እርሻ ለማስፋፋት ሲችል፤ ጤናው ሲጠበቅ፤

ሰብአዊ መብቱ ሲከበር ወዘተርፈ ነው። ድሃው አማራ ብቻ ነው ማለቴ አይደለም። የአፋሮችን የኑሮ ሁኔታም ብንመረምረው ከዱሮው የባሰ ነው። ዱሮ የአፋር ለማኝ አይታሰብም ነበር፤ ዛሬ የማይታሰበው በገሃድ ይታያል። የአፋርም ሕዝብ በድህነቱ ይነገድበታል ማለት ነው። አገር ወዳዱንና ታታሪውን የአፋሩን ሕዝብ ለማኝ ያደረገው ህወሓት ነው።

## የዜሮ ድምር እድገት ውጤት

የፌደራል መንግሥት ድጋፍ ለክልሎች ልማት ወሳኝ ነው። ግብአትን በሚመለከት፤ ህወሓትና በአማራው ክልል የሚገኙ ደጋፊዎቹ ያደረጉት ከዚህ የተለየ ነው። ህወሓት ትኩረት የሰጠው የራሱን ክልል፤ ማለትም የትግራይን ሕዝብ የምግብ ዋስትና ማመቻቸት፤ የሕዝብን አቅም መገንባት፤ የመሰረተ ልማትና የዘመናዊ ኢንዱስትሪዎችን ማስፋፋት፤ ለወጣቱ ትውልድ የስራ እድል መፍጠር፤ ሌላው ቀርቶ የውጭ ንግድን ማስፋፋት፤ ከሱዳን ጋር ያለውን መገናኛ ማጠናከር፤ ለዚህ ሁሉ የአቅም ግንባታ የሚረዳ የፌደራል መንግሥት የባጀት ድጋፍ ማመቻቸት፤ የኢትዮጵያን ባንኮች ያለምንም መያዣና በዝቅተኛ ወለድ ብድር እንዲሰጡ መቀስቀስ ወዘተርፈ መሆኑ አይካድም። ይህ ኀጠኝነትን፤ ጠባብ ብሄርተኝነትን፤ ትእቢተኝነትን፤ እብሪተኝነትን እና ኀሳዊ አድልዎን የሚያንጸባረቅ የዜሮ ድምር የእድገት መርህ የተዛባ የነፍስ ወከፍ ገቢና የተዛባ የልማት ውጤትን ያሳያል!
እነዚህን አስመልክቶ አምስት ምሳሌዎችን ልስጥ።

አንድ፤ በ 2006-2009 በትግራይ ክልል የተደረገው የኢንቬስትመንት ፈሰስ 12.6 ቢሊየን ብር ሲሆን በዓማራው ክልል 2.8 ቢሊየን ብር ብቻ ነው። የትግራዩ ፈሰስ ከአራት እጅ በላይ መሆኑ ነው። የትግራዩ ኢንቬስትመንት ለ90,000 ተወላጆች የስራ እድል ፈጥሯል፤ የአማራው ለ76,000 ብቻ! በመሰረተ ልማት የተደረገው ፈሰስ ምንም ሊነጻጸር አይችልም።
ሁለት፤ የጤና አገልግሎትን በሚመለከት ከላይ በተጠቀሰው ጊዜ የህጻናትን ህይወት ሁኔታ ብንመረምር ያለው ልዩነት ሰፊ ነው። በትግራይ ክልል ከአምስት አመት እድሜ በታች የሚሞተው የህጻናት ቁጥር ከ1,000 ህጻናት 73 ሲሆን በአማራው ክልል ከ1,000 ህጻናት 94 ይሞታሉ። በህጻናት ህይወት ላይም ከፍተኛ አድልዎ አለ ማለት
ነው። በአማራው ክልል በተስቦ በሽታ፤ በወባ፤ ከቆሻሻ ውሃ በሚመጣ በሽታ፤ በምግብ እጥረት፤ በኤችአይቪ ኤድስ የሚሙተው ቁጥር በቅጡ ባይታወቅም ግዙፍ መሆኑ አይካድም።

## የወጣቱ አሰቃቂ ህይወት

በጎንደር፤ በደብረ ታቦር፤ በባህር ዳርና በሌሎች ከተማዎች ተዘዋውሮ ሁኔታውን የተመለከተ ግለሰብ ብዙ ወጣት ወንዶች እግራቸው ወይንም እጃቸው/ክንዳቸው ወይንም ጀርባቸው በጥይት እንደተፈረካከሰ አይቶ ይሄ ለምን ይሆን? ብሎ ሲመራመር የህወሓት አልሞ ተኳሾች ትኩረት የሚሰጡት ለወጣቱ ትውልድ መሆኑን መረጃ አገኘ። እነዚህ ጎንደሬዎች፤ ጎጃሜዎች፤ ወሎየዎችና ሌሎች አካለ ስንኩል እንዲሆኑ የተደረገበት ዋና ምክንያት ለህወሓት አደጋ እንዳይፈጥሩ፤ መሳሪያ ይዘው እንዳይከላከሉ፤ ለሕዝባቸው መከታ እንዳይሆኑ ለማባከን ነው። ወጣቱ ትውልድ በተፈጥሮ በሽታ፤ በረሃብ ብቻ ሳይሆን በስርዓቱ ጨካኝነት መስዋእት እየሆነ ነው። ተምሮ ስደት!! ኑሮም ውድመት!!
የአልጀዚራ ጥናት ያሳየው 500,000 አማራ እውር መሆኑን ነው፤ ይህ ሊወገድ የሚችል በሽታ መሆኑን ታዛቢዎችና ባለሞያዎች ተችተውታል። አለም ባንክ ስሰራ በነበረበት ወቅት አንዲት ስራ አስኪሃጅ የነገረችኝ ትዝ ይለኛል። "ለኤድስ የሚሰጠው እርዳታ ለምን ለአማራው ክልል አይደርስም?" ብላ ስትጠይቅ "የአስተዳደር ብቃት ስለሌለ ነው" ብሎ የነገራት ባለሥልጣን ወያኔ ነው። በሌላ አነጋገር የአማራው ሕዝብ በልዩ ልዩ በሽታዎች እንዲሞት ተፈርዶበት ነበር ማለት ነው። ጎንደሬ ባለሞያዎች የሉም ብሎ ምክንያት መስጠት እውነቱን ለመሸፈን ነው።

ሶስት፤ በUNESCO 2005 ዘገባ፤ የትምህርት እድል ከተስፋፋባቸው የኢትዮጵያ ክልሎች መካከል የመጀመሪያውን ደረጃ የያዙት አዲስ አበባና ትግራይ ናቸው። በዚህ ክልል የአንደኛ ደረጃ የትምህርት እድል ሽፋን 99 በመቶ ደርሷል። በአማራው ክልል 68 በመቶ ነው። በአማራው ክልል 33 በመቶ በላይ የሚገመቱት ህጻናት በምግብ እጥረት የተነሳ እድገታቸው ተበክሏል (the growth of these Amhara children is severely stunted). በተከታታይ ድርቅ የሚታወቀው የትግራይ ክልል የእርሻ ዘርፍ የተለየ ትኩረት ተሰጥቶት ግዙፍ የኢንቬስትመንት ፈሰስ ተለግሶታል። ከ2005-2009 የእርሻው ክፍል በዝቅተኛ በአመት 9.5 በመቶ በከፍተኛ በአመት 15 በመቶ አድጓል።

ይህ ውጤት እንዴት ተሳካ? ብለን ብንጠይቅ የፌደራሉ መንግሥት ፤ የውጭ ለጋሶችና የአገር ውስጥ ባንኮች በሚያደርጉት ግዙፍ ፈሰስ ነው የሚል መልስ እናገኛለን። ከዚህ ላይ አንድ
የማላልፈው ጉዳይ አለ። ይኼውም፤ የኢህአዴግ መንግሥት ግዙፍ የውጭ እርዳታ የሚሰጠው በኢትዮጱያ ሕዝብ ስም ነው። በትግራይ ክልል ስም አይደለም። አንበሳውን ክፍል የማረከው ግን ህወሓት ነው። ኢህአዴግ በኢትዮጵያ ሕዝብ ስም ግዙፍ እርዳታ ይለገሳል፤ የውጭ ብድር ይበደራል። እዳውን የሚሸከመው የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው። ጥቅሙን ማራኪ ህወሓት፤ እዳውን ወራሽ የኢትዮጵያ ሕዝብ!!!!
አራት፤ ቅደመ ህወሓት የትግራይ ክልል የሰሊጥ ምርት አምርቶ ለውጭ ገበያ አያቀርብም ነበር። በተጠቀሰው የዘገባ አመት ዙሪያ፤ "የትግራይ ክልል 1.3 ሚሊየን ቶን ሰሊጥ አምርቶ ከዚህ 90,000 ቶን ሰሊጥ ለውጭ ገበያ በሱዳን ወደብ ሸጧል፤ $121 ሚሊየን ገቢ አትርፏል። ጥናቶች የሚያሳዩት ቅድመ ህወሓት ሰሊጥ አምራቹ ጎንደሬው መሆኑን ነው። ይህ ክስተት፤ የመሬት ነጠቃ ጥቅም አለው የሚለውን ነጥብ ያጠናክራል። የእርሻው ክፍል ብቻ አይደለም ያደገው።

አምስት፤ የፌደራሉን መንግሥት በበላይነት የሚያሽከረክረው ህወሓት የኢንዱስትሪ--የሲሚንቶ፤ የጨርቃ ጨርቅ፤ የብረት መገጣጠሚያ፤ የመኪና መለዋወጫ ወዘተርፈ ኢንቬስትመንት ፈሰስ አድርጎ ይህ ክፍል በዝቅተኛ በአመት 10 በመቶ በከፍተኛ 15 በመቶ እንዲያድግ አስችሎታል። ይህ ኢንቬስትመንት የስራ እድል ከፍቷል፤ የነፍስ ወከፍ ገቢ እንዲጨምር አድርጓል፤ የግል ክፍሉ እንዲያብብ አመቻችቶለታል። የክልሉ ሕዝብ ለህወሓት ታማኝና ታዛዢ እንዲሆን አድርጓል።
የትግራይ ክልልና ሕዝብ የእድገቱ ተጠቃሚ መሆኑ አይደለም ችግሩ። እኔ የትግራይ ሕዝብ ኑሮ እንዲሻሻል እመኛለሁ። ችግሩ አይን ያወጣው፤ ነጠኛውና ጠባብ ብሄርተኛው አድልዎና የዜሮ ድምር እድገት መርህ ለአማራውና ለሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብ እድገት ማነቆ መሆኑ ነው። ይህ መወገድ ያለበት ጭካኔ የሚካሄደው በብሄሮች እኩልነትና ፍትህ ተመካኝቶ ነው። ህወሓት በብሄሮች እኩልነት ካመነ ለምን ነጻና ፍትሃዊ ምርጫ እንዲካሄድ አመቻችቶ ስልጣኑን ሕዝብ ለሚመርጠው ፓርቲ አያስረክብም?
በሰብእነት እኩልነት አለመኖር የትግራይ ሕዝብ ህይወት ከሌላው ህይወት የተለየ ሊሆን አይችልም!! ለመሆኑ የጎንደሬውን፤ የወሎየውን፤ የጎጃሜውን፤ የአፋሩን፤ የአፏኩን፤ የኦጋዴን ሶማሌውን ወዘተርፈ የኑሮ ሁኔታና ህይወት ወያኔዎችና ሌሎች ሄደው አይተውታል? ያዩት አይመስለኝም። ቢያዩትም እንደሌለ ይናገራሉ። የመሬት ነጠቃ፤ ተስፋፊነትና ምዝበራ ለመገንጠል ይረዳ ይሆን? ጥያቄውን ታሪክ ይመልሰዋል! ህወሓት ስልጣን ከመያዙ በፊት የተለየና ጥበባዊ የሆነ የበላይነት ስልት (ስትራተጅ) ተከትሎ በጎንደር፤ በወሎ፤ በጎጃምና በአፋር የለም መሬትና ሌላ የተፈጥሮ ኃብት የበላይነት ነጠቃ ዘዴውን ስራ ላይ አውሏል። ስለዚህ፤ ህወሓት ለም መሬትንና ሌሎችን የተፈጥሮ ኃብቶች ነጥቆና የትግራይን ክልል አስፋፍቶ የመገንጠል ዓላማውን የጸነሰው ገና ስልጣን ከመያዙ በፊት ነው። እንዴት?
አንባቢው የሚከተሉትን ህወሓት የፈጸማቸውን አስኳል ነጥቦች እንዲመለከታቸው አሳስባለሁ።
አንድ፤ ሕዝቡ ትጥቁን እንዲፈታ አደረገ፤ ለራሱ የሚመቹ ካድሬዎችን መለመለ፤ የአማራውን ክልል ታማኞቹ እንዲቆጣጠሩለት መለመለ እና አመቻቸ።

ሁለት፤ የትግራይ ክልል የተከዜን ድንበር ተሻግሮ ለም መሬቶችን ወደ ክልሉ አጠቃለላቸው። ነዋሪዎቹን አያሳደደ፤ እያሰረ፤ እየገደለ፤ እንዲሸሹና እንዲሰወሩ እያደረገ በምትካቸው የራሱን ወገኖች፤ ትግሬዎችን አሰፈረ፤ ለሬፈረንደም የሚጠቅሙ ሁኔታዎችን ፈጠረ።
ሶስት፤ ህወሓት ስልጣን ከመያዙ በፊትና ስልጣን ከያዘ በኋላ በነጠቃቸው ለም መሬቶች ላይ ከ500,000 በላይ የሚገመት የትግራይን ሕዝብ አሰፈረ፤ የሕዝቡን ስርጭት ቀየረው። አራት፤ ስልጣን ከያዘ በኋላ፤ ክልሎች በቋንቋና በብሄር መስፈርቶችና መለያዎች ብቻ ሕጋዊ እውቅና ይኖራቸዋል በሚል የረቀቀ ዘዴ በ1994 የሕዝብ ቆጠራ አካሄደ፤ በነጠቃቸው መሬቶች ዙሪያ የጎንደሬው፤ የወሎየው፤ የጎጃሜው፤ የአፋሩ ቁጥር በሚያስደንቅ ሁኔታ ቀነሰ፤ የትግራዩ ሰፋሪ ቁጥር አንበሳውን ብልጫ ያዘ (Numeric superiority established) ።

አምስት፤ ህወሓት ስልጣን ከመያዙ በፊት ከሱዳን መንግሥት ጋር ባደረገው የውስጥ ውል መሰረት ሰፊ መሬት ለሱዳን አስረከበ፤ የትግራይ ክልል ከሱዳን ጋር እንዲዋስን አደረገ፤ በሱዳንና በትግራይ መካከል ግዙፍ መሰረተ ልማት ተካሄደ፤ ንግድ ተስፋፋ፤ በትግራይና በሱዳን መካከል ጠንካራ የውጭ ግንኙነት ተፈጠረ።
ስድስት፤ ጎንደር ከሱዳን ጋር ከጥንት ጀምሮ የነበራት ድንበር ተቀየረ፤ ጎንደር ተከበበች። ሰባት፤ ህወሓት አዲስ ካሪኩሉም ቀየሰ፤ አዲስ የፈጠራ ታሪኮችን ጥናት አካሄደ።

ስምንት፤ የትግራይ ክልል ተለጥጦና ተስፋፍቶ ድንበሩ ወደ ቤኒ-ሻንጉል ጉሙዝ ተዘረጋ፤ ህወሓት አባይን የመቆጣጠር ብቃት አገኘ። ዘጠኝ፤ የኢትዮጵያ የድንበር ኮሚቴ በተደጋጋሚ "ለሱዳን የተሰጠው ሰፊ መሬት ሕገ-ወጥ ነው" የሚል በጥናት የተደገፈ አቤቱታ ቢያቀርብም፤ ህወሓት በእብሪተኛነት አቤቱታውን አልተቀበለውም፤ ህወሓት ያደረገው ማንም የኢትዮጵያ መንግሥት ያላደረገውን፤ ሊያደርገውም የማያስበውን ነው። ሰፊ የኢትዮጵያን ለም መሬትና ሌላ የተፈጥሮ ኃብት የያዘ መሬት ለሱዳን ማስረከብ ማለት የኢትዮጵያን ነጻነት፤ ግዛታዊ አንድነትና ደህንነት ወደ አደጋ ማሸጋገር ማለት ነው። ህወሓት ይህን መሬት ለባለውለታው ለሱዳን መንግሥት ይስጥ እንጅ ተከታታይ ትውልድ እና የወደፊት አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ መንግሥታት ውሉን እንደሚሽሩት አምናለሁ።
አስር፤ ህወሓት አባይን በበላይነት ለመቆጣጠር በሚያስችል ሁኔታ ለማመቻቸትና አካባቢውን ሙሉ በሙሉ ለመቆጣጠር በማሰብ የጎጃሙን መተከል አውራጃ ወደ ቤኒ ሻንጉል አጠቃለለ፤ የአባይን ግድብ ለራሱ የበላይነት አመቻቸ። ጎጃሜውና የቤኒ-ሻንጉል ጉሙዝ ሕዝብ እርስ በርሱ እንዲጋጭ ሁኔታዎችን አመቻቸ።

አስራ አንድ ፤ ጎንደሬው እርስ በርሱ እንዲጋጭና የትግራይ ተስፋፊነትና የበላይነት አስተማማኝ እንዲሆን ለማድረግ በሚል ስሌት ተጋብቶ፤ ተዋልዶ፤ ተዛምዶ፤ ተጎራብቶና ተደጋግፎ የሚኖረውን፤ በተለይ በጎንደር፤ በወሎና በጎጃም በሰላም የሚኖረውን ሕዝብ እርስ በርሱ እንዲናከስ ሞከረ፤ አሁንም "አንተ ቅማንት ነህ፤ አንተ አገው ነህ፤ ወልቃይቴው ትግሬ ነህ" ወዘተ በሚል መርህ የብሄር ልዩነት አለ የሚል የከፋፍለህ ግዛው ዘዴን ይከተላል። ሬፈረንደም እንዲካሄድና ጎንደር እንዲከፋፈል አመቻችቷል።

አስራ ሁለት፤ ህወሓት በአማራው ሕዝብ ላይ እልቂት (የብሄር ማጽዳትና ማጥፋት/ Ethnic cleansing and genocide) ስራውን አገር አቀፍ በሆነ ደረጃ አካሄደ፤ ሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብ በአማራው ሕዝብ ላይ ጥላቻ እንዲያድርበት አደረገ፤ ብዙ መቶ ሽህ አማራ ተገደለ፤ ከቀዬ ተባረረ፤ ተሰደደ፤ ታሰረ፤ እንዲሰወር ተደረገ። የመሬቱን መነጠቅ፤ የትግራይን ተስፋፊነት፤ የሰፈራውን ጥልቀትና ብዛት ለማጤን በአካባቢው የተገደለውን፤ የተሰወረውንና የተሰደደውን ሕዝብ ብዛት አብሮ ማየት ያስፈልጋል።
ህወሓት አሁንም ግድያውንና ሌላውን በደል ያመቻቻል ተብሎ የተገመተው በአማራው ክልል፤ በተለይ በጎንደር፤ በወሎና በጎጃም የሚኖረው አማራና ሌላ ሕዝብ ሰጥ ለበጥ ብሎ ለህወሓት እንዲገዛ፤ ለመሬቱና ለማንነቱን እንዳይነሳ ለማድረግ ነው።

አስራ ሶስት፤ የበላይነቱና ምዝበራው አስተማማኝ እንዲሆን፤ ህወሓት አማራውን ከኦሮሞውና ከሌላው ወንድሞቹ፤ እህቶቹ ጋር እንዲጋጭ አደረገ፤ አሁንም እኔ ስልጣኔን ብለቅ "ኦሮሞው" ይጨፈጭፍሃል የሚል ከእውነቱ የራቀ መርዝ በድብቅ ያሰራጫል፤ ጎንደሬው ይኼን ሃሰት አልቀበልም ብሏል። ይህ ትክክል አቋም ነው።

አስራ አራት፤ ህወሓት፤ የህበር ብሄር የፖለቲካ ፓርቲዎችና ሌሎች ስብስቦች እንዲፈርሱና በህወሓት የበላይነት እንዲያዙ አድርጓል።

ሰርጎ ገቦችን አሰራጭቷል።
አስራ አምስት፤ ህወሓት ለራሱ ተገዢና ታማኝ የሆኑ የህብረ ብሄርና የብሄር ፖልቲካ ፓርቲዎችን ፈልፍሏል።
አስራ ስድስት፤ የአማራውን ሕዝብ የተፈጥሮ ኃብትና ድንበር በማያዳግም መልኩ ለዋውጦ የጎንደሬው፤ የወሎየውና የጎጃሜው ጉረሮ እንዲታነቅ፤ ለህልውናው አስጊ የሆነ የአስተዳደር ሁኔታ እንዲፈጠርለት ወስኗል። አስተዳደሩን አመቻችቷል።

የህልውና ጥያቄ
አሁን የተከሰተውን ሁኔታ የህልውና ጥያቄ ነው የሚያስብለው ይኼው ነው። በጀግናውና በቆራጡ በኮሎኔል ደመቀ የተመራው የወልቃይት ጠገዴ እንቅስቃሴ የህወሓትን ተንኮል፤ ተስፋፊነትና የመሬት የበላይነት ስትራተጅ ስላወቀውና ስለተቃወመው አሁን የአማራ ተጋድሎ ተብሎ የሚጠራውን የሕዝብ አመጽ መሰረት ጥሏል። ይህ መስዋእት የተከፈለበትና ወደፊትም የሚከፈልበት ትግል ያስተማረኝ ነዋሪው ሕዝብ ለራሱ ክብር፤ ለራሱ ህይወት፤ ለራሱ ህልውና፤ ለራሱ የተፈጥሮ ኃብት ባለቤትነት ቆርጦ መነሳቱን ነው። በዚህ አጋጣሚ ላልፈው የማልፈቅደው መልእክት፤ ኮሎኔል ደመቀ የጀግናውን የአጼ ቴዎድሮስን ፈለግ ተከትሎ አዲሱን ትውልድ ያስተማረውን ጀግንነት አድናቂ መሆኔን ጭምር ነው።

ሰው ይወለዳል፤ ይሞታል። የማይሞተው ግን ለወገንና ለአገር የሚሰራው ቁም ነገር ነው። ይህ ምንም መተኪያ የሌለው ህያውና ዘለአለማዊ ጉዳይ ነው። ኮሎኔል ደመቀን ታሪክ መዝግቦታል፤ ተከታታይ ትውልድ ያስታውሰዋል።
የወልቃይትን ጉዳይ ከወያኔ ስርዓት እልፈት ባሻገር እናስብው የህወሓት የመሬት ነጠቃና ተስፋፊነት ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍ አጥፊ የፖሊሲ መርህ መሆኑን መካድ ለህሊናም ይቀፋል። ይህ ተስፋፊነት ብዙ ደም ፈሶበታል። በቅጡ ያልታወቀ ብዙ ሺህ ወጣት ትውልድ ታስሮበታል፤ አካለ ጎደሎ ሆኖበታል፤ እንዲሰወር ተደርጓል። የአማራው ተጋድሎ እንቅስቅሴ የሚያሳየው ሕዝብ መሬቱ ሲነጠቅና አንዱ ክልል ሲስፋፋ በመሬቱ ላይ የሚኖረው ሕዝብ አብሮ ይጠፋል፤ ይሞታል፤ ይደኸያል፤ ይታሰራል፤ ይሰደዳል፤ እንዲሰወር ይደረጋል፤ ባይሰወርም በቁሙ ይዋረዳል ወዘተርፈ ማለት ነው።

በእኔ ግምት፤ ከላይ እንዳሳየሁት የህወሓት የመሬት ነጠቃና የትግራትይ ክልል ተስፋፊነት ስራ ደም ፈሶበታል፤ ብዙ ሺህ ወጣት ትውልድ ታስሮበታል፤ እንዲሰወር ተደርጎበታል። ይህን ማሰብ የሁሉም ኢትዮጵያዊያን ግዴታ ነው። ልክ የኦጋዴን ሶማሌ ወንድሞቻችን የረሃብ ሰቆቃ እንደሚያሳስበን ሁሉ የወልቃይት ጉዳይም የእያንዳችን ጉዳይ ሆኗል። እኔ የማየው በሕዝቡ ላይ በደረሰው አሰቃቂ የህልውና ሁኔታ ነው። ይህ ሕዝብ እንዴት ሊኖር ይችላል? ህወሓትን እንጠይቀውና መልስ ይስጠን። ይህ ግዙፍ ሕዝብ ወደ የት እንዲሄድ ይፈልጋል?

እኔ የሕዝቡን ትግል የማየው በተናጠል አይደለም። የማየው ከወያኔ የአገዛዝ እልፈት ባሻገርና የህወሓት ተጠቂ ከሆነው ከአብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሰቆቃ አንጻር ነው። ይህን አስተሳሰቤን ያጠናከረልኝ ቁም ነገሩ፤ አዲስ ቆርጦና ደፍሮ የተነሳው ሁሉንም ኢትዮጵያዊያን የሚወክል፤ በተለይ የአማራውና የኦሮሞው ሰፊ ሕዝብ ትውልድ መፈጠሩና መስዋእት ለመክፈል መወሰኑ ነው።
ጎንደሬው ወያኔ የሚጨፈጭፈው "ኦሮሞ ወንድማችን ነው" ያለበት መሰረታዊ ምክንያት "አንድ አገር! አንድ ሕዝብ! የሚለውን ስሜት ለማጠናከር ነው። በገፍ እንደከብት የሚታረደው ወጣት ትውልድ ይህን የሕዝብ ወንድማማችነት እስከተቀበለ ድረስ ትግሉ ረዢም ጊዜም ቢወስድም ስኬታማ እንደሚሆን አምናለሁ። ስለሆነም፤ የውጭ ተቆርቋሪ ኃይል አገር ቤት ካለው ጋር ጠንካራና ዘላቂነት ያለው ግንኙነት መፍጠርና ማጠናከር ይኖርበታል። ይህ ለአንድ አገር ዘላቂነት፤ ለአንድ ስብጥር ሕዝብ አብሮ የማደግ አስፈላጊነት የመተባበር ጉዞው መስፋፋትና መጠናከር አለበት። እርስ በርስ የሚደረገው መጠላለፍ፤ መናኮር፤ ሽሚያና ዘለፋ መቆም አለበት የምልበት ዋና ምክንያት መጠላለፉ የሚረዳው በመሬት ላይ የሚታገለውንና የሚሞተውን ታጋይ ሳይሆን ህወሓትን ስለሆነ ነው። መረባረብ ያለብን ችግሩን በፈጠረውና ችግሩን ለመፍታት ብቃትና ፍላጎት በሌለው በህወሓት ስርአት ላይ ነው። ይህ በወጣቱ ትውልድ መሪነት በመካሄድ ላይ ያለው ሕዝባዊ አመጽ ከህወሓት እልፈት በኋላ ለምትመሰረተው የሁሉም ኢትዮጵያዊያን ቤትና ኩራት የሆነች ዲሞክራሳዊት ኢትዮጵያ ምሰሶና ማገር እንደሚሆን እገምታለሁ፤ መሆንም አለበት እላለሁ።

ይህ ትንተና ለምን አስፈለገ?
ከላይ እንዳሳየሁት፤ የዚህ ትንተና መሰረት ለማንነቱ፤ ለህይወቱ፤ ለክብሩና ለሃገሩ የሚቆረቆር ትውልድ ይህን የህወሓት ግፍ ተቀብሎ ለመኖር አይችልም የሚል ነው። ሕዝቡ ከዚህ የባሰ ችግር ሊመጣብኝ አይችልም፤ "የቁም ሙት አልሞትም" ብሎ ይታገላል። እርግጥ፤ የሃይል ሚዛኑ ለጊዜው የራሱ ባይሆንም ሕዝብ የሚደግፈው የፍትህ-ርትእ፤ የነጻነትና የእኩልነት ትግል ሊቆም አይችልም። አስርት ዓመታት ሊወስድ ይችላል እንጅ፤ በመጨረሻ ድል የሕዝብ መሆኑን ማስመስከሩ አይቀርም የሚል እምነት አለኝ። በኢትዮጵያ ዘላቂነት፤ በስብጥር ህዝቧ አንድነትና እኩልነት፤ በሕግ የበላይነትና በዲሞክራሲ አስፈላጊነት የሚያምኑ ስብስቦችና ግለሰቦች በመሬት ነጠቃና የህወሓት ተስፋፊነት፤ በድርጅታዊ ምዝበራ አደጋ ዙሪያ ግልጽ የሆነ አቋም መውሰድ ግዴታቸው ነው እላለሁ።

የተዘረፈው ኃብት፤ የተነጠቀው መሬት የኢትዮጵያዊን ኃብት እንጅ የህወሓትና ቆምኩለት የሚለው የትግራይ ሕዝብ ኃብት ብቻ አይደለም። ህወሓትና ደጋፊዎቹ “አገር አቀፍ በሆነ ደረጃ ያካበትኩት ኃብት የእኔና የክልሌ ብቻ ነው” ካሉ ከውጭ ወራሪ ሊለዩ አይችልም። የቤልጀየሙ ንጉስ ኮንጎን የራሱ የግል ኃብት አድርጎ ከመዘበረው አይለይም። የመሬት

ነጠቃና በዚህ ዙሪያ የሚደረግ የህወሓት ተስፋፊነት ከማንኛውም አስኳል ጉዳይ በበለጠ ደረጃ ለኢትዮጵያ ዘላቂነትና ለሰላም ጸር መሆኑ ብዙ መረጃ አያስፈልገውም። ይህ የፖሊሲ ጉዳይ፤ ከመሬት ላይ ከሚታየው ሃቅ ውጭ ሆኖ፤ “ለአንድነትና ለመቻቻል” ሲባል ለነገ ተብሎ የሚቆይ ጉዳይ አይደለም። ግልጽ መሆን ያለበት ዛሬ በመገናኛ ብዙሃን አፈና ሊታወቅ ባይችልም፤ በተለይ በጎንደር፤ በጎጃም፤ በወሎና በአፋር የሚካሄደው የመሬት ባለቤትነት ጥያቄ፤ የማንነትና የነጻነት/የዲሞክራሲ ጥያቄ የተቆራኙ ክስተቶች ሆነዋል። የመሬት ባለቤትነት የሰብአዊ መብት ጉዳይ ነው። የዜግነት መለያና መታወቂያ ጉዳይ ነው። የኢትዮጵያዊነት መለያችን፤ ማረጋገጫ ማህተማችን ነው። የሕግ የበላይነት መስፈርት ነው።

በዚህ አጋጣሚ ልዳሥሰው የምፈልገው አስኳል ጉዳይ የአማራው ሕዝብ ተጋድሎ የመጨረሻ ግብ ምን ይሆናል፤ ምን መሆን አለበት? የሚለውን አከራካሪ ጉዳይ ነው። የአማራው ሕዝብ በመላው ኢትዮጵያ የሚኖር፤ ከሌላው ሕዝብ ጋር በጋብቻ፤ በኃይማኖት፤ በባህል፤ በኢኮኖሚና በሌሎች ትሥስሮች የተቆራኘ፤ የተዛመደ፤ የተባበረ ሕዝብ ነው።

ስለሆነም፤ አማራው ከኢትዮጵያ ውጭ አገር የለውም። በኢትዮጵያዊነቱ ጠንቶና ኮርቶ የሚኖር ታላቅ ሕዝብ ነው። የሚጠቃውም በብሄሩ ብቻ አይደለም። በኢትዮጵያዊነቱም ጭምር ነው። አማራው የራሱን መንግሥት ለማቋቋም ፍላጎትም፤ ምኞትም፤ ዓላማም የለውም። የሚፈልገው መብቱ እንዲከበርለት ነው። “የራሱ መንግሥት ያስልፈልገዋል” የሚለው ታክቲክ ወይንም ዘዴ የህወሓቶች ፈጠራ እንጅ የአማራው ፍላጎት አይደለም!!

ታላቁ የኦሮሞ ሕዝብ ከራሱና ከመሰረታት አገሩ ለመገንጠል እንደማይችል ሁሉ፤ አማራውም ከቆመላትና በሁሉም ክፍሎች ከሚኖርባት አገር ለመገንጠል አይችልም፤ አይፈልግም።

አማራው ራሱን አጠናክሮ፤ መብቱን አስከብሮ፤ ህልውናውን መጠበቅና ማስከበር ግዴታው ነው። ይህ የህልውና ጥያቄ ነው።

ሆኖም፤ አማራው በተናጠል ኢትዮጵያን ሊታደግ አይችልም። አማራው ኢትዮጵያዊ እንደመሆኑ መጠን፤ የሚያስፈልገው የትግል ሂደት፤ በኢትዮጵያ ዘላቂነት፤ ሉዐላዊነትና በስብጥር ሕዝቧ አብሮና ተከባብሮ መኖር ከሚያምኑ ወገኖቹ ጋር ተባብሮ ስርአቱን የመለወጥ ግዴታው ከመቸውም ጊዜ በበለጠ ደረጃ የሚታይ፤ የሚጨበጥ መሆኑን አሳስባለሁ። የአማራው ሕዝብ ጠላት ስርአቱ እንጅ ሌላው ሕዝብ አይደለም። ህወሓት እንደሚለው ሳይሆን፤ የማራው ሕዝብ ለትግራይ ሕዝብ ጠላት አይደለም። ሆኖም አያውቅም። እኔ ይኼን ባደግሁበት አካባቢ አውቀዋለሁ። የትግራይ ሕዝብ በድርቅ ረሃብ ሲሰቃይ የጎንደርና ሌላው የጎረቤት ሕዝብ እንደ ደረሰለት በልጅነቴ በአካል አይቸዋለሁ።

አንድ አገር! አንድ ሕዝብ! የምልበት መሰረታዊ ምክንያት በኢትዮጵያ ሕዝብ ወንድማማችነት/እህትማማችነት፤ በክፉ ጊዜ መደጋገፍ እና አብሮ መኖር፤ አብሮ ማደግ ሙሉ

እምነት ስላለኝ ነው። ከህወሓት ውጭ ሕዝብን የግድ ተጣላ የሚል መንግሥት አይቸም፤ ሰምቸም አላውቅም። ይህ የጥላቻ መርዝና አመለካከት ኋላ ቀር ነው!! አጥፊ ነው!!

አማራው ለህልውናው ሲል ተባብሮ ይቁም ምን ማለት ነው?

ወደፊት ስመለከተው፤ እኔ በብሄርና በኃይማኖት የፖለቲካ ፓሪቲነት መደራጀትን አላምንም፤ አልቀበልም፤ ለኢትዮጵያ አያዋጣትም። ሆኖም በብሄር ወይንም በኃይማኖት፤ በማህበረሰባዊ፤ በሰብአዊና ተመሳሳይ ሁኔታዎች መሰብሰብን፤ መደራጀትን፤ ጠበቃነትን እደግፋለሁ። ማንም ብሄር ወይንም ኃይማኖት የህወሓት ኢላማ መሆን የለበትም እላለሁ። ህወሓት በብሄር ተደራጅቶ ሌሎችም በብሄር እንዲደራጁ ስላስገደዳቸው ለጊዜ የሚኖራቸው አማራጭ በብሄር መደራጀቱ አስፈላጊ መሆኑን እቀበለላሁ። ግን የጋራ የሆነ ወይንም ብሄራዊ/አገራዊ መርህ ያስፈልጋቸዋል።

አፋሮች ብብሄር ቢደራጁም አገር ወዳድ ናቸው፤ ሌሎችንም ለመጥቀስ ይቻላል። ቁም ነገሩ መድረሻችን ምን ይሆናል የሚለው ነው። መድረሻችን ለሁሉም ቤት የምትሆን ዲሞክራሳዊ ኢትዮጵያን መመስረት ነው። ይህ ራእይ እሩቅ አይመስለኝም። ግን ጥረትን፤ ህብረትን፤ መተማመንን፤ መፈላለግን ይጠይቃል።

አማራው የህወሓት ኢላማ መሆኑ አያከራክርም። ዛሬ በህወሓት አልሞ ተኳሾች የሚሞተው ጎንደሬው፤ ወሎየው፤ ጎጃሜው፤ አፋሩ ነው። ልንክደው የማንችለው ሃቅ በእነዚህ አበይት ጉዳዮች ዙሪያ ሕዝብ ከቀዬ እየተፋለሰ፤ እየሞተ፤ ከኑሮው እየተገለለ፤ እየታሰረ፤ እየተሰደደ፤ ቤቱና ንብረቱ እየተቃጠለ ነው። ይህን ግፍ የሚፈጽመው የውጭ ጠላት አይደለም፤ የኤርትራ መንግሥት አይደለም፤ አሜሪካ አይደለም፤ የሶማሌ መንግሥት አይደለም። ህወሓት ነው።

አንዳዶቻችን ይህን በመሬት ላይ የሚካሄድ ሃቅ ለመቀበል አልቻልነም። ሆኖም፤ ህወሓትን “እንቃወማለን” እንላለን። ምን ማለት ነው?

ህወሓትን እንቃወማለን ካልን ማንኛውንም ጸረሕዝብ፤ ጸረ-ኢትዮጵያ፤ ጸረ-ዲሞክራሲ ፖሊሲ መቃወም ግዴታችን ነው። በፊት ሳይነገርለት የቆየውን ሁኔታ ያባባሰው የህወሓት/ኢህአዴግ አስቸኳይ አዋጅ ነው። አዋጁ ህወሓት የፈለገውን እልቂት እንዲያካሂድ አድርጎታል። ይህ አዋጅ ሲያልቅም የሚከተለው የተሻለ ይሆናል የሚል እምነት የለኝም፤ ስርዓቱ ካልተለወጠ በስተቀር! ስርዓቱን ለመለወጥ ከተፈለገ፤ ህብረትና አንድነት እንደሚያስፈልግ አንባቢ እስከሚሰለች ድረስ ጽፌበታለሁ! አንካደው። የአንድነት ብዝርታ የሚጠቅመው ህወሓትን ነው።

ህወሓት የፈጠረውን አደጋ በግልጽ ላቅርበው

የህወሓትን የመሬት ነጠቃና የትግራይን ተስፋፊነት የሚደግፉ ግለሰቦችና ስብስቦች በመረጃ አያምኑም። ይህ ትንንተና እነሱን ለማባበልና ለማሳመን አይደለም። አይኑን የጨፈነን፤ አእምሮውን የዘጋን ግለሰብ በመረጃ ለማሳመን አይቻልም። የዚህ ጥናትና ምርምር ኢላማው  የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ነው፤ የተጎዱት ኢትዮጵያዊና ናቸው። ህወሓት በጎንደር፤ በወሎ፤ በጎጃምና በአፋር ያካሄደው የመሬት ነጠቃ፤ የትግራይ ተስፋፊነት፤ የሕዝብ ሰፈራና አዲስ ካርታ ሕገወጥ ነው። በምን መረጃዎችና በምን መስፈርቶች የሚለውን ልመልስ።

ስድስት መስፈርቶች እጠቅወማለሁ። እነዚህም፤

1. ከታሪክ አንጻር ሲመረመር የተነጠቁት መሬቶች የትግራይ አካል ሆነው አያውቁም (ታሪካው ባለቤትነት)።
2. ከመሬት ይዞታ አንጻር (Defined Territory) ሲታይ፤ የተነጠቁት መሬቶች በሕግ የሚታወቁበት መጠሪያ አላቸው፤ ጎንደር፤ ወሎ፤ ጎጃም፤ አፋር ይባላሉ። በእነዚህ አካባቢዎች የሚኖረው ሕዝብ ጎንደሬ፤ ወሎየ፤ ጎጃሜ፤ አፋር ይባላል። ይህን ስል ሌሎች ብሄሮች የሉም ማለቴ አይደለም። ጎንደር የተለያዩ ብሄሮችንና ኃይማኖቶችን የምታስተግድ ክፍለ ሃገር ናት (ከተፈጥሯዊ ይገባኛልነት)።
3. ከአስተዳደር አንጻር ሲታይ የሚያሳየው፤ እነዚህ ክፍላተ ሃገራት በትግራይ ተወላጆች የበላይ ባለሥልጣናት (ጠቅላይ ገዢዎች ወይንም አስተዳዳሪውች) አልተገዙም። ለትግራይ አስተዳደር ግብር ከፍለው አያውቁም (ከአስተዳደር ተከታታይነት)።
4. ከሕዝብ ስርጭት አንጻር ሲመረመር፤ የህወሓት ተስፋፊነት የነዋሪውን የብሄር ስርጭት በኃይል ከመቀየሩ በፊት (Before TPLF's enforced demographic changes in the annexed lands and its 1994 census) ያለው ሁኔታ የሚያሳየው፤ ከአፋር ክልል ውጭ፤ በተነጠቁት አካባቢዎች የሚኖረው ሕዝብ፤ ከ98 በመቶ በላይ አማራ፤ ሌላው ቅማንት፤ አገው ወዘተርፈ መሆኑን ነው። በእንዚህና በአፋር ክልል የሚኖረው ጎንደሬ፤ ወሎየና ጎጃሜ፤ አፋር እንጅ፤ የትግራይ ብሄር አባል አለመሆኑን ነው (ከአያት፤ ከቅድመ አያት ነዋሪነትና ተከታታይነት)።
5. ከባህል፤ ከስነ ልቦና፤ ከስነ ጥበብ፤ ከሕዝብ ግንኙነት፤ ከጋብቻ፤ ከመከደጋገፍና ከተመሳሳይ እሴቶች አንጻር ሲታይ በጎንደር የሚኖረው ሕዝብ በጎንደሬነቱ እንጅ በትግሬነቱ አያምንም፤ ወልቃይቴው "ጎንደሬ፤ አማራ ነኝ፤ ማንነቴ ይከበር" እያለ በግድ

"ትግሬነትን ተቀበል" የሚለው ጭፍን መርህ ህገ-ወጥ ነው። ወሎየው፤ ጎጃሜውና አፋሩም ተመሳሳይ እምነትና ትስስር አለው።
6. ከጅኦግራፊ አቀማመጥና ከኢኮኖሚ ትሥስር አንጻር ሲታይ ጎንደሬው በግልጽ የሚታወቅ ድንበር ነበረው፤ ወሎየው፤ ጎጃሜውና አፋሩም ተመሳሳይ ድንበር ነበረው። የኢኮኖሚውና የማህበረሰብ ግንኙነቱም የሚያንጸባርቀው ይህን ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፍ የቆየ ድንበርና በመሬት ላይ የሚታይ የኑሮ ግንኙነቶች ሁኔታ ነው።

ባጠቃላይ ከታሪክ፤ ከመሬት ይዞታ፤ ከአስተዳደርና ከግብር ክፍያ፤ ከጅኦግራፊ፤ ከሕዝብ ስርጭት፤ ከስነ ልቦና ባህል ወዘተርፈ አንጻሮች ሲታይ ህወሓት የመሳሪያ ኃይልን ተጠቅሞ የፈጠረው አዲስ የመሬት ነጠቃ፤ ተስፋፊነት፤ የሕዝብ ሰፈራና አዲስ ካርታ ሕገወጥ ነው። ይህን ሕገ-ወጥና አዲስ የታሪክ ፈጠራ ለማጠናከር እፈልጋለሁ።

አንደኛ፤ የመሬት ነጠቃ ለኢትዮጵያና ለመላው ሕዝቧ አደገኛ እንደሆነ በተደጋጋሚ አሳስቤአለሁ። በመረጃ የተደገፈውና የኢትዮጵያዊያንንና የውጭ ባለሞያዎችን አድናቆት ያስከተለው The Great Land Giveaway (የመሬት ነጠቃና ቅርሚት) 2011 መጽሃፌ የመሬት ነጠቃ ለአገራችን የሚያስከትለውን አደገኛ ክስተት አስመልክቶ ሊከሰቱ የሚችሉትን እንደምታዎች አስቀድሞ አሳስቦ ነበር። ባለፉት ሃያ አምስት ዓመታት፤ በአብዛኛዎቹ የኢትዮጵያ ክልሎች የሚካሄደው ግጭት የመሬት ነጠቃ፤ ቅርሚትና የማንነት ጥያቄ አግባብ ያለው መፍትሄ አለማግኘቱ መሆኑን በተደጋጋሚ አይተናል። የመሬት ባለቤትነት ህይወት ነው። ባለቤትነት ቤተሰብ ነው፤ ክብር፤ ዜገነት፤ ማንነት ነው። ከማንነትና ከዜግነት ጋር ቀጥታ የሆነ ግንኙነት ያለው አበይት ጉዳይ ነው። ዛሬ ሁለቱን ለመለየት ወደማይቻልበት ደረጃ ደርሰናል።

የመሬት ባለቤትነት ጥያቄ የነጻነትና የሰብአዊ መብት መከበር ወይንም አለመከበር ጥያቄ ነው። ዲሞክራሲ ስንል ባለቤትነትንም አብረን ማጤን ግዴታችን ነው። ዲሞክራሲ በባዶ መሬት ወይንም በአየር ላይ የተንሳፈፈ ነገር አይደለም። የመሬት ባለቤትነት በተባበሩት መንግሥታት እውቅና አለው። United Nations Declaration on the Rights of Indigenous Peoples አንቀጽ አንድ (Article 1) እንዲህ ይላል። Indigenous peoples have the right to the full enjoyment, as a collective or as individuals, of all human rights and fundamental freedoms as recognized in the Charter of the United Nations, the Universal Declaration of Human Rights and international human rights law.

ህወሓት የነጠቀው መሬት የሕዝቡን ሰብአዊና ማህበረሰባዊ መብቶች አናግቶታል፤ ነስቶታል፤ ነጥቆታል።

ስለሆነም፤ ህወሓት አብዛኛው የአለም የሚከተለውን ሕግ ጥሷል። የራሱን ሕገ-መንግሥት አክብሮ አያውቅም።

መሬቱን የተነጠቀ ሕዝብ ህይወቱንም፤ ማንነቱንም፤ ክብሩንም፤ ዜግነቱንም፤ መብቱንም ይገፈፋል። የዜጎች መብቶች ሲገፈፍ የሚከተለው ቀውስ ከባድ መሆኑን በሌሎች አገሮች ብቻ ሳይሆን በኢትዮጵያም እያየነው ነው። የርዋንዳ ታሪክ ትዝ ሊለን ይገባል። በህወሓት የመሬት ነጠቃ ደስ የሚላቸው ደጋፊዎችና የውጭ ኃሎች እንዳሉ ማመን ግዴታችን ነው። ሁለተኛ፤ ህብረ ብሄር የሆኑ ስብስቦችንና ግለሰቦችን ከሚያስማሟቸው መርሆዎች መካከል (Fundamental principles) በሕግ ፊት የእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ዜጋ መብት እንዲከበር፤ ማንኛውም ብሄር በሕግ ፊት የእኩልነት መብቱ እንዲከበር የሚለውን ይጨምራል። ባለቤትነት የዚህ ተመክሮ አካል ነው። ይህ ሲባል የአፏኩ መብት ከዐማራው፤ ከኦሮሞው፤ ከጉራጌው፤ ከትግራዩ ወዘተርፈ ሊለይ አይችልም የሚል

መሆኑ አያከራክርም። ይህ ሲባል ህወሓቶች እንደሚከተሉት ጭፍንና አጥፊ መርህ የትግራይ ሕዝብ የሚመራበት “የይገባኛል” ፖለቲካ ከአማራው መለየት አለበት ማለት አይደለም። በአንድ አገር የተለያዩ ህጎችና መመሪያዎች ሊኖሩ አይችልም። ከላይ ስለ ጠባብ ጎሰኛነት አድልዎ እንዳነሳሁት፤ አንዱ አስገባሪ ሌላው ገባሪ ሊሆን አይችልም። ይህ ከሆነ ስርዓቱ ሙሉ በሙሉ በህወሓት ተማርኳል፤ የህወሓት መሳሪያ ብቻ ሆኗል ማለት ነው። የኢትዮጵያ የሚባል መንግሥት የለም ማለት ነው። በመሰረቱ ሲታይ የጎንደሬው፤ የወልቃይቴው መብትና የመሬት ባለቤትነት ከትግራዩ የተለየ ሊሆን አይችልም። የሆነው ግን ይኼው ነው። ለጎንደሬው፤ ለጎጃሜው፤ ለወሎየው፤ ለአፋሩ የተለየ መርህ ሊኖር አይችልም። ግን ሆኗል። የዐማራው ብሄር መብት ከሌላው ብሄር መብት የተለየ ሊሆን አይችልም። ግን ሆኗል።

## ጉረሮው የታነቀ ሕዝብ

በህወሓት የበላይነትና አዛዥነት የሚካሄደው የኢህአዴግ መንግሥት ይህን የተሳሳተና አደገኛ የህወሓት ሴራ ሊተቸው አልቻለም፤ የሚችልም አይመስለኝም። ኢህአዴግ ህወሓትን ይፈራዋል!! ኢህአዴግ ሊሸሸው የማይችለው ሃቅ አንድ ነው። ህወሓት የሌለ ታሪክ ፈጥሮ የትግራይን ክልል አስፋፍቷል።
የመሬት ነጠቃውና የትግራይ ተስፋፊነት የአማራውን ሕዝብ ጉረሮ አንቆታል፤ እንዳይጮህ ሰንጎ ይዞታል። ጉረሮው ታንቋል ስል የሚኖርበት መሬቱ ተነጥቋል፤ ህይወቱ ተናግቷል፤ መብቱ ታፍኗል ማለቴ ነው። የተፈጥሮ ኃብቱ ሲነጠቅ የሚከተለውን ግፍ በአጭሩ ለማሳየት ሞክሬአለሁ።

ለምሳሌ፤ የተፈጥሮ ኃብት ለእድገት ወሳኝ ነው። አማራው የወንዞች ባለጸጋ ነው። ሆኖም ተጠቃሚ አይደለም። አብዛኛው የአማራ ክልል ሕዝብ ከወንዞቹ የሚመረት የኤሌክትሪክ መብራት ተጠቃሚ አይደለም። መብራቱ በራሱ ወንዞች ተመርቶ ወደ ትግራይ ይተላለፋል። አማራው ቢበዛ የሚጠቀመው ኩራዝ ነው። እንኳን የገጠሩ ሕዝብ ከተማዎችም መብራት የላቸውም። በትግራይ ክልል 197 ከተማዎችና አካባቢዎች የመብራት አገልግሎት አላቸው። የንጹህ ውሃ ተጠቃሚው ሕዝብ ቁጥር ከሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጥር ይበልጣል። የቴሌፎን አገልግሎትም ተመሳሳይ ነው፤ 64 በመቶ የሚገመተው የቴሌፎን አገልግሎት አለው። ይህ እድል ለአማራው ሕዝብ ተነፍጎታል። ይህ የተዛባ ኢንቬስትመንት ፖሊሲ ውጤት ነው።
ወደ ዋናው ጉዳይ ስመለስ ህወሓት መስፋፋት ስኬታማ የሆነው ህወሓት የመሳሪያ ኃይል ስላለው ነው እንጅ በታሪክ ስለተደገፈና ነዋሪው ሕዝብ መሬቱን “ንጠቀኝ” ስላለው አይደለም። ሕዝብ የራሱን ጉረሮ አያንቅም፤ የሚያንቀውን ይታገላል፤ እየታገለም ነው። በዚህ አንጻር ሲታይ የውጭ ኃይል የሚያደርገው በደልና ህወሓት የሚያደርገው ግፍ ተመሳሳይነት አላቸው።

## ታሪክን መበረዝ ሃቁን አይቀይረውም

የታሪክን መበረዝ ካልተቀበልን በስተቀር (እኔ አልቀበልም)፤ ሰቲት ሁመራ፤ ወልቃይት ጠገዴና ሌሎች ህወሓት ኃይሉን ተጠቅሞ ወደ ራሱ ክልል ያካተታቸው ለም መሬቶች፤ ወንዞችና ሌሎች የተፈጥሮ ኃብቶች ላለፉት ሺህ ዓመታት በትግራይ አስተዳደር ወይንም አገዛዝ ስር ውለው አያውቁም። ይህ ሲባል የትግራይ ሕዝብ የለም መሬቶች ተጠቃሚ አልነበረም ማለት አይደለም። በአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ብዙ ሽህ የትግራይና የኤርትራ ሕዝብ በሰቲት ሁመራ ዘመናዊ እርሻ ስራ ይሰራ እንደ ነበር አስታውሳለሁ። ይህ ወደፊትም አስፈላጊ ነው። የሕዝብ ስምምነት ካለ ማለቴ ነው። ህወሓት የፖለቲካውን ስልጣን ማርኮ አገሪቱን በሙሉ ከያዘ በኋላ የሆነው ከዚህ የተለየ ነው። የውስጥ “ወረራ” ቢባል አግባብ አለው።
ኢትዮጵያ የዘረኛው፤ የጠባብ ብሄርተኛው፤ የጎጠኛው፤ የትእቢተኛው፤ የሙሰኛው የህወሓት ምርኮኛ አገር ሆናለች። ምርኮኛ በመሆኗ ህወሓትና ደጋፊዎቹ ለራሳቸውና ለቆሙለት ክልል አንድ (መሪው ክልል ማለት ነው) ጠበቃ ሆነው፤ ካርታዋን እንደፈለጉት ለውጠውታል። ለውጠው ነዋሪውን “ተቀበል፤ አጽድቅ፤ ይህን ካላደረግህ ወዮልህ” ይሉታል። የህወሓት አልሞ ተኳሾች አስፈጻሚ ኃይል ሆነው ያገለግላሉ። እንደፈለጉት ይገላሉ፤ ያስራሉ፤ የፈለጉትን እንዲሰወር ያደርጋሉ። ይህ የህወሓት የመሬት ነጠቃና የትግራይ ክልል ተስፋፊነት ስኬታማ የሆነው፤ በሕዝብ ፈቃድና ፍላጎት ሳይሆን በየመሳሪያ ኃይል ነው። ይህ የመሳሪያ ኃይል የሚደገፈው በኢትዮጵያ ሕዝብ ባጀት ነው። በሌላ አነጋገር ብናስቀምጠው የኢትዮጵያ ሕዝብ በራሱ ኃብት ይቀጣል፤ ይታፈናል፤ ይገዛል ማለት ነው።

ህወሓት የኢትዮጵያን ታሪክና የሕዝቡን ትሥስር አፈራርሶ፤ አገሪቱን ምርኮኛ አድርጎ የአገሪቱን ካርታ ሙሉ በሙሉ ቀይሮታል። ህወሓት/ኢህአዴግ ስልጣን ከያዘ በኋላ “የሀገሪቱን የፖለቲካና የአስተዳደር ካርታ” ለህወሓት የበላይነት በሚጠቅም ጮሌነት ለውጦታል። ከላይ በመረጃ እንዳሳየሁት፤ አዲሱ ህወሓት ያወጣው ካርታ ያስተጋባው የሕዝቡን ታሪክ፤ ጅኦግራፊ፤ ድንበር፤ ግንኙነትና ትሥስርና ጥቅም ሳይሆን የህወሓትን ጥቅምና የቡድኑን ተስፋፊነት ነው። ህወሓት የጎንደርን፤ የወሎን፤ የጎጃምንና የአፋርን ለም መሬት ድንበርና ይዞታ፤ ነዋሪውን ሕዝብ በሚያደክምና በሚያደኸኝ ደረጃ ቀይሮታል። የወልቃይት ጥያቄ ተብሎ የሚጠራው የማንነትና የባለቤትነት ትግል የተከሰተው በዚህ ምክንያት ነው።
የዚህ የማንነትና የመሬት ባለቤትነት ጥያቄ አድማስ ሰፊ መሆኑን ላሰምርበት እፈልጋለሁ። ጥያቄው የነጻነት፤ የፍትህ፤ የዲሞክራሲና የኢትዮጵያዊነት ጭምር ነው። ለዚህም ነው፤ ሁሉንም ኢትዮጵያዊያን ይመለከታል የምለው።
ህወሓትና መሰል ደጋፊዎቹ ይህን የመሬት ነጠቃና የመስፋፋት ሃቅና ያስከተለውን አደጋ ይክዳሉ። ባለሞያዎችና ተመልካቾች የሚሰጡት ምክንያት እንዲህ የሚል ነው። የትግራይን ጥቅምት በሚመለከት ጉዳይ ላይ ህወሓትና ሌሎች የትግራይ ስብስቦች ተመሳሳይ አቋም አላቸው የሚል አመለካከት አለ። ሃቁን ለማወቅ የምንችለው እኔ የምተቸውን በመቀብል ብቻ አይደለም፤ የታሪክ ምሁራንን ሰነዶች በመመርመርና በዋቢነት በመጥቀስ ጭምር ነው። ይህን በሚመለከት ብዙ ጥናቶችና መረጃዎች ተሰብስበዋል።

የምጠቀመው እነዚህን መረጃዎች ይሆናል።

አንድ፤ “ ወልቃይት ጠገዴና አላማጣ ኮረም በአጼ ዮሓንስ ዘመን በትግራይ ሥር አልነበሩም”

ህወሓቶ የትግራይ ነበሩ ይላሉ፤ ጎንደሬዎችና ሌሎች አልነበሩም ይላሉ። ሃቁን ከታሪክ አንጻር እንየው። “አጼ ዮሓንስ ከ 1871 ዓ.ም እስከ 1889ዓ.ም (እ.ኤ.አ) ኢትዮጵያን የመሩ ንጉስ ናቸው:: ንጉሱ በንግሥና ዘመናቸው የራሳቸው ጠንካራና ደካማ ጎን ቢኖራቸውም፣ ከጠላት ድርቡሽ ጋር በመፋለም ለሀገራቸው ክብር ሕይወታቸውን የሰጡ ንጉስ ናቸው::” ይህ ኢትዮጵያዊነታቸው እንዳለ ሆኖ ሳለ፤ “ጥቂት የማይባሉ የሕወሀት ሰዎች፣ ከወልቃይትና ጠገዴ ጋር በተያያዘም የሚጠቅሱት እሳቸውን ነው” ይልና ደራሲው “ወልቃይት እና ጠገዴ ፣ ጥንት በአጼ ዮሓንስ ዘመነ መንስግት በትግራይ ስር ነበረች ” በማለት እንደ ዋና የመስፋፋት መከራከርያ ሲያቀርቡት ይደመጣል” ይላል። በእኔ ግምትና ጥናት ይህ የፖለቲካ ውሳኔ እንጅ በታሪክ የተደገፈ አይደለም። ለማስታወስ ያህል፤ ህወሓቶችና ሌሎች ጠባብ ብሄርተኞች የኢትዮጵያን ታሪክ ሂደት ተቀብለው አያውቁም። “ኢትዮጵያ የመቶ አመት ታሪክ ያላት አገር ናት” የሚል ቡድን እንዴት ይታመናል? የህወሓት አባቶች ከኢትዮጵያ ይልቅ ለኤርትራ ይከራከራሉ፤ ጸረ-ኢትዮጵያ የሆነ አቋማቸው በየቀኑ ይሰማል። ጸረ-ኢትዮጵያዊነትና እውነተኛ ታሪክ፤ ዘመናዊነትና ፍትሃዊ እድገት አብረው አይሄዱም። ጸረ-ኢትዮጵያና ጸረ-የኢትዮጵያ ሕዝብ የሆነ አቋም ይዞ ኪራይ ሰብሳቢነትንና ሙስናን ለመቅረፍ አይቻልም። በራሱ የሚተማመን ኢኮኖሚ ለመመስረት አይቻልም። የመሬት ነጠቃ ስልት ሊያስከትል የሚችለውን መዘዝ ለመቋቋም አይቻልም።

ህወሓቶች በማንኛውም አበይት ጉዳይ የሚያቀርቡት፤ ለምሳሌ ኤርትራን፤ እድገትና ፍትህን፤ የመሬት ነጠቃን፤ ድንበርን፤ ድርጅታዊ ምዝበራን፤ ኪራይ ሰብሳቢነትንና ተመሳሳይ መረጃን ከእውነቱ በራቀ ሁኔታ ነው። ይህን ሃቅ ታዋቂ ምሁራንና ተቋሞች ዘግበውታል። የትግራይ መስፋፋት ስሌት ከዚህ የተለየ አይደለም። “በአጼ ዮሓንስ ዘመን የነበረው የትግራይ ግዛትና፣ አጠቃላዩ የኢትዮጵያ ግዛት ምን እንደሚመስል በዝርዝር በሀገር ውስጥና በውጭ ሊቃውንት ተጽፏል:: ስለ ወልቃይትም አስተዳደር በማን ስር እንደነበረ በዝርዝር ጽፈውታል:: ለዚህም የእውቁን የፈረንሳዊ የጂኦግራፊ ፕሮፌሰር ኤሊስ ሬክለስ መጽሓፍን በዋቢነት መጥቀስ ይቻላል:: በዩንቨርሲቲ ኦፍ ብረስልስ የኮምፓራቲቭ ጂኦግራፊ (University of Brussels, Professor of Comparative Geography) ፕሮፌሰርና የዴፓርትመንቱ ሀላፊ የነበረው ይሄው ፕሮፌሰር ፤ በ1880 ጀምሮ በርካታ መጽሓፎችን በዓለም ጂኦግራፊ ላይ ጽፏል:: እነዚህም መጽሓፍቱ ከለንደንና ፓሪስ ጆኦግራፊካል ሶሳይቲ የወርቅ ሜዳሊያ ተሸላሚ አድርገውታል::” ከእነዚህ መጻሕፍት አንዱ በ 1880 የተጻፈው The Earth and its Inhabitants የሚለው ሲሆን፤ ዘጠኝ ተከታታይ ክፍሎች አሉት። የዚሁ መጽሓፍ ክፍል አራት በገጽ 443 ላይ የሰሜን እና ምስራቅ አፍሪካን የወቅቱን ጂኦግራፊ በዝርዝር ይተነትናል:: በአጼ ዮሓንስ ዘመን የነበረውንም የኢትዮጵያን ክፍላተ ሀገራት በዝርዝር ቁልጭ አድርጎ እንዲህ ጽፎታል::

“The Amhara government provinces are: Dembia, Chelga, Yantangera, Dagossa, Kuarra,
Begemidir, Guna, Saint, Wadla, Delanta, Woggera, Simen, Tselemt, Armachiho,Tsegede, Kolla Wogerra፣ Waldiba and Wolkait”

Tigray territories from the book – The Earth and its Inhabitants

“ከላይ ለመግለጽ እንደሞከርኩት ይህ ጽሁፍ የተጻፈው በ1880ዎቹ አጼ ዮሃንስ የሀገሪቱ ንጉስ በነበሩበት ዘመንና የተጻፈውም በጊዜው ከነበሩ ከተለያዩ የጂኦግራፊካል ሶሳይቲዎች የወርቅ ሜዳይ ተሸላሚ በሆነ ባለሙያ ፕሮፌሰር ነው:: ይህ በ1880ዎቹ የተጻፈ መጽሓፍ እንደሚያስረዳው በአጼ ዮሃንስ ዘመን ወልቃይት: ጠለምት : ዋልድባ : አላማጣ : በሙሉ በትግራይ ስር አልነበሩም:: እነዚህን ቦታዎች በስም ጠቅሶ እንደሚነግረን በትግራይ ስር ሳይሆን በጎንደር ስር ነበሩ” ይልና “በአጼ ዮሓንስዘመን ወልቃይትና ጠግዴ በትግራይ ስር ስለነበሩ ነው አሁን ወደ ትግራይ የጠቀለልናቸው ” የሚለው መሰረት የሌለው መሆኑን ይሄ መረጃ ያሳየናል” በሚል ደምድሞ “ከአጼ ዮሓንስ በፊትስ እነዚህ ቦታዎች ይተዳደሩ የነበሩት በማን ነው?” ጥያቄ አቅርቦ በመረጃ ደግፎ ይመልሰዋል።

ሁለት፤ “በኣጼ ቴዎድሮስም መን ወልቃይት ጠገዴ በትግራይ ስር አልነበሩም”

ኣጼ ቴዎድሮስ በ(1818 – 1868 እ.ኤ.አ) የኢትዮጵያን አንድነት ለማስከበር ከፍተኛ ጀብድ የሰሩ ንጉስ ነገስት፤ ስመ ገናና ኢትዮጵያዊ ንጉስ ነበሩ:: በየቦታው የነበሩ መሳፍንትን አሸንፈው፣ ማዕላዊ መንግስት ከመሰረቱ በኋላ፣ ቀጣይ ራዕያቸው የምዕራብያውያንን ቴክኖሎጂ እዚሁ ኢትዮጵያ እንዲመረት ማድረግ ነበር:: ለዚህም ከበርካታ አውሮፓ ሀገራት ጋር ግንኙነት መስርተው ነበር:: የአውሮፓውያን ጥበበኞችን ኢትዮጵያ ለማስቀረት እና ጥብቅ ግንኑነት ለመመስረት፣ አጼ ቴዎድሮስ ልጃቸውን ለአንድ ስዊስ ኢንጂነር እስከመዳር ደርሰው ነበር:: በዚህም ምክንያት በርካታ አውሮፓውያን ጠቢባን በአጼ ቴዎድሮስ ዘመን ኢትዮጵያ መጥተዋል:: እነዚህም ባለሙያዎች ኢትዮጵያ መጥተው ስለ ሀገሪቱ በዝንርዝር ጽፈዋአል:: የእንግሊዝ መንግስትና የኢትዮጵያ ግንኑነት መሻከር ሲጀምር፣ እንግሊዞች ስለኢትዮጵያ ይበልጥ የማወቅ ፍላጎታቸው ጨመረ:: የእንግሊዝ መንግስት የintelligence ሰዎችም የእንግሊዝ መንግስት ፓርላማና የጸጥታው ኃይል ኢትዮጵያን በሚገባ ያውቃት ዘንድ ትዕዛዝ ወጣ:: የእንግሊዙ Topographical and Statistical Department of The War Office ኤ . ሲ ኩክ (A. C. Cook) በተባለ እንግሊዛዊ ኮሎነል አማኻኝነት ስለ ኢትዮጵያ ከ15ኛው ክፍለ ዘመን ጀመሮ በተለያዩ እውሮፓውያን ተጻፉ መጻሕፍት ባንድ ላይ እንዲጠርዘ ተደረገ:: የሚደንቀው ይሄ መጽሓፍ በ 1867 ዓ.ም እ.ኤ.ኣ የታተመው በግስቲቷ ጥያቄ ለእንግሊዝ ሀውስ አፍ ኮመንስ

ሎወር ሀውስ ግብአት (House of Common lower House) ይውል ዘንድ መሆኑ ነው::
በዚሁ መጽሓፍ ውስጥ፤ የወቅቱ የኢትዮጵያ ዝርዝር ጉዳይ ተጽፏል:: ይሄውም መጽሓፍ ስለ ወልቃይትና ጠገዴም በአጼ ቴዎድሮስም ይሁን ከሳቸው በፊት በማን ስር ይተዳደሩ እንደነበር በዝርዝር ያትታል::
“The Provinces of Amhara are : Simen, Waldibba, Wolkait,Wogera,Chilga, Kuara, Belesa, **Fogerra, Damot, Gojjam, Begemidir, Beshilo ….. Waldiba situated to the NW of Semein between the Tekeze and the Angereb,** extends as far as the junction of the two rivers. Welkait is to the west Of Waldiba it is intersected through its whole length by the two river tekuar and guang. It is more wooded than waldiba..” (**Routes in Abyssinia (printed in 1867 G.C) page 188)**
ይሄው ታሪካዊ መጽሓፍ በወቅቱ የነበረውንም የትግራይ ክፍለሀገር ድንበር እና ግዛት እነማን እንደነበሩ በማያሻማ ቋንቋ እንዲህ ይነግረናል፡፡
“The territory of Tigre whose capital is Adwa, is bounded on the West by Shire, on the Southwest by Temben and Adet on the South by Geralta on the South –East by Haramat, on the East by Agame, and on the North by the rivers of Mereb and Belessa”
የትግራይ ግዛትስ? ብሎ ለሚጠይቅ ወገን ፤ ይሄው መጽሓፍ በወቅቱ የነበርቸው ትግራይ ምን እንደምትመስል እንዲህ ሲል አስፍሮታል በዚሁ መጽሓፍ ላይ ገጽ 187 – 188 የትግራይን ግዛት እንዲህ ሲል ይገልጸዋል።
“The territory of Tigray whose capital is Adwa is bounded on the west by Shire, on the south west by Temben and Adet, on the south by Geralta, on the South East by Haramat, on the East by
Agamae, and on the North by the Rivers Mereb and Belessa.”
M Northern Ethiopia areas
የትግራይ ወሰን የት ላይ ነበር?
**Routes in Abyssinia (printed in 1867 G.C) page 188)** “በ 18ተኛው ክፍለ ዘመን የትግራይን ወሰኖች በማያሻማ ሁኔታ በግልጽ አስቀምጦታል:: የትግራይ ወሰን በምዕራብ – ሽሬ ፤ በምዕራብ ደቡብ – ተምቤን እና አዴት ፤ በደቡብ – ገር አልታ ፤ በምስራቅ – አጋሜ ፤በሰሜን – መረብና በለሳ ናቸው:: የታሪክ ሰነዶች በአጼ ቴዎድሮስም ዘመን እንደሚነግረን ፤ ወልቃይትና ጠገዴ በትግራይ ስር አልነበሩም::” ህወሓት ስልጣን ከመያዙ በፊትና ስልጣን ከያዘ በኋላ በተስፋፊነት ከጎንደር፤ ከወሎና ከጎጃም የነጠቀው መሬትና ይህን የሚያንጸባርቀው ካርታ ከታሪክ ጋር ምንም ግንኙነት የለውም። መተከል ለምን ወደ ቤኒ ሻንጉል ተቀላቀለ? ህወሓት ለምን የጎንደርን መሬት ለሱዳን አስረከበ? ከመስፋፋት ጋር ቀጥታ የሆነ ግንኙነት አለው።

ሶስት፤ “ በዘመነ መሳፍንት ዘመንም ወልቃይት ጠገዴ በትግራይ ስር አልነበሩም”
በዘመነ መሳፍንት “ኢትዮጵያ ማዕከላዊ መንግስት አልነበራትም:: መሳፍንቶች የገነኑበትና በሀገሪቱ ማዕከላዊ አስተዳደር የጠፋበት ዘመን ነበር:: በዚህ ማዕከላዊ የመንግስት ሕግ በሌለበት ወቅት እንኳን ወልቃይት፥ጠገዴ፥ ዋልድባ ፥ አላማጣ፥ ኮረም እና የመሳሰሉ ቦታዎች በትግራይ ስር አልነበሩም…..ጀምስ ብሩስ የተባለው ስኮትላንዳዊ ፥ በዘመነ መሳፍንት ኢትዮጵያ መጥቶ ኢትዮጵያ በዘመነ መሳፍንት ምን ትመስል እንደበረ፥ ቁልጭ አድርጎ አስቀምጦታል:: እያንዳንዱ መስፍንት ግዛቱ የት ድረስ እንደነበረ፥ የትኛው መስፍን ማንን ይገዛ እንደነበረ በሰፊው ተንትኖታል:: በዚህም መሰረት ስለ ትግራይ ግዛትና እንዲህ ሲል ምስክርነቱን ይሰጣል :: **Travel to discover source of the Nile**፤ Volume 3 page 582 እንዲህ ይላል።

“Tigre is bounded by the territory of the Bahirenegash that is by the river Mereb on the East and Taccazze upon the west. It is about one hundred and twenty miles broad from E. to W. and two hundred from N. to S. በ Chapter 10 ላይ Geographical division of Abyssinia into province በሚለው አንቀጹ ላይ በይበልጥ ቁልጭ አድርጎ እንዲህ ያስቀምጠዋል።” The first division is called Tigre, between Red Sea and the river Tekeze. Between that River (Tekeze) and the Nile Westwards where it bounds the Oromo, it is called Amhara. Tekezze is the natural boundary between Tigre and Amhara”
እነዚህ የታወቁ ምሁራንና ተመራማሪዎች በተለያየ ጊዜ ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ያዩትንና የተገነዘቡትን መረጃ አቅርበዋል፤ ያቀረቡት ሁሉ ተመሳሳይ ነው። አግባብ የሚኖረው የህወሓት የመሬት ነጠቃና መስፋፋት ስኬታማ የሆነው በታሪክ ሳይሆን የፖለቲካ የበላይነት ይዞ በመሳሪያ ኃይል ስኬታማ ለማድረግ መሞከሩ ነው።

አራት፤ **“ወልቃይት በ1630ዎቹ** ዘመና በማን ስር ነበረች?”
“በ16ኛው መቶ ኢጋማሽ ላይ ያሉ ያታሪክ መዛግብትም የሚናገሩት ተመሳሳይ ነገር ነው: በተለያዩ ወገኖች ተደጋግሞ የሚጠቀሰው የማኑኤል በሬዳም መጽሓፍ የሚተነትነው ያንኑ ነው: ይሄ መጽሓፍ የተጻፈው በ1634 ሲሆን በወቅቱ የነበረውን የትግራይ ግዛት በዝርዝር አስቀምጧል: እሱም እንደሌሎቹ መጻህፍት የትግራይ ድንበር ተከዜ እንጂ ተከዜን ተሻግረው ያሉት ወልቃይትና ጠገዴ

ናቸው አይልም: «Tractatus tres historico-geographici (1634): A seventeenth century historical and geographical account of Tigray, Ethiopia (Aethiopistische Forschungen) 1634» የመጀመሪያ ምዕራፍ ስለ ትግራይ ግዛት እንዲህ ይላል፡፡

“Among all the kingdoms that the Emperor of Ethiopia possesses today one of the greatest if not the greatest and the most important is the kingdom Tigre. From north to south, that is from the limits of the Hamasen to Enderta, it covers an areas of from ninety to one hundred leagues (3.2 miles); and from the east, which is besides Dancali, located at the entrance to the Red sea to the southern end of the Red Sea, to the west bounded by the Tekezze River beside the Semen, it covers an area of similar size, so that the Kingdom has a nearly circular shape.”

ታሪክ እንዲሁ በፈጠራና በሃይል ትክክል ነው ለማለት አይቻልም። ታሪክ የሚጠቅመው ሃቁን ለሚቀበልና ለሚያስተናግድ እንጅ ለጠባብ ብሄርተኞች/ጎጠኛ ጥቅም መሳሪያ ሊሆን አይችልም። ኤርትራን ከእናት አገሯ የነጠለ ቡድን የፈለገውን መረጃ ብናቀርብ እኔ ወይንም ሌሎች የሚሉትን ለመቀበል ፈቃደኛ እንደማይሆን አልጠራጠርም።

ሆኖም፤ ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ህይወት ተቆርቋሪ የሆንን ኢትዮጵያዊያን የወልቃይት ጠገዴ ጉዳይ የሁላችንም ጉዳይ መሆኑን መቀበል ግዴታችን ነው። የኦሮሞ ጉዳይ ያገባናል፤ የአ፟ክ ጉዳይ ያገባናል፤ የአፋር ጉዳይ ያገባናል የሚለውን እቀበላለሁ።

በተመሳሳይ፤ ኢትዮጵያዊያን የወልቃይት ጉዳይ የራሳችን ነው፤ ያገባናል እንዲሉ አሳስባለሁ። “እኔም ኦሮሞ ነኝ” ለማለት ከቻልን፤ እኔ እችላለሁ፤ “እኔም ጎንደሬ፤ ወሎየ፤ ጎጃሜ፤ አፋሬ ነኝ” ለማለት እንዴት አንደፍርም? ፍትህ የጋራ ነው፤ የግል አይደለም።

ይህን ስል አሁንም የምመካበት የሕዝቡን ትግልና እምቢተኛነት ነው። ሕዝብ ለራሱ ህይወት ካልታገለ ሌሎቻችን የምናደርገው ትችት የትም አይደርስም። በተደጋጋሚ የማሳሰበው እውነተኛው ታሪክ ከሕዝብ ጋር እንጅ ከህወሓትና ከተመሳሳይ ድርጅቶችና ግለሰቦች ጋር አይደለም የሚለውን ነው። ታሪክ እንዲመዘግበው የምመኘው እስኳል ጉዳይ ወልቃይት-ጠገዴና ሌሎች ከነዋሪዎች የተነጠቁ ለም መሬቶች ለብዙ መቶዎች አመታት በትግራይ አስተዳደር ስር ሆነው አያውቁም የሚል ነው። ወደ ኋላ ሄደን ስናይ በአጼ ዘርዓ ያቆም ዘመነ መንግሥት እነዚህ መሬቶች የትግራይ ክልል አካል ሆነው አያውቁም።

አምስት፤ **“በአጼ ዘርዓ ያዕቆብ (14ኛው ክፍለ ዘመን) ዘመንም ወልቃይት ጠገዴ በትግራይ ስር አልነበሩም”**

አጼ ዘርዓ ያዕቆብ በኢትዮጵያ ታሪክ ከተነሱ ሃያልና ሊቅ ነገስታት ውስጥ አንዱ ነበሩ:: በቀድሞ ስሙ ፈጠጋር በአሁን ስሙ ኦሮሚያ አዋሽ ወንዝ አካባቢ የተወለዱት አጼ ዘርዓ ያዕቆብ፥ የሀድያ ሲዳሞ ንጉስ ልጅ የሆነችውን እሌኒን አግብተው፥ በ37 ዓመታቸው ከነገሱ ጀምሮ በርካታ ዓበይት ስራዎችን አከናውነው አልፈዋል:: እኒሁ ንጉስ ከፍተኛ የጥበብ ፍቅር የነበራቸውና ከመሆናቸው ባሻገር፥ ራሳቸው ብዙ መጻሕፍትን ጽፈዋል:: በሳቸው ዘመንም ብዙ መጻሕፍት እንዲጻፉ ድጋፍ በመስጠታቸው አያሌ መጻሕፍት ተጽፈዋል:: ከነዚህ መጻሓፍት አንዱ በአክሱም ንቡረ ዕድ የተጻፈው ዜና አክሱም መጽሃፍ ነው:: ዜና አክሱም ከሃይማኖያትዊ ሐተታው ባለፈ ስለ 14ኛዋ ክፍለ ዘመን ኢትዮጵያ በዝርዝር ጽፎታል:: ይህ መጽሐፍ የኢትዮጵያን አጠቃላይ ወሰንና ታሪክ ብቻ ሳይሆን የክፍላተ ሀገራቱንም ድንበር ጥንቅቅ አድርጎ ዘግቦታል:: የትግራይንም ክልል በካርታና በጽሁፍ ከዚህ እንደሚከተለው ይገልጸዋል::

Chart – List of Tigrai areas on Zena Axum book

በዚህ መጽሃፍ የቀረበው መረጃ አንድና አንድ ብቻ ነው፤ “ወልቃይትና ጠገዴ በፍጹም ፣ የትግራይ አካል አንዳልነበሩ” አስምሮበታል። ዮሓንስ መኮንን Ethiopia: the land, its people , History and Culture በሚለው መጽሓፉ Page 351 በአጼ ዘርዓ ያ ዕቆብ ዘመነ መንግስት የነበረውንና በመጽሓፍ አክሱም የተተነተውን የትግራይን ካርታ እንዲህ ያቀርበዋል።

“The Book of Axum.. Shows a traditional schematic map of Tigray with its city Axum at its center surrounded by the thirteen principal provinces: Tembein, Shire, Seraye, Hamasen, Bur, Sama, Agame, Amba Senait, Geralta, enderta, Sahart and Abergele.”

በተመሳሳይ ሁኔታ በJohn R. Short የተጻፈው The World through Maps: A History of Cartography የዓለም ጂኦግራፊን (ገጽ 352) መጽሓፍ በ15ኛው ክፍለ ዘመን የነበሩ የትግራይ ግዛቶች ከላይ የተጠቀሱት መሆናቸውን መጽሃፉ አክሱምን በመጥቀስ ያስረዳል… የሚነግረን፣ ወልቃይትና ጠገዴ በፍጹም የትግራይ አካል አንዳልነበሩ ነው።” ከላይ እንዳሳየሁት፤ በቅርቡ ጉዳዩን በሚመለከት ክቡር ራስ መንገሻ ስዩም ተጠይቀው በማያሻማ ደረጃ “የትግራይ ክልል ተከዜ መሆኑን” ገልጸዋል።

በአጼ ኃይለ ሥላሴና በደርግ መንግሥታት የነበረው የጎንደርና የትግራይ ክልል ድንበርና ካርታ ከላይ ከተጠቀሱት የተለየ አይደለም። ይህን አጠናክረው ካቀረቡት ደራሲዎች መካከል አንዱ ክርስቶፈር ክላፐም ነው። እንዲህ ይላል።

“The area concerned (welkait -Tsegede) separated from Tigray by impressive natural barrier of Setit Tekezze river has never been governed as part of Tigray at any period in the past, but has come under Gonder and Semein.” (Christopher Clapham: Transformation and continuity in revolutionary Ethiopia (Cambridge: Cambridge university press 1988 pp 259).

ለማጠናከር የምፈልገው አበይት ጉዳይ ችግሩ የመረጃ አለመኖር አይደለም። ችግሩ፤ መረጃን በፍጹም አልቀበልም ብሎ በኃይል ግዙፍ ለም መሬት ከጎንደሬው፤ ከወሎየውና ከጎጃሜው ሕዝብ የነጠቀውና የጎንደርን መሬት ለሱዳን መንግሥት እንደ ገጸ በረከት ያስረከበው ህወሓት ነው። በኦሮምያ የተከሰተው ሕዝባዊ አመጽ ከዚህ ከህወሓት የመሬት ነጠቃ ጋር የተያያዘ መሆኑን አይተናል።

ባጠቃላይ ሲታይ፤ የፈረንሳይ፤ የእንግሊዝ፤ የጀርመን፤ የፖርቹጋል፤ የአሜሪካና የኢትዮጵያ የታሪክ ምሁራንና ተመራማሪዎች

በማያሻማ ደረጃ የጎንደርን፤ የወሎንና ሌሎችን ዛሬ የአማራ ክልል ብሎ ህወሓት የሰየማቸውን ክፍለ ሃገራት ከትግራይ ክልል የሚለይ ድንበር በመረጃና በካርታ እየቀረጹ አስቀምጠውታል። እዚህ ላይ ለማስታወስ የምፈልገው አስኳል ጉዳይ ህወሓት የመሳሪያ ኃይል ተጠቅሞ ድንበሩን ለወጠው እንጅ ትክክለኛውን ታሪክ ተቀበለ የሚያስብል መረጃ የለም። ኢትዮጵያን በብሄርና በቋንቋ ለያይቶ በመያዙ ብቻ ህወሓት ታሪክ ሰራ፤ ታሪክ ፈጠረ፤ ታሪክን አስተካከለ የሚያስብል መረጃ የለም።
አንድ ቡድን ራሱን የበላይ አድርጎ ታሪክ ሰርቻለሁ ቢል መሬቱን የተነጠቀው ሕዝብ አዲሱን ሰው ሰራሽ ታሪክ የመቀበል ግዴታ የለበትም። ታሪክ የሰራው፤ የአገሪቱን ነጻነት፤ ዳር ድንበርና ሉዐላዊነት ያስከበረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ብቻ ነው። ታሪክ የሰሩት የኢትዮጵያን ሕዝብ አስተባብረው ለክብሩ፤ ለነጻነቱ፤ ለታሪኩ፤ ለወደፊት ጥቅሙ እንዲታገል አቅም የፈጠሩለት፤ ከሁሉም ብሄር፤ ብሄረሰብና ኃይማኖቶች የተወጣጡ የኢትዮጵያ መሪዎች ናቸው። ህወሓት ይህን የሚያኮራ የሁሉም ኢትዮጵያዊያን ታሪክ አጠፋ እንጅ ኢትዮጵያን የሚያጠናክር፤ ሕዝቧን የሚያስተባብር ታሪክ አልሰራም።

ወደፊትም ቢሆን አሁን ያለው በቋንቋና በብሄር መለያዎች የተቀየሰው የክልል አስተዳደር መቀየር አለበት፤ ለምሳሌ፤ እንደ ናይጀሪያ በጅ ኦግራፊና በሌላ መስፈርቶች ይቀየስ ቢባል በምንም የማይለወጥ ነው ተብሎ የሚታወጀው የትግራይ ክልል እንደሚሆን እገምታለሁ። ሌላውን ከፋፍሎ ትግራይን አንድ ወጥ ነው ቢባል ምን አስተያየት ይኖረናል? ለሚለው መልስ ለመስጠት አልሞክርም። አግባብም አይኖረውም።
ቁም ነገሩ፤ ህወሓቶች አሁንም የሚከተሉት የተስፋፊነት ስልት የጎንደርን፤ የወሎንና የጎጃምን ሕዝብ "በንኡስ" ብሄር በመከፋፈል ጥቅማቸውን ለማስከበር መሞከር ነው። አማራውን ከሌላው ከፋፍለው ጉዳዩ በሬፈረንደም ይታይ ይሉናል። "ወልቃይት ራስ ገዝ አስተዳደር ይኑረው" ይሉናል። የሕዝብን መብቶች አፍኖ፤ ሕዝብን በገፍ ከቀዩ አስወግዶ፤ ብዙውን ገድሎና እንዲሰወር አድሮ ሬፈረንደም ሊካሄድ አይችልም።
ህወሓቶች ልክ ኤርትራን በሬፈረንደም እንዳስገነጠሉት ሁሉ አሁንም ይህን የማጭበርበሪያ ዘዴ ይጠቀሙበታል። ይህ የመከፋፈል ስልት በሌሎችም ክልሎች ከስራ ላይ እንደዋለና ወደፊትም እንደሚውል አልጠራጠርም። የህወሓትን እድሜ ለማራዘም ሲባል አዲስ የአገር አስተዳደር ካርታም ቢቀረጽ አልደነቅም።
ለምሳሌ ኦሮምያን በመከፋፈል! የኢትዮጵያን ሕዝብ መሬት ለሱዳን በማስተላለፍ!!! በማንኛውም መስፈርት ብንገመግመው፤ የህወሓትን እድሜ ለማራዘም የማይደረግ ፈሊጥ አይኖርም ማለት ነው።

ይህን ክፍል ክፍል ለማጠቃለል
የወልቃይት-ጠገዴ ጥያቄ የሁሉም ኢትዮጵያዊያን ጥያቄ ሆኗል።
ህወሓት የኢትዮጵያን ሕዝብ በብሄር፤ በቋንቋና በዘር የከፋፈለበት ዋና ምክንያት ለራሱ የፖለቲካና የኢኮኖሚ የበላይነት እንዲጠቅመው መሆኑ በመረጃ የተደገፈ ነው። ይህ የበላይነት ለመሬት ነጠቃ፤ ለመስፋፋትና ለምዝበራ መሰረት ሆኗል።
ይህ የበላይነት መርህ ከየት መጣ? የሚለውን ጥያቄ ብዙ ባለሞያዎችና ምሁራን ተችተውታል። ይህን የከፋፍለህ ግዛው መርህ ወደ አስተዳደር የለወጠው ፋሽስቱ ጣልያን ነው። ምክንያቱ ህወሓት ከሚከተለው ከፋፋይነትና የተፈጥሮ ኃብት የበላይነት ጋር ተመሳሳይ ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ ጣሊያን የፈለገው መከፋፈል ስኬታማ እንዳይሆን መስዋት ከፍሏል። በተመሳሳይ ባለፉት 25 ዓመታት የወልቃይት ጠገዴና ሌላው የጎንደር፤ የወሎ፤ የጎጃምና የአፋር ሕዝብ የህወሓትን አፋኝና ከፋፋይ፤ ነጣቂና ግፈኛ ስርዓት ሲታገል ቆይቷል። አሁንም መስዋእት እየሆነ ነው። ይህ የመሬት ነጠቃ ከትውልድ ወደ ትውልድ ይተላለፋል የምለው ለዚህ ነው።
የመሬት ነጠቃውና መስፋፋቱ ከነጻነትና ከሰብአዊ መብቶች መከበር ጋር ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት አለው።
የነጻነትና የሰብአዊ መብት መስፈርት አንድ ካልሆነ አንድነትና በጋራ መስራት ትርጉመ ቢስ ይሆናል

• ኢትዮጵያ የጋራችን እስከሆነች ድረስ፤ እድገቱም የጋራ መሆን አለበት። በኤፎርት የተዘረፈው ኃብት ለኢትዮጵያ ሕዝብ መመለስ አለበት። እድገቱ የጋራ እንዲሆን ከተፈለገ ያለ-አግባብ የተነጠቀው ለም መሬት ለነዋሪዎቹ መመለስ አለበት።
• አብዛኛው እድገት የሚካሄደው በእርሻ ነው። በዚህ የኢኮኖሚ ክፍል ሆነ በሌላ አንዱ የበላይ ሌላው የበታች የሚሆንበት የኢኮኖሚና የማህበራዊ እድገት በምንም አያዋጣም። ዘላቂነትና ፍትሃዊነት የለውም። ህወሓት የሚከተለው የዜሮ ድምር ፖለቲካና የኢኮኖሚ እድገት ፍትህን መሰረት ያደረገ አለመሆኑን ማንኛውም ተመልካች ተችቶታል።
• የዜሮ ድምር ኢኮኖሚ የአንዱን መብት ጥሶ፤ የተፈጥሮና ሌላውን ኃብቱን መማረክ ማለት ነው። የመወዳደር፤ የማምረት፤ መሬትን በባለቤትነት ይዞ የማሻሻል፤ የመሸጥ፤ የመንቀሳቀስ እድሉ እንዳይኖረው የመንግሥት መሰናክሎችን መፍጠር ማለት ነው። ይህ ሲሆን በእድገቱ ላይ የሚያስከትለው ጫና ከባድ መሆኑን ከላይ በመረጃ አቅርቤአለሁ።
• ቀረብ ብለን የራሳችን አገር ስንመለከት፤ ኬንያ እያደገች ትሄዳለች። በህወሓት የምትዘረፈው ኢትዮጵያ እየደኸየች ትሄዳለች። ልጆቿ እንዲሰደዱ ታስገድዳለች። ጋና ነጻና ፍትሃዊ ምርጫ አካሂዳ መንግስቷን በሰላም ትለውጣለች፤ ኢትዮጵያ ልጆቿን ታስራለች፤ ትገድላለች፤ እንዲሰወሩ ታደርጋለች። ይህን የታፈነ የፖለቲካ ሁኔታና ጠባብ የኢኮኖሚ እድገት ውጤት ብዙ ድርጅቶች ተችተውታል።
• አንከታድ ያወጣውን ሰፊ ዘገባና በአሁኑ ወቅት የሚታየውን የኑሮ ቀውስ፤ የውጭ ብድር እየጨመረ መሄድ፤ የአቅርቦት ዝቅተኛነት፤ የዋጋ ግሽበት፤ የኃብት ሽሽት፤ ከድርቅ የሚከሰት የተፈጥሮ ረሃብ ስፋትና ጉዳት፤ የሶስት መቶ ሽህ ህጻናት ሞትን ወዘተርፈ ቀረብ ብሎ ማየቱ ይጠቅማል እላለሁ።

• ኢትዮጵያ የወንዞች፤ የዝናብ፤ የጥሩ አየር፤ የለም መሬት፤ ለመስኖ የሚውል የግዙፍ መሬት፤ ገና የማይታወቅ የመአድን፤ የባህል ቅርሶች፤ የታታሪ ሕዝብ ባለ ጸጋ አገር ናት።

• ሆኖም፤ ትራባለች። የምግብ ጥገኛ ናት። ይህ ተከታታይ ረሃብ ሊቀረፍ ይችል ነበር። ማነቆ የሆነባት ተፈጥሮ አይደለም። በሙስና፤ በአፈና የተበከለው ስርዓት ነው።

• ይባስ ብሎ፤ በጎንደርና በሌሎች የዐማራ ክልል ቦታዎች በገበሬው ላይ የሚደረገው እልቂት፤ የሰብል ውድመትና ሌላ እድገቱን እንደሚቀንሰው ለመገመት አስቸጋሪ አይደለም።

• ህወሓት ይህን ሲያደርግ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ተጣላ ማለት ነው። ከሕዝብ ጋር የተጣላ መንግሥት ሕዝብን ሊወክል ቀርቶ ሊያገለግል አይችልም። እንዲያውም፤ የህወሓት አፈና፤ ጭካኔና ሜና ምርት በሚሰበሰብበት ጊዜ በመካሄዱ፤ ረሃብን አስከትሏል፤ ድህነትን አባብሷል። ይህን የፈጠረው ድርቅ ሳይሆን መንግሥት ነው። "ወንዞች፤ ዝናብ፤ ለም መሬት ያለው ሕዝብ እንዴት ይራባል!! ብሎ መጠየቅ አግባብ አለው። "የኢትዮጵያ መንግሥት" ለአፈና፤ ለስለላ፤ ለመከላከያ፤ ለአቤቱታ የሚያወጣውን ግዙፍ ኃብት ለገበሬዎች አቅም ግንባታ፤ ለመስኖ፤ ለእርሻ ዘመናዊነት፤ ለአካባቢ መሻሻል ቢያውለው የኢትዮጵያ ሕዝብ አይራብም።

• ለማጠናከር፤ ተከታታይ ረሃብ የሚከሰተው ስርዓቱ የገማና ጸረ-ሕዝብ ስለሆነ ነው። መወገድ አለበት።

በነገራችን ላይ፤ ህወሓት ዘለዓለማዊ አይደለም። ያልፋል። ይጠፋል። ይከስማል። ሆኖም፤ ያጠፋል። የጎንደር፤ የጎጃም፤ የወሎ፤ የአፋርና ሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ይደማል እንጅ ዘለዓለማዊ ነው። በብሄርና በቋንቋ የከፋፈለውንና ያደከመውን ስርዓት ጥሎ በአብሮነት አገሩን ከድህነት፤ ከኋላ ቀርነትና ከጥገኝነት ሰቆቃ ነጻ እንደሚያወጣት አምናለሁ።
ህወሓቶች በጎንደር ዙሪያ ለም መሬቶች እንደ ተራ በረከትና የልደት ስጦታ ለሱዳን ሲሰጡ፤ በህወሓት ሲነጠቁና ወደ ትግራይ ሲዛወሩ ሕዝቡ ያለው ምርጫ ምን ይሆናል?
አንድ፤ መሬቱን በሕግና በድርድር ማስመለስ፤
ሁለት፤ ይህ የማይሳካ ከሆነ ራሱ መስዋእት ከፍሎ፤ የፈለገውን ጊዜም ቢወስድ ሙብቱን ማስከበር ይሆናል።
የኢህአዴግ መንግሥት ደፋርና አስተዋይ ቢሆን የሚመረጠው የመጀመሪያው መንገድ ይሆናል። ሆኖም፤ ያለፉት 25 ዓመታት የሚያስተምሩን በህወሓት የበላይነት የተያዘው መንግሥት ሕዝባዊ አማራጮችን አይቀበልም። ራሱን ስለሚጠራጠር ሕዝቡን አብሮ ይጠራጠረዋል። "እኔ ከሞትኩ ስርዶ አይብቀል" የሚል ይመስላል።

ሁለተኛው አማራጭ ለምን ያስፈልጋል?
ጥያቄው የህልውና ስለሆነ ነው። ይኼ እኔ የፈጠርኩት ወይንም የምመኘው አይደለም። ሕዝቡና ታዛቢዎች የሚሉት ነው። ወጣቱ በገፍ የሚታገልበትና የሚሞትበት ነው።
ለማጠናከር፤ የመሬት ባለቤትነትና ህልውና የተያያዙ ሆነዋል። አንዱን ከሌላው ለመለየት አይቻልም። ነዋሪዎች ይሰደዱ ወይንም በገፍ ይጨፍጨፉ የሚል ኢትዮጵያዊ የሚኖር አይመስለኝም። ይህን የሚል ካለ የህወሓትን የዐማራ ብሄር ማጥፋት ዘመቻ ይደግፋል ማለት ነው። በአኟኩ፤ በኮንሶውን፤ በኦጋዴን ሶማሌው፤ በኦሮሞውና በሌላው ላይ በተከታታይ የሚደርሰውን የህወሓትን ጭካኔ ካወገዝን በዐማራው ላይ የሚያካሂደውንም ጭካኔ ማውገዝ አግባብ አለው። ይህ የህሊና ጥያቄ ነው። ከምሁራን የሚጠበቅ የኢትዮጵያዊነት መለያችን ጥያቄ ነው። ማንኛውም ግለሰብና ስብስብ ይህን አገር የሚያጠፋ፤ እልቂት የሚያስከትል ችግር በድርድርና በሕግ እንዲፈታ ጥረት ማድረግ አለበት። ይህ አማራጭ ስኬታማ ካልሆነ ሊከተል የሚችለውን እልቂት ለመገመት አስቸጋሪ አይደለም።

ተመልካቾች የሚሉት ህወሓት ድርድር የሚባል ነገር አያውቅም ነው። ይህ በቂ ምክንያት አይደለም። ሕዝብ እየሞተ ድርድር አልፈልግም ካለ የሕዝቡን ትግል መደገፍ አግባብ አለው። ህወሓት ድርድር ካልፈለገ ለሰላምና ለእርቅ የተደረገውን ጥረት ሁሉ ለኢትዮጵያና ለዓለም ሕዝብ ማቅረብ ግዴታችን ነው። በዚህ አጋጣሚ አንባቢውን አደራ የምለው የአሜሪካ ምክር ቤት ስለ ኢትዮጵያ ያረቀቀውን "የሰብአዊ ሙብት መከበርና ሁሉን አሳታፊ የሆነ አገዛዝ አስፈላጊነት" የቀረበውን፤ "H.R. 28" 36 መደገፍ ነው። ሕዝቡን ለሰብአዊ ሙብቱ የሚያደርገውን ትግል መደገፍ የእያንዳዳችን ታሪካዊ ግዴታ ሆኗል። ይህን ለማድረግ መተባበርና በአንድ ድምጽ መናገር ወሳኝ ነው።

• የጎንደር፤ የወሎና ሌላው የዐማራና የሌላ ብሄር ሕዝብ ከትግራይ ሕዝብ ጋር ቅራኔ የለውም። ቅራኔውን የፈጠረው ህወሓት ነው፤ ሕዝቡ አይደለም። የትግራይ ሕዝብ በራሱ ስም ጥላቻን የፈጠሩለትን መምከር ግዴታው ነው። እኔ እስከማውቀው ድረስ፤ ሕዝቡ ተጋብቷል፤ ተዋልዷል፤ ተጎራብቷል። የማይካደው ሃቅ፤ በክፉም ሆነ በደጉ ወቅት፤ የጎንደርና ሌላው የዐማራ ሕዝብ ከትግራይ ሕዝብ ጋር የጠነከረ የመደጋገፍ ግንኙነት ታሪክ አለው።

• ስለሆነም፤ በዘላቂነት ስመለከተው፤ የሚያዋጣው የፖሊሲ አቅጣጫ ይህን የወንድማማችነት፤ የእህትማማችነት ታሪክ ማጠናከር የእያንዳንዳችን ታሪካዊ ግዴት ነው። ይህ የሁላችንም ምኞትና ጥረት መሆን አለበት። መነሻው መሆን ያለበት የህወሓት አመራር የብሄር ጥላቻ መርዝ እያስተጋባ ይህን ታሪካዊ ግንኙነት መበከሉ፤ አሁንም ማባባሱ፤ ወደፊትም አደጋው እየሰፋ መሄዱ ነው።

• በእኔ ግምት ለትግራይ፤ ለዐማራ፤ ለኦሮሞ፤ ለደቡብ፤ ለአኟክና ለሌላው ሕዝብ ተቆርቋሪ የሆነ ግለሰብና ስብስብ ማንኛውንም የብሄር ሆነ ሌላ ጥላቻና አድልዎ ማስወገድ ያለበት አሁን ነው። ማንኛውም ለፍትህ የቆመ ግለሰብ ወይንም ስብስብ መጀመሪያ ራሱን መለወጥ አለበት። ራሱን ከብሄር ጥላቻ ወጥመድ ሰብሮ መውጣት አለበት። እኛ በአሁኑ የዓለም ትሥስር ዘመን "የፓሌስታይንና የኢስራኤል" የእርስ በርስ እልቂት ሁኔታዎች እንዳይፈጠሩ ካላደረግን በታሪክ መወቀሳችን የማይቀር ነው።

• ራስን መለወጥ ማለት በቅንነት በተሞላ መንፈስ ለአንድ አገር! ለአንድ ሕዝብ! ማሰብና ተባብሮ መስራት ማለቴ ነው። ሁኔታው ጊዜ አይሰጥም። አገሪቱ የጦር አውድማ ከመሷ በፊት እንመካከር፤ እንተባበር! የትግራይ ሕዝብ ከአጭር ጊዜ ጥቅሙ ባሻገር ህወሓት

በዐማራው ሕዝብ ላይ ብቻ ሳይሆን በሌሎች ሕዝቦችም ላይ የሚያካሄደውን ጭካኔና ግፍ የሚያወግዝበት ቀን አሁን ነው። ህወሓትን እቃወማለሁ ማለት በቂ አይደለም። ዋናው የመቃወም አላማውና የመጨረሻ ግቡ ምን ይሆናል የሚለውን መመለስ ነው። ህወሓት የሚለፈልፈውን የጥላቻ ፕሮፓጋንዳ ማውገዝ አግባብ አለው፤ ጊዜው ነው።

ልዩነቶችን በጨዋነት ማስተናገድ አስፈላጊ ሆኗል በህወሓት የመሬት ነጠቃና የመስፋፋት ሂደት በሚመለከት የሃሳብና የፖሊሲ ልዩነቶች መኖራቸው ነውር አይደለም። ነውሩ የችግሩን ጥልቀትና ስፋት አለማወቅና ካወቁም ንቆ መተው ወይንም አድርባይ መሆኑ ነው። በጨዋነት፤ በመደማመጥና በመከባበር በፖሊሲዎች ላይ ለመነጋገርና ለመደራደር አለመቻል ኋላ ቀርነትና አድር-ባይነት ነው። ኋላ ቀርነት የህወሓት ርእዮት ነው፤ ከጠባብ ብሄርተኝነትና ጎጠኝነት ጋር የተያያዘ ነው! በአንድ አገር አብሮ ለመስራት መደማመጥና መቻቻል መሰረት ነው። መከባበር መሰረት ነው። እውነተኛ ታሪክን መቀበል ግዴታችን ነው። የብሄርና ሌላ ልዩነት ካለ ያንን ልዩነት በመረጃ አቅርቦ መነጋገር አስፈላጊ ነው። እንዲሁ የህወሓትን አጀንዳ ተቀብሎ ሌላውን መዝለፍ ከወገንተኛነት አይለይም። እኛ ለመላው ሕዝብ ደህንነትና የኑሮ መሻሻል ለመነጋገር ካልቻልን ይህን የህወሓት ጠባብ ብሄርተኛ ቡድን ከመቀበል ምን ይለየናል?
በወልቃይት ጠገዴ ምክንያት የሚካሄደው የዐማራ ተጋድሎ እኔን ብቻ የሚመለከት አይመስለኝም: ፡ ሆኖም በኢትዮጵያዊነቴ የምኮራና የማምን ብሆንም የወልቃይት ጉዳይ እኔንም ያገባኛል የሚል እምነት ስላለኝ ይህን የአቋም ትንተና አቅርቤአለሁ። የካያምነውን የማሳመን ግዴታ የለብኝም። ለተቆርቋሪ ኢትዮጵያዊያን ግን ግዴታ አለብኝ፤ ለኢትዮጵያን ለመላው ሕዝቧ ግዴታ አለብኝ--ያለችኝን በቅንነት ማበርከት!!
በተመሳሳይ፤ በጋምቤላ፤ በኦሞ ሸለቆ፤ በአፋር፤ በደቡብ፤ በቤኒ-ሻንጉል ጉሙዝ፤ በኦሮምያና በሌሎች ክልሎች የተካኤደውና የሚካሄደው የመሬት ነጠቃና አፈና እኔንም እንደሚያገባኝና እንደሚያሳስበኝ በመጽሃፍቶች ላይ አሳስቤአለሁ።
እኔ የታዘብኩት ግን የወልቃይትን ጥያቄ በሚመለከት ተቃዋሚዎች፤ ልሂቃንና ምሁራን መደበቃቸው፤ ድምጽ ለማሰማት አለመድፈራቸው ለምን ይሆን? ብየ ስጠይቅ አጥጋቢ መልስ አላገኘሁም። ምሁራን፤ ልሂቃን፤ ህብረ-ብሄርና ሌሎች የፖለቲካና የማህበረሰብ ድርጅቶች በዚህ ጉዳይ ላይ ሚዛናዊ አቋም መውሰድ አለባቸው የሚል እምነት አለኝ። ይህን እምነቴን የሚያጠናክረው በመሬት ላይ የሚካሄደው አሰቃቂ እልቂት መሆኑን በዚህ ጥናት አሳይቻለሁ።

ይህን አሰቃቂ ክስተት መሰረት ያደረገው በህወሓት ተጸንሶ በዐማራው ላይ የተካሄደው የብሄር ጥላቻ ነው። “ህዝባዊ ሓርነት ትግራይ አማራዎች ከድሮ ጀምሮ የትግራይ ሕዝብ ጠላቶች ናቸው። እነዚህ አህዮች ከአገራችን ይውጡ፤ ትግራይ የራሳችን ነጻ አገር ነች....” (የህወሓት ታጋይ ጋህዲ፤ ቁጥር 2 ከትግርኛው የተቀዳ ገጽ 162). ይህ ብቻ አይደለም። አባባሉ ይዘገንናል፤ ዐማራውን አህያ ብሎ መሳደብ በጠላትነት የተፈረጀውን ሕዝብ ሰብእነት ገፎታል ለማለት ይቻላል። በኢትዮጵያ ታሪክ ከአንድ ላይ የኖረውን፤ ለኢትዮጵያ የ3,000 ዓመታት የነጻነትና የስልጣኔ ታሪክ ኬሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ተባብሮ መስዋእት ሆኖ ያቆያትን የትግራይን ሕዝብ ከሌላው አገር ወዳድና ጀግና የኢትዮጵያ ሕዝብ፤ በተለይ ጎረቤት ከሆነው ከሰሜኑ የዐማራ ሕዝብ በሚለያይ ሁኔታ እንዲህ የሚል መርህ ተከትሎ ቆይቷል። “ህወሓት ነጻ የሆነች የትግራይ ሪፑብሊክ ለመመስረት ነው ዋናው የትግላችን ዓላማ” (ጋህዲ ቁጥር 2, 2001) ከትግርኛው የተቀዳ። አከራካሪው ጉዳይ “የመገንጠል ዓላማ” አለኝ ማለቱ ብቻ አይደለም።
ህወሓት ለመገንጠል ባለው አላማ ሲፎክር ቆይቷል። የመገንጠል መብት የሌላውን ሕዝብ መሬት ማጠቃለል፤ የአገሪቱን ንብረት መዝረፍ ሊሆን አይችልም። በጥያቄ መልክ ላቅርበው። ሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ለመገንጠል ከፈለግህ መጀመሪያ የነጠቅኸውን ለም መሬት መልስ! የዘረፍከውን ኃብት ለኢትዮጵያ ሕዝብ መልስ! ቢል ምን መልስ ይሰጠዋል? የሚሰጠው መልስ “መሬትክንም ሆነ የተዘረፈውን ኃብት በመሳሪያ ኃይል ትነጥቀዋለህ እንጅ ፈቅደን አንሰጥህም” እንደሚሆን አልጠራጠርም። ይህ “እገነጠላለሁ እና አስገነጥላለሁ” የሚል የማስፈራሪያ በትር በተደጋጋሚ ሲነገር ቆይቷል።

ዋናው ምክንያት ህወሓት ጠንካራ ስለሆነ አይደለም። እኛ ህወሓት ሆን ብሎ በፈጠረልን የብሄር ልዩነቶች ስለተከፋፈልን ነው። መሬቱና ኃብቱ የተዘረፈው ሕዝብ ማስፈራሪያውን አልፎ በራሱ ጥበብና ስልት መብቱን ለማስከበር እየሞከረ ነው። የህወሓት የነጻነት ዓላማ ስኬታም ሊሆን የሚችለው የተጎዳው ሕዝብ በፍርሃት ዓለም ከኖረ ብቻ መሆኑን በሌሎች አገሮች ታሪክም ጭምር አይተናል። ህወሓት ከሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብ አግባብ በሌለው መልክ ለም መሬቶችን ነጥቆ የህወሓት ኃብት አድርጌ በሰላም እኖራለሁ ማለት እልቂትን መጋበዝ መሆኑን በመሬት ላይ እያየን ነው።
እኔ ትግራይ የኢትዮጵያ አካል መሆኗን አምናለሁ። ይህ እምነት የሚጠይቀው ወሳኝ የፖሊሲ ለውጥ ነው። ማለትም፤ የህወሓት የመሬት ነጠቃና ትግራይን የማስፋፋት መርህ መለወጥን ይጠይቃል። የተዘረፈው ኃብት እንዲመለስ ይጠይቃል። ነጻነት እንዲከበር ይጠይቃል። የታሰሩት የፖለቲካ እስረኞች እንዲፈቱ ይጠይቃል። የአስቸኳዩ አዋጅ እንዲነሳ ይጠይቃል። ህወሓት ጭፍንና ኋላ ቀር ስለሆነ እነዚህን አያሟላም። ስለማያሟላ፤ ኢትዮጵያ የመፈራረስ እድሏ ከፍ ያለ ይሆናል የሚሉ አሉ። ይህ አደጋ ከተከሰተ ግን፤ የሚጎዳው ሁሉም የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው፤ ትግራይንም ጨምሮ!
የወልቃይት ጠገዴ የማንነትና የመሬት ባለቤትነት መሰረታዊው ችግር መንስኤ የህወሓት የመሬት ነጠቃና የትግራይ ክልል መስፋፋት ውጤት ነው። መሬት ነጠቃ ምዝበራ ነው። መሬት ነጠቃ የፖለቲካ ሙስና ወይንም ሌብነት ነው። እዚህ ላይ አንባቢውን የማሳስበው ተጨማሪ ሃሳብ አለኝ። ይኼውም፤ የወልቃይት ጠገዴ ጥያቄ የማንነት ጥያቄ ብቻ አይደለም። መሰረታዊ የሆነ የህልውና ጥያቄም ጭምር ነው። ለምን?
ህወሓት በነዋሪው ላይ የጅምላ ጭፍጨፋ እያካሄደበት ነው። ወረራውና ጭፍጨፋው የጣሊያን ጦር እንኳን ያልተፈጸመበት የዘር ማጥፋት ዘመቻ (Ethnic cleansing and genocide) እየተፈጸመበት ይገኛል። ይህ በወንጀለኛነት ያስከሥሳል፤ ያስጠይቃል። ኢትዮጵያዊው ጎንደሬ፤ ወልቃይቴ የማንነት ችግር የለበትም። ከላይ በተደጋጋሚ እንደገለጽኩት፤ ኖሮትም አያውቅም።
ጎንደሬነትና ኢትዮጵያዊነት ተደጋጋፊ መሆናቸውን ተቀብሎ ለአገሩ መስዋእት የከፈለ፤ ድንበሩን አስከብሮ የቆየ ሕዝብ ነው። ዛሬ

ከፊቱ ላይ የተደቀነበት ወይን የተነጻጸረበት አደጋ ግን የሞት-ሽረት አደጋና ትግል ነው።

ስለሆነም፤ ሌላው ኢትዮጵያዊ ወገኑ ሁሉ ሊደርስለት የገባል!!!! ካልደረሰለት ግን ነገ በራሱ ላይም ግፍና በደል ይደርስበታል። የዐማራው ተጋድሎ መሰረትም ይኼው ነው። ይህ ሕዝባዊ ትግል አይቆምም የምልበትም ምክንያት ይኼው ነው።
ከታች በግርጌው አባሪ ሆነው የቀረቡት ካርታዎች እንደሚያሳዩት ህወሓት ዓላማውን ስኬታማ ለማድረግ በወሎው፤ በጎንደሩና በጎጃሜው ዐማራ ላይ ከፍተኛ ጥቃት አካሂዷል፤ እያካሄደ ነው። ዛሬ የገበሬዎችን ቤቶች፤ መንደሮችንና ሰብልን በከባድና በቀላል መሳሪያ እያቃጠለ ሕዝቡን ወደ የባሰ ችግር ያዛወረው ይኼው ቡድን ነው። የዐማራው ሕዝብ የማንንም መሬት ልንጠቅ አላለም፤ አይልም። "መኖሪያየ፤ ማንነቴ ይከበር" ብሎ የተነሳ ሕዝብ ነው። ህወሓት የትግራይን ድንበር ለጥጦና አስፋፍቶ የዐማራውን ክልል ድንበር አጥብቦታል። በማበህበረሰባዊና ኢኮኖሚያዊ መስፈርቶች ሲታይ፤ ህወሓት የአማራውን ጉረሮ አንቆታል ያልኩት ለዚህ ነው።
ይህ ሲሆን "በጠላትነት" የተፈረጀው የዐማራ ብሄር ለም መሬት፤
ወንዞች፤ ተራራዎችና ሌሎች የተፈጥሮ ኃብቶች እና ዳር ድንበር ታይቶ በማይታወቅ ደረጃ ተለውጦ አንገቱ በኢኮኖሚ ማእቀብ ውጥረትና ሰንሰለት ታስሯል።
(The TPLF has effectively managed to strangulate the economic life and viability of the Amhara region). ያለው አማራጭ ስደት፤ እስራት፤ መገደል፤ እንዲሰወሩ መገደድ፤ "አህያ ነህ" ቢባልም ሰጥ ለጥ ብሎ መገዛት ወይንም "ለህልውናየ መታገል አለብኝ" ብሎ ቆርጦና ደፍሮ መነሳት ነው። ሕዝቡ ወስኖ የሚታገለውና መስዋእት የሚሆነው ለመጨረሻው መሆኑን በመሬት ላይ አየየን ነው።
ሆኖም፤ ይህ እንቅስቃሴ ከሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል ጋር መቆራኘት አለበት እላለሁ። መታወቅ ያለበት አበይት ሃቅ አለ። ይኼውም፤ የወልቃይት ጠገዴ ዐማራና ሌላ ሕዝብ ችግሩን በሕገ መንግሥቱ አመራር መሰረት ሊፈታ ሞክሮ አልተቻለም። እንዲያውም አማላጆቹ ታስረዋል ወይንም ተሰደዋል፤ የተገደሉም አሉ። ከችግሮቹ መካከል አንዱ፤ ህወሓት በፖለቲካ ድርድር፤ በሰላምና በእርቅ አለማመኑ ነው።
እኔ እስከማውቀው ድረስ፤ ጎንደሬውና ሌላው ዐማራ ቆርጦ የተነሳባቸው ሰብሳቢ ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው፤
አንድ፤ ራሱን ከእልቂት ለማዳን (የህልውና ጥያቄ የሚባለው) ፤
ሁለት፤ ራሱን ከእልቂትና ከስደት አድኖ ኢትዮጵያን ከሌሎች ኢትዮጵያዊያን ጋር ተባብሮ ከመፈራረስ ለማዳን፤
ሶስት፤ ሰብአዊ መብቶቹን ለማስከበር፤ ይህን ለማድረግ ለህልውናው መሰረት የሆኑትን መሬቶቹን ባለቤትነት ለማረጋገጥ፤ ለማስመለስ፤
አራት፤ በኢትዮጵያ የወደፊት እድል ሙሉ ተሳታፊ ለመሆን፤ ለህወሓት/ኦነግ/ሻቢያ ስልጣን ያስተላለፈው የለንደኑ አይነት ዝግ የፖለቲካ ድርድር እንዳይካሄድ ለመከላል፤
አምስት፤ ጠባብ ብሄርተኝነትን አስወግዶ እውነተኛ ዲሞክራሳዊት ኢትዮጵያን ለመመስረት ለሚደረገው ትግል አስተዋፆ ለማድረግና፤
ስድስት፤ በውጭ ግንኙነት ዙሪያ ከሰፈው የዐማራ ሕዝብ ጋር ብቻ ሳይሆን ከሌሎች ኢትዮጵያዊያን ጋር ተባብሮ አጥፊውን ስርዓት ለማጋለጥ፤ የዐለም ሕዝብ አገሪቱ የደረሰችበትን አደጋ ተገንዝቦ ለአምባበነኑ መንግሥት የሚለግሰውን እርዳታ እንዲያቆም ለማድረግ ነው።

ጎንደሬው ጠባብ አይደለም
ጎንደሪውና ሌላው የዐማራ ሕዝብ "የኦሮሞው ሕዝብ (የወንድሞቻችን) ደም ደማችን ነው" የሚል የማያሻማ ኢትዮጵያዊነት ድምጽ አሰምቷል። የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዐላማ "ሰንደቅ ዓላማችን ነው" ብሏል፤ የኢትዮጵያ ሉዐላዊነት እንደሚመለከተው ተናግሯል።
ጎንደሬውን የሚደነቅ ሕዝብ ያደረገውም በኢትዮጵያዊነቱ ከፍተኛ እምነት ያለው መሆኑና ለመብቱ ቆርጦ መነሳቱ ነው። ጎንደሬው፤ ወሎየው፤ ጎጃሜውና ሌላው አማራ ከኢትዮጵያ ውጭ አገር አያውቅም፤ አገር አይፈልግም፤ ሌላ አገር አይመኝም። ራሱም የበላይ የመሆን ምኞት የለውም። ቆርጦ የተነሳው አግባብ ላለው ለመብቱ፤ ለማንነቱ፤ ለክብሩ፤ ለነጻነቱ፤ ለህይወቱ ለሚመካበት ለመሬቱ፤ ለሃገሩ፤ ለዳር-ድንበሩ ነው። የወገኖች መብትና ነጻነት እኔንም ያገባኛል የሚል ሕዝብ መሆኑን ደጋግሞ አስመስክሯል።
በእኔ ግምት፤ በዐማውራና በኦሮሞው፤ በአፏኩና በኮንሶው፤ በኦጋዴን ሶማሌውና በአፋሩ ወዘተርፈ የሚካሄደው እልቂት ካልቆመ ነጻነትና የዲሞክራሲ ስርዓት አይታሰብም። የኢትዮጵያ የመፈራረስ እድል ከፍ ይላል። ዐማራው ራሱን ከእልቂት ካላዳነ፤ ዲሞክራሲም ሆነ ኢትዮጵያ የምትባል አገር አስተማማኝ አይሆኑም። ሰላም፤ እርጋታ፤ የህይወት ዋስትና፤ እድገት
አይታሰብም። ለጊዜው ይመስላል!! የአስቸኳዩ አዋጅ ሁኔታውን አብርዶታል እንጅ መሰረታዊዎቹ ችግሮት እንዳሉ ናቸው። ሕዝብ ለመብቱና ለነጻነቱ መነሳቱ አይቀርም የሚል እምነት አለኝ።
ህወሓት ሰብአዊ መብቶችን እየገፈፈ፤ መሬት እየነጠቀ ወዘተርፈ የተሃድሶ ግድብን እሰራለሁ ብሎ የኢትዮጵያን ሕዝብ ካለህ ደሞዝ ወይንም ገቢ አዋጣ ሲል የሚሰራው ግድብ ለማን ነው? የሚለው ጥያቄ አለመተማመንንና ጥርጣሬን ያመጣው ይኼው የህወሓት የመስፋፋትና የመገንጠል ዐላማና ከዚህ ባሻገር በዘላቂነት ያቀደው የመገንጠል ዓላማ በይፋ ባይነገርም ግልጽ መሆኑ ነው። የተሃድሶ ግድብ ኢትዮጵያ ውስጥና የኢትዮጵያ ሕዝብ ኃብት ነው። የዚህ ግድብ ዘላቂ ደህንነት የመላው ኢትዮጵያዊያንን ተሳትፎ እና የሁሉንም ኢትዮጵያዊያንን ጥቅም መከበር ይጠይቃል። የዚህም ግድብ ጥቅም እንደሌላው በህወሓት ከተማረከ እድሜው አስተማማኝ የሚሆን አይመስለኝም።

ህወሓት የኢትዮጵያን ዘላቂ ጥቅም አላስከበረም፤ አያስከብርም

እኔ ኢትዮጵያ ወንዞቿን በሙሉ ተጠቅማ ድህነትን እንድትቀረፋ እመኛለሁ። እፈልጋለሁ። እስከ ህይወቴ መጨረሻ ድረስ ለዚህች ታላቅ ለመሆን ለምትችል አገር እታገላለሁ። ጠበቃ ሆኘ አገለግላለሁ። በዚህች አገር አልነግድም፤ ለድርድር እንድትቀርብ አልፈቅድም። የሕዝቧም ሰብአዊ መብትና ነጻነት ለግል ወይንም ለቡድን ጥቅም እንዲነገድበት አልፈቅድም፤ እከራከራለሁ። ይኼ ዛሬ የጀመርኩት አይደለም። በሶስት ተከታታይ መንግሥታት ስሚገትበት ቆይቻለሁ!!!

ኢትዮጵያ የዐባይንና ሌሎች ግድቦችን የመስራትና የመስኖ እርሻዋን የማስፋፋት ሙሉ መብት አላት። በዶሃ፤ ካታር የተከራከርኩት ይህን አቋም ይዤ ነው። ሆኖም፤ ይህ ትርጉም የሚኖረው የነዋሪዎቹና የመላው ኢትዮጵያ ሕዝብ ነጻነት፤ ሰብአዊ መብት፤ የኢኮኖሚና ሌላ ጥቅም ሲከበር ብቻ ነው። የተሃድሶ ግድብ አስዋን አይደለም፤ ያለው ኢትዮጵያ ውስጥ ነው። ተጠቃሚው መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ፤ በተለይ ነዋሪው መሆን አለበት። ኢትዮጵያ የተፈጥሮ ኃብቷን በሙሉ የመጠቀም መብት እንዳለ ሆኖ፤ ቀስ በቀስ ይህም ለኢትዮጵያ ይጠቅማል ተብሎ የታሰበ ግድብ አስተማማኝ ወደ አልሆነ ሁኔታ እየተለወጠ ነው። ህወሓት አገሪቱን ከማጋለጥ አያርፍም።

ለምሳሌ፤ በህዳሴው ግድብ የተሰማሩ የዐማራና የኦሮሞ ሰራተኞች በጥርጣሬ ታስረዋል፤ ከስራቸው ተባረዋል። ያባረራቸው ህወሓት ነው። ይህ የሚደረገው በማን ስምና ለማን ጥቅም እንደሆነ ኢትዮጵያዊያን ያውቁታል። ህወሓት ለሕዝብ ተገዢ ስላልሆነ በማንኛውም ማህበረሰባዊ ኑሮ የፈለገውን ያደርጋል። የፖለቲካ ስልጣን አስክሮታል!! ህወሓት "አውራ ፓርቲ" ስለሆንኩ አውራ ወይንም ታላቅ ክልል ይገባኛል የሚል አመለካከት እንዳለው በዚህ ትንተና አሳይቻለሁ።

*ታላቋ ትግራይ ምን ማለት ነው?*

ከታች ህወሓት ራሱ ያወጣውን ሰነድ (ማኒፌስቶ) ደጋግመን ብንመረምር፤ "ታላቋ ትግራይ" የሚለው ጉዳቱ ከፍተኛ ባይሆን ኖሮ አከራካሪ ባልሆነም ነበር። የአገር ውስጥ የመሬት ነጠቃና መስፋፋት "የታላቋ ትግራይ" መሰረት ነው፤ የለም ለማለት መሬት አልተነጠቀም ከማለት አይለይም። ልክ ታላቋ ብሪታኒያ ሌሎችን አጠቃልላ ራሷን "ታላቅ" እንዳለችውና ሶማሌያ የኢትዮጵያንና የኬንያን ድንበሮች አልፋ የሶማልኛ ተናጋሪው የሚኖርበትን ሁሉ "የታላቋ ሶማሊያ" አካል ነው ብላ በተደጋጋሚ ወደ ጦርነት እንዳመራችው ሁሉ፤ ህወሓት ያደረገውና የሚያደርገውም ተመሳሳይ ነው። ታላቋን ሶማሊያን እመሰርታለሁ ያለችው ሶማሊያ ተበታትናለች፤ ፈርሳለች። ለማጠናከር የምፈልገው የመሬት መስፋፋት ግጭት ፈጥሯል፤ ግጭቱ የሚያቆም አይመስለኝም። ታላቅ የሆነው ታናሽ ሊሆን ይችላል!

አንድ ክልል የሌሎችን ክልሎች ለም መሬት የእኔ ነው ብሎ ሲያጠቃልል ታላቅ መሆኑ አይቀርም። በተጻራሪው መሬቱ የተነጠቀበት ሕዝብ መሬት ጠባብ ይሆናል ብሎ ለመከራከርና አቋም ለመውሰድ፤ የሮኬት ሳይንቲስት መሆንን ወይንም በፖለቲካ ምርምርና ጥናት የዶክተሬት ማእረግ መቀበልን አይጠይቅም። መሬቱ የተወሰደበት ነዋሪ ዋናውና ወሳኙ መስካሪ መሆን አለበት። ነዋሪው ይወገዳል፤ ይጎዳል፤ ሰፋሪዎች ይተኩታል፤ ለተሰፋሪዎቹ የኃይል ዋስትና ይሰጣቸዋል። ነዋሪው ቅድመ አያቶቹ የሰጡትን መሬት አጥቶ ይደኸያል፤ ይሰደዳል፤ ይሞታል፤ ይታሰራል። የባሰውን ብሎ፤ የህወሓትን የመሬት መስፋፋትና የትግራይ ድንበር ጎንደርን አልፎ ወደ ቤኒ ሻንጉል ጉሙዝ ወሰን ሲሸጋገር የሕዳሴ ግድቡ የማን ይሆናል፤ ማንን ይጠቅማል፤ ማንን ይጎዳል፤ ለማን የበላይነት መሳሪያ ይሆንል፤ የውሃ ኃይሉን ለውጭ ገበያ አቅርቦ ማን የውጭ ምንዛሬ ባለሃብት ይሆናል? የሚሉት ጥያቄዎች ሁሉ ሊታሰብባቸው ይገባል። አሁንም ቢሆን ጨዋታው የዜሮ ድምር እድገት ይሆናል። አንዱ ተጠቃሚ ሌላው ተመልካች ሆኖ ሰላም አይታሰብም።

በማንኛውም መስፈርት ሲታይ፤ የዐማራው ሕዝብ ተጠቃሚ እንደማይሆን ለመገመት አያዳግትም። እንዲያውም፤ ባለፉት ሃያ አምስት አመታት የዐማራው ሕዝብ ለባሰ ድህነትና ስደት ተጋልጧል። የአለጀዚራ ሰፊ ዘገባ የዐማራው ሕዝብ ከሌላው የኢትዮጵያና የዐለም ሕዝብ ድሃ፤ በሽተኛ፤ ችግረኛ መሆኑን አስምሮበታል። የማይካደው ክስተት፤ ችግሩ የሞት-ሽረት ሆኗል። የህወሓት የመስፋፋት ሴራና ያስከተለው ማህበረሰባዊ፤ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ቀውስ ነዋሪውን ሕዝብ እያመሰውና እያስጨነቀው ነው። ጭካኔውና በደሉ፤ ወጣቱን የጎንደርንና የሌሎች የዓማራ ክልል አካላት ትውልድን ከመቸውም ጊዜ በበለጠ እያንቀሳቀሰው ነው።

የወልቃይት ጥያቄ የመላው ኢትዮጵያ ጥያቄ ሆኗል

ዛሬ አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ የወልቃይት ጠገዴ ጥያቄ መመለስ አለበት፤ የነዋሪው ሕዝብ ዲሞክራሳዊ መብት ነው የሚለው ለዚህ ነው። ጎንደር፤ ጎጃምና ወሎ የህወሓት ኮማንድ ፖስት ምሽግ ሆኖ ብዙ ወጣት፤ እናት፤ አባት፤ ሽማግሌ የሚሞተው ለክብሩ፤ ለመብቱ፤ ለነጻነቱ፤ ለህይወቱ ነው። አሁን በሚካሄደው የህወሓት አጥቂነት ቤቶችና መንደሮች እየተቃጠሉ ነው፤ እንስሳዎች እየተገደሉ ነው፤ አስመራው እየተቃጠለ ነው። ይህ ዓለም እንዳያውቀው በአፈና የተያዘ ግፍ የሚካሄደው መገናኛ ብዙሃን ፍጹም በሆነ ደረጃ ተከልክሎ ምስክር እንዳይኖር ፍጹም በሆነ በጨለመ ሁኔታ ነው። የአሜሪካ ኤምባሲ ዜጎቹን ወደ ሰሜን ጎንደር እንዳሄዱ የከለከለበት ዋና ምክንያት ሁኔታው ከቁጥጥር ውጭ በመውጣቱ ነው። ህወሓት ጥቃቱን በማስፋፋት መሬት ቆርሶ ከሰጠው ከሰሜን ሱዳን ጋር ተባብሮ የኢትዮጵያን ሕዝብ ይወራል፤ ያሰቃያል። ይህ አሳፋሪ ጦርነት ማንን ለማጥቃት እንደሆነ ግልጽ ነው፤ የጎንደርን ሕዝብ!! የአማራውን ብሄር!!

ሁላችንም ማጤን ያለብን በአሁኑ ወቅት ብዙ የዐማራ ተተኪ ትውልድ እየሞተ፤ እየታሰረ፤ እየተሰደደና እየተሰወረ፤ እየታገለ መሆኑን ነው። በገፍ የሚታገለውና የሚሞተው ጎንደሬው ነው። ገበሬው ነው። ይህ መሬቱና መብቱ የተገፈፈ ሕዝብ ከዚህ የባሰ ሊመጣ አይችልም እያለ ነው። ይህ ትግል የሚያካሂደው በማንም የውጭ ኃይል ድጋፍ አይደለም፤ ነዋሪው ሕዝብ በራሱ ጥረት፤ የሕዝብ ድጋፍ፤ ድርጅትና የጎበዞች አለቃዎች አመራር ነው። የጎበዝ አለቃ ሞቶ ሌላው እየተተካ መሆኑን መካድ አይቻልም። ይህ ሁኔታ እስከመቸ እንደሚቆይ አይታወቅም። የሚታወቀው ክስተት ግን፤ መስዋእትን ተቀብሎ ጎንደሬውና ሌላም መሬቱና መብቱ የተነጠቀው፤ በአብዛኛው የአማራ ሕዝብ ራሱን ከእልቂት ለማዳን እምቢተኛነት መጀመሩና ይህ እምቢተኛነት እየተስፋፋ መሄዱ ነው። ይህ በየአካባቢው የሚካሄድ ትግል የሚቆም አይመስለኝም።

"Amhara resistance (የዐማራ ተጋድሎ)" የሚባለው ባዶና ቀፎ አይደለም። ሕዝብ እየሞተ ነው፤ ቢያንስ ወደ 52,000 ወጣት ታስሯል፤ ብዙ ሽህ እንዲሰወር ተደርጓል። የአስቸኳይ አዋጁ ሁኔታውን አባብሶታል፤ ሃቁ እንዳይታወቅ አድርጎታል። ይህ "የተደበቀ

እልቂት” በማያሻማ ደረጃ መወገዝ አለበት። ለሕዝብ ህይወት የሚያስብ ድርጅት ሁሉ ይኼን የህወሓት ጭካኔ ማውገዝና ለዐለም ሕብረተሰብ ማስታወቅ አለበት።

ምንም እንኳን ህወሓት የአስቸኳዩን አዋጅ መሰረት አድርጎ በጎንደር፤ በጎጃምና በወሎ ሕዝብ ላይ “ጦርነት” ቢከፍትም፤ ይህ የሞት-ሽረት ትግል በምንም አይቆምም። ከላይ በማስረጃ ድጋፍ እንዳሳየሁት፤ ችግሩ የህልውና ጥያቄ ስለሆነ ነው።

## ተቃዋሚ ፓርቲዎች ምን አቋም ይወስዳሉ?

ተቃዋሚ ነን የሚሉ ድርጅቶችና ግለሰቦች ይህን ለሕዝብ እልቂት መንስኤ የሆነ የህወሓቶች የመስፋፋት ዐላማና ያስከተልውን ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍ አደጋ በሰከነ አእምሮና ጥናት ቢያዩት ይሻላል የሚል ጠንካራ እምነት አለኝ። ጉዳዩን ሊሸሹትና ሊፈሩት አይችሉም። ከላይ እንዳቀርብኩት ጉዳዩ የግል አይደለም፤ እኔን የሚያስጨንቀኝ የጎንደሬው፤ የጎጃሜው፤ የወሎየውና የሌላው ዐማራ ሕዝብ መጨፍጨፍ ነው። እኔን የሚያስጨንቀኝ የኦሮሞው፤ የአፏኩና የሌላው ሙብት መረገጥ ነው። ይህ ስለሆነ ነው አንዳንዴ “ተቃዋሚ ነን” ከሚሉ ድርጅቶች የሚነገረው አቋም የሚመስል ብሂል ከህወሓት መርህ በምንም አይለይም ብየ ትችት ለመስጠት የምገደደው። ተቃዋሚ ማለት በመሬት ላይ ያለውን አሰቃቂ ሁኔታ አይቶ፤ ሁኔታውን መርምሮና አመዛዝኖ አቋም መውሰድ ማለት ነው። በገፍ የሚሞተው የጎንደሬና ሌላ ዐማራ ሕይወት “እንደ እንስሳ” ህይወት መታየት የለበትም። ይህ የሚሆንበት ጊዜ አልፏል።

ግልጽ ለማድረግ፤ በጥናትና በመረጃ የተደገፈ አቋም መውሰድ አስፈላጊ ነው እላለሁ። የብዙ ሰዎች ህይወት እየወደመ፤ ቤታቸውና ንብረታቸው እየተቃጠለ ዝም ብሎ “በአንድነትና በመቻቻል፤ በጨዋነትና በአድር ባይነት” ሰበብ ሊሸነገል አይችልም።

ራሴን ለማመስገን ሳይሆን ስለ ኢትዮጵያዊነትና ስለ አንድነት ሌት ተቀን እሰራለሁ። ድጋፌን እሰጣለሁ። ይህን ማንም ሊያስተምረኝ አይችልም። ማንም እንዲነጥቀኝም አልፈቅድለትም። አንድነት ሲባል ግን የግል ወይንም የቤተሰብ ጉዳይ አይደለም። የፖሊሲ ጉዳይ ነው። የመንግሥት ስርዓትን ስር ነቀል በሆነ ደረጃ የመለወጥ ጉዳይ ነው። አንድነት ሲባል በመሬት ላይ የሚካሄደውን እልቂት ወደጎን ትቶ አይደለም። ይህ ሽሽት ይባላል። የፖለቲካ መሪዎችን አስሮ ድርድር እናድርግ ማለት ምን ትርጉም አለው! መሬት ነጥቆ ድርድር ይደረግ ማለት ምን ትርጉም አለው! ብዙ ሽህ ኦሮሞውና አማራ አስሮ ሰላምና እርቅ ያስፈልጋል ማለት ምን ትርጉም አለው! አንባቢ ያስብበት።

## የዐማራው ሕዝብ ትእግስት እንደ ድክመት ታይቷል

ሕዝቡ ትእግስተኛ በመሆኑ ነው እንጅ፤ ዛሬ በጎንደር---ወልቃይት ጠገዴ፤ አርማጭሆ፤ ሁመራ ወዘተርፈ--- በወሎ ራያና አዘቦ-- እና በጎጃም መተከልና ሌላ በገፍ የሚገደለው፤ የሚታሰረውና እንዲሰወር የሚደረገው በብዙ ሽህዎች የሚገመተው ወጣት የዐማራ ትውልድ ትግሉን የጀመረው ባለፉት ወራት አይደለም። ሕዝብ ትግሉን የጀመረው፤ ከፋኝና ሌሎች ስሞች ይዞ ሲንቀሳቀስ ቆይቷል። የሕዝብ እምቢተኛ ቡድኖች ብቅ ጥልቅ ሲሉ መቆየታቸው አይካድም፤ እድል እየጠበቁ።

አንባቢ እንዲያውቀው የምመኘው፤ ተቃዋሚው መሬቴን አላስነጥቅም ብሎ የተነሳው ህወሓት ተከዜን ተሻግሮ፤ መሬቶችን መቆጣጠር ሲጀምር ነው። አዲስ ካርታ ከመቅረጹ በፊት መሆኑ ነው። ይህ ሕዝባዊ እምቢተኛነት ህወሓት፤ ተከዜን አልፎ በጎንደርና በሌሎች ቦታዎች ለም መሬቶችን ወደ ትግራይ ለማጠቃለል ከጀመረበት “የውስጥ ወረራ” ጀምሮ ሲካሄድ ቆይቷል።

የጎንደር ሕዝብ በታሪኩ ታጥቆ ራሱን ከውጭ ወራሪ ሲከላከል የኖረ ሕዝብ ነው። አባቴ ሶስት መሳሪያዎች ነበሯቸው። ህወሓት ይህን ታጥቆ የመከላከል ባህል ለማጥፋት ሞክሯል። የሞከረበት ዋና ምክንያት መሬቱን ለማጠቃለል ስለወሰነ ነው።

በነገራችን ላይ፤ ነዋሪው የመሳሪያ ኃይል የሚጠቀመው የአካባቢውን ሕዝብ ከውጭ ጠላቶች ለመከላከል ብቻ አይደለም። ለምሳሌ ከሱዳን። “የውስጥ ወረራ” እንዲሁ ችላ የሚባል አለመሆኑን ያውቃል። የኦሮሞ ሕዝብ የተነሳው በውስጥ የመሬት ነጠቃ ዙሪያ ነው። “የገበሬውን መሬት አትንጠቁ” ብሎ!! በጎንደር፤ በጎጃምና በወሎ የሚደረገው “የዐማራ ተጋድሎ” ተብሎ የሚጠራው እንቅስቃሴ የጀመረው በማንነት ጥያቄና በመሬት ነጠቃና መስፋፋት ዙሪያ መሆኑን የሕዝቡ ትግል ብቻ ይመሰክራል። ይህ የነዋሪውን ሕዝብ መሬት፤ ድንበር፤ ጥቅምና ህይወት የለወጠ የመሬት ነጠቃ አሁን ለሚካሄደው ግጭትና እልቂት መሰረት ነው። እኔ አልፈጠርኩትም፤ የፈጠረው ህውሓትና ህወሓትን የመሰርቱት ግለሰቦችና ቡድኖች ናቸው።

ከታች በቀረበው ካርትና በሌሎች የአጼ ኃይለ ሥላሴና የደርግ መንግሥታት ካርታዎች በማነጻጸር እንዲሚታየው፤ የትግራይና የጎንደር ድንበር ተከዜ ነው። ልኡል ራስ መንገሻ ስዩም ሲጠየቁም የትግራይ ድንበር ተከዜ እንደሆነ መስክረዋል። የአጼ ቴዎድሮስ፤ የአጼ ዮሃንስ፤ የአጼ ምኒልክ፤ የአጼ ኃይለ ሥላሴ እና የደርግ መንግሥታት ይህን ድንበር አክብረው የክፍለ ሃገሩን አስተዳዳሪዎች ሰይመው እንደነበር ታሪክ ምስክር ነው።

ለምሳሌ፤ በአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ቢትወደድ አዳነ ያስተዳደሩት ክፍል ሃገር በማንኛውም ጊዜ የትግራይ አካል ሆኖ አያውቅም በሚል መረጃ ነበር። የትግራይ ክልል ወይንም ባለሥልጣን ወልቃይት ጠገዴን ወይንም ሌላውን የዐማራ ክፍለ ሃገር አስተዳድሮ አያውቅም። ቀደም ሲል እንዳሳየሁት፤ ብዙ ባለሞያዎች ያደረጓቸው ጥናቶች (አንዱን ከዚህ ትንተና ጋር አባሪ አድርጌዋለሁ) ራያና ቆቦም የትግራይ አካል አይደለም። የህወሓቶችና ደጋፊዎች የፈጠራ ታሪክና የሕዝብ ሰፈራ ይህን ሃቅ አይቀይረውም። ዛሬ በመሬት ላይ ያለው ሁኔታ ምን ይመስላል?

## መስዋእት የሆነው ጎንደሬው

አሁን የሚካሄደውን የጭካኔና የዘር ማጥፋት ምሳሌዎች ዘገባ እንየው። አንድ የጎንደር ተቆርቋሪ ጋዜጠኛ “እጅግ በጣም አሳሳቢ!” በሚል አርእስት እንዲህ ብሏል። “በወገራ ከ500 በላይ ቤተሰቦች ቤታቸውና ንብረታቸው በመንግሥት ወታደሮች ተቃጥሏል።” እኔ ባደረግሁት ጥናት፤ በዐማራ ገበሬዎች ላይ እየደረሰ ያለውን ሰቆቃ የዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ በቸልታ እያየው ነው! የትግሬ ወያኔ

አገዛዝ በዐማራው ሕዝብ ላይ እያደረሰው ያለው በደል ከቀን ወደ ቀን እየተባባሰ ሒዷል። "በዐማራ ሕዝብ ላይ ይፋ የእልቂት አዋጅ ታውጇል፡፡ ራሳቸውን ከጥቃት ለመከላከል እየተጋደሉ ያሉ ዐማሮች በሕይወታቸውና በንብረታቸው ላይ ይህ ነው የማይባል ጉዳት ደርሷል፡፡ በተለይ በሰሜን ጎንደር በአርማጭሆና በወገራ
ወረዳዎች የዐማራ ገበሬዎች ቤት እየተቃጠለ፣ ንብረታቸው እየተወረሰና እየወደመ ሕፃናት፣ ነፍሰ ጡር ሴቶችና አዛውንቶች በሜዳ ላይ ተበትነዋል፡፡ ሰሞኑን ከኅዳር 24 ቀን 2009 ዓ.ም. ጀምሮ በወገራ ወረዳ በእንቃሽና ጃኖራ ቀበሌዎች ይኖሩ የነበሩ ከ500 በላይ ቤተሰቦች ተበትነዋል፡፡ በንተራና በአውድማ ያለ ሰብል ከከባድ መሣሪያ በሚወጣ እሳት ዶጋ አመድ ሆኗል፡፡ በ2007/8 ዓ.ም. በነበረው ድርቅ ያላገገሙ ቤተሰቦች ዘንድሮ ያመረቱት ምርት በወያኔ መንግሥት ያለምንም ምሕረት ወድሟል፡፡ ይህ የለየለት አረመኔያዊ ተግባር ሲሆን የዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ሁሉ ሊያወግዘው የሚገባ ጉዳይ ቢሆንም በቸልታ እየታየ ነው።" ይህ ሁኔታ እንዳይታወቅ የሆነበት ዋና ምክንያት የመገናኛ ብዙሃን ስለሌም ጭምር ነው።
ለናሙና ያህል
"ዛሬ ከተጎዱ ቤተሰቦች ጋር ባደረግነው ውይይት በእንቃሽ ቀበሌ ከ50 በላይ ቤቶች ወድመው ወደ 200 የሚሆኑ ቤተሰቦች ተበትነዋል፤ በጃኖራ ቀበሌም ተመሳሳይ ውድመት ደርሷል፡፡ ትናንት እና ዛሬ ተበትነው የሚገኙ ቤተሰቦች ወደ 500 እንደሚደርስ ተጎጅዎች ተናግረዋል፡፡ የሚከተሉት አባውራ ቤቶችና ቤተሰቦች ስም ዝርዝራቸውን ያገኘናቸው ብቻ ነው።"
ስም የቤተሰብ ብዛት ቀበሌ
1) ምስጋነው አጠኔ 12 እንቃሽ
2) መለሠ ተሾመ 7 እንቃሽ
3) ተሾመ ደሴ 5 እንቃሽ
4) ታደለ መልሰው 4 እንቃሽ
5) ደመወዝ ነጋሽ 10 እንቃሽ
6) ለከው ይለፉ 10 እንቃሽ
7) ካሣው ታየ 5 እንቃሽ
8) ዘሪሁን ተዘራ 4 እንቃሽ
9) ንጉሥ ዘሬ 3 እንቃሽ
10) ታከለ ማረው 4 እንቃሽ
11) ቀኑ ገሠሠ 2 እንቃሽ
12) ያለው አበበ 9 እንቃሽ
13) ደጉ በዜ 5 እንቃሽ
14) መሳፍንት ተስፋ 5 ጃኖራ

የችግሩ አሳሳቢነት ከዚህ ላይ የተገለጸውን ያክል ብቻ አይደለም፡፡ በኅዳና የተበተኑ ሕጻናትንና አቅመ ደካማ ሰዎችን ልቅሶ መስማትም የበለጠ ያሳምማል፡፡ ማንኛውም በዐማራ ሕዝብ ላይ የሚደርሰውን እልቂት የሚያሳስበው ሰብአዊ ፍጡር ሁሉ ይህን አረመኒያዊ ድርጊት እያወገዘ በሚቻለው ሁሉ እንዲያግዝም ጥሪ ቀርቧል፡፡"
ሌላው የማይካደው የታሪክ ሃቅ የትግራይ ተወላጆች በሰቲት ሁመራና በሌሎች ለም ቦታዎች፤ በነዋሪው ሕዝብ ፍላጎትና ፈቃድ፤ በሕዝቡ የወንድማማችነት፤ እህትማማችነትና ጉርብትና ባህል ከትግራይ እየመጣ ስራ የሚያገኝበት፤ ኃብታም የሚሆንበት ሁኔታ እንደነበር ነው። በአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ሰቲት ሁመራ፤ መተማና ሌልች ቦታዎች ዘመናዊ እርሻ ሲስፋፋ፤ የሰራተኛ እጥረት ስለነበረ፤ ከግማሽ ሚልየን በላይ የሚገመት የኤርትራና የትግራይ ተወላጆች የስራ እድል ነበራቸው።
በአስተናጋጅነቱና በጨዋነቱ ወደር የሌለው የጎንደር ሕዝብ የትግራይን ሕዝብ እንደራሱ አድርጎ አስተናግዷል። ይሉኝታ የሚባል ነገር የማያውቀው ህወሓት ውለታውን አልከፍልህም ብሎ የባሰውን በጠላትነት ፈርጆታል። መሬቱን ሲቀማው እያጠፋው ነው። ይህ ጠላትነት አያዋጣም።
ህወሓጥ ስልጣን ከመያዙ በፊት፤ በተለይ ስልጣን ከያዘ በኋላ ብዙ መቶ ሽህ የትግራይ ተወላጆችን በነጠቃቸው መሬቶች ላይ አስፍሯል። የሕዝቡን ስርጭት ቀይሮታል። ይህን ከውስጥ ወረራ ምን ይለየዋል?
ለዚህ ነው፤ አንድ አገር! አንድ ሕዝብ! የሚል መርህ ብንቀበል ኖሮ፤ ዱሮ እንደነበረው፤ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በየትኛውም የኢትዮጵያ ክፍል ለመኖር፤ የግል ኃብት ለማያዝ፤ ለመምረጥና ለመመረጥ መቻል አለበት የምለው። እንደ ህወሓት በጠባብ ብሄርተኝነትና በጎጠኝነት የተበከለ የፖለቲካ ፓርቲ ዘዴውን ይቀያይራል እንጅ "በአንድ አገር፤ በአንድ ሕዝብ" ፍልስፍናና በተባባሪነት አያምንም። ህወሓት ህብረ ብሄር ድርጅቶችን በጠላትነት የፈረጀው ለዚህ ነው።
መሰረታዊ የፖሊሲና የስርዓት ለውጥ አሁን ከተደነገገው የክልል ስርአት ጋር እንደሚጋጭ አውቃለሁ። ራስን የማስተዳደር መብት ችግር አይደለም፤ ችግሩ የእያንዳንዱን ኢትዮጵያዊ መብት ተጠብቆ እንዴት ስኬታማ ይሁን የሚለው ነው። ለማንኛውም፤ ማጤን ያለብን ግን አሁን ያለውን ለከፋፍለህ ግዛው አመች የሆነውን፤ በብሄርና በቋንቋ ተቃርኖዎች የተመሰረተውን ስርአትና አገዛዝ፤ አንድ አገር! አንድ ሕዝብ! በሚል፤ በዜግነት መብት ላይ በተመሰረት ስርዓት መተካት አስፈላጊ ነው የምልበት። ስርዓቱን ሕዝብን በሚወክል አገዛዝ ካልተካነው አሁን የሚካሄደው የመሬት ነጠቃና መስፋፋት አያቆምም። ምዝበራው አያቆምም፤ ግጭት የተለመደ ይሆናል። (we will continue to normalize abnoramilites and distortions to the point of endangering the country and the welfare of its 102 million people).
ከላይ እንዳሳየሁት ወደፊትም፤ የመሬት ነጠቃንና የትግራይን መስፋፋት ኃይል ተጠቅሞ ዘላቂ ማድረግ ሰላምንና እርጋታን አይፈጥርም። ይህን የህወሓትን ተራ ውንብድና ዘላቂ ለማድረግ የሚደረግ ሴራ፤ ማንም ነዋሪም ሆነ ሌላ ኢትዮጵያዊ መቀበል

የለበትም። ህወሓትን ማስገደድ ያለብን፤ በአጼ ኃይለ ሥላሴና በደርግ ዘመናት የነበረው የተለመደ የወንድማማችነት፤ የእህትማማችነት፤ የስራና የኃብት የማካበት ፖሊሲ፤ የመሬት ባለቤትነት፤ ባህልና ልምድ በህግ እንዲከበር ማድረግ ነው። አግባብ ያለው የመሬት ይዞታ ፖሊሲ ያስፈልጋል። ይህን ስል ለማስገንዘብ የምፈልገው ጉዳይ አለ።

ይኼውም፤ ህወሓት በመተደጋጋሚ ያሳየው ባህርይ እንደማይለወጥ መጠራጠር የለብን የሚል ነው።

ለምሳሌ፤ ሕገ ወጥ በሆነ ዘዴና መርህ ያካበተውን አስርት ቢሊየኖች ዶላር ኃብት ለኢትዮጵያ ሕዝብ አይመልስም። የመሳሪያ ኃይል ተጠቅሞ የነጠቀውን ለም መሬት አይመልስም። ይህን ካደረገ ለትግራይ ሕዝብ የገባውን ቃል ኪዳን ሳበ ማለት ነው። ከሳበ ህወሓት ጠፋ ወይንም ሞተ ማለት ነው።

ቀላል ምሳሌ ላቅርብ። የአውሮፓ ፓርላማና ሌሎች መንግሥታት ሰብአዊ መብቶችን በሚመለከት ህወሓት/ኢህአዴግን አወገዙት፤ ይህ ውግዛ ህወሓትን አንዲት ሴንቲሜትር ያህል ለውጥ እንዲያሳይ አላስገደደውም። አፈናውና ድርጅታዊ ምዝበራው በባሰ ደረጃ ቀጥሏል። ስለዚህ ያለው አማራጭ ሕዝባዊ አመጽ ይሆናል! ይህን ስኬታማ ለማድረግ አዲስ የትብብር ባህል ያስፈልጋል።

በማንኛውም መስፈርት ስገመግመው፤ የህወሓቶች ጠባብ ዘረኛነት፤ ብሄርተኛነት፤ ጎጠኛነትና የትግራይ መስፋፋት መለያው የጸረ ዐማራ፤ የጸረ-ሕዝብ፤ የጸረ-ኢትዮጵያ፤ የጸረ-ሰላም፤ የጸረ ጉርብትና፤ የጸረ-ዲሞክራሲ አገዛዝ ሂደት መሆኑን ነው። ወልቃይቴውንና ሌላውን የዐማራ ሕዝብ አባርሮና እንዲሰደድ አድርጎ ትግሪዎችን ማስፈር “የአገር ውስጥ ወረራ” ነው። ይህ ግፍ ለሰላምና አብሮ ለመኖር ጸር ነው።

የሚያዋጣው ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲሸጋገር የቆየውን የመሬት ባለቤቱን መብቶች አክብሮ ሌላውም ኢትዮጵያዊ፤ ትግራዩንም ጨምሮ፤ ባለበት ቦታ መብቱ እንዲጠበቅ፤ የሌላውን መብት እንዲያከብር ማድረግ ነው። ይህ ደግሞ ህወሓት የማያስበውን፤ የማያምንበትን መፈቃቀርን ይጠይቃል። አርቆ ማሰብን ይጠይቃል።

የዐማራው፤ የቅማንቱ፤ የወልቃይት ጠገዴው፤ የአገው፤ የወይጦው፤ የቤተ ኢስራኤሉና የሌላው ሕዝብ “በቃ” ብሎ የተነሳው ለዚህ ነው። ችግሩ የህልውና ሆኗል የምለው ለዚህ ነው። ማንም ዜጋ በራሱ አገር፤ በራሱ መሬት፤ በራሱ ወንዝ፤ በራሱ ተራራና ሌላ የተፈጥሮ ኃብት ለማዘዝ ካልቻለ የሚከተለው የማይፈታ “የእርስ በርስ ጦርነት” መሆኑ እየተነገረ ነው። “ምሁር” ነን የምንለው ግለሰቦች ሚና ሃቁን ተናግረን መፍትሄ እንዲገኝ መጣጣር ነው። የሌለውን ታሪክ አለ ብሎ መናገር ሁኔታውን ያባብሰዋል እንጅ መፍትሄ አይሆንም። ያለፈውንና አሁንም የተባባሰውን የህወሓቶችን ግፍ፣ አግላይነት፤ በደል፤ እልቂትና አፈና መካድ ሁኔታውን ያባብሰዋል እንጅ መፍትሄ አይሆንም። የችግሩን መሰረት ካወቅነውና ከተቀበልን መፍትሄው አይጠፋም። ከካድነው መፍትሄ አይታሰብም። ማንኛውንም ችግር ለመፍታት የሚቻለው መጀመሪያ የችግሩ መነሻና ምክንያት ጭብጥ ሲሆን ነው። የችግሩ መነሻና መድረሻ ህወሓት ነው። የመሬት ነጠቃና ተስፋፊነት ነው።

የወልቃይት ጠገዴን የማንነት፤ የባለቤትነት፤ የነጻነት፤ የስብአዊ መብትና የዲሞክራሲ ጥያቄ አግባብ ባለው መልክ በመረጃ ተደግፌ አቅርቤዋለሁ። እንድንወያይበት፤ እንድንማርበት አሳስባለሁ!!!

ድምዳሚዎችና የመፍትሄ አቅጣጫዎች

ለችግሩ መፍትሄ አለ ወይንስ የለም?

ቅንነትና የፖለቲካ ፈቃደኛነት ካለ መፍትሄም አለ። የአካባቢው አባቶች፤ እናቶች፤ ወጣቶች፤ የጎበዝ አለቃዎች፤ የአካባቢ ስብስቦችና ሌሎች የሚሏቸውን ሃሳቦች ማንጸባረቅ ግዴታችን ነው።

አንድ፤ በአገር አቀፍ ደረጃ ስመረምረው፤ ህወሓትና ደጋቺዎቹ የኢትዮጵያን የፖለቲካ ስልጣን፤ ዘመናዊ ኢኮኖሚና የተፈጥሮ ኃብት ማርከውታል። ስለሆነም፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ መሰረታዊ የሆነ የስርዓት ለውጥ ያስፈልገዋል። ይህ ተግዳሮት የሚጠይቀው ሕዝባዊ አመጽ ይሆናል። ይህም መተባበርን ይጠይቃል።

ሁለት፤ የህወሓት የመሬት ነጠቃና የትግራይ ተስፋፊነት በእቅድ የተሰራ፤ ዘላቂነት እንዲሆን በጦር መሳሪያ ኃይል የተደገፈ ነው። ህወሓት ለትግራይ ሕዝብ ቃል ኪዳን የገባበት ስለሆነ በድርድር የሚፈታ አይመስለኝም።

ሶስት፤ ጎንደሬው፤ ወሎየው፤ ጎጃሜውና ሌላው የአማራና የሌላ ብሄር ነዋሪ የገጠመው ችግር የመኖር-አለመኖር፤ ማለትም፤ የህልውና ጥያቄ ሆኗል። ችግሩን ሊወጣው የሚችለው በመተባበር፤ አቅምን በማጠናከርና ሌሎች ኢትዮጵያዊያን እንዲተባበሩት ያልተቆጠበ ጥረት በማድረግ ነው።

አራት፤ የመጀመሪያው ትኩረት ግን በያካባቢው አቅምን ማጠናከር፤ መደራጀት፤ ጠንካራና የማይበገር ሕዝባዊ አመራር መፍጠር ነው፤ ይህ እየተፈጠረ መሆኑን አውቃለሁ፤

አምስት፤ የወልቃይት-ጠገዴና ተመሳሳይ ጥያቄዎች ብሄራዊ ችግሮች ናቸው። የወልቃይት ጉዳይ የአንድ አካባቢ ጉዳይ ብቻ አይደለም። ልክ የድንበሩ ጉዳይ የአካባቢ እንዳለምሆኑ መጠን፤ የወልቃት-ጠገዴ ጉዳይም የአካባቢ፤ የጎንደሬ ጉዳይ ብቻ ነው የሚሉ ግለሰቦችና ስብስቦች ተሳስተዋል ከሚል ድምዳሜ ላይ ደርሻለሁ። ስለዚህ፤ ሌሎች ኢትዮጵያዊያን ጉዳዩን እንደራሳቸው ጉዳይ እንዲቆጥሩትና እንዲታገሉበት አደራ እላለሁ። በያካባቢው ብቅ ብቅ ያሉት እንቅስቃሴዎች የሁላችንም ትኩረትና ድጋፍ ያስፈልጋቸዋል።

ስድስት፤ የወልቃይት የማንነት፤ የባለቤትነት፤ የሰብአዊና ዲሞክራሳዊ መብቶች ጥያቄ የህልውና ጥያቄ ነው። ከላይ እንዳሳሰብኩት፤ ይህ ጥያቄ ሁሉንም ኢትዮጵያዊያን ያገባቸዋል። በተለይ፤ ተቃዋሚ ነን የሚሉ ምሁራን፤ ልሂቃን፤ ተቃዋሚ ፓርቲዎችና ሌሎች አቋም መውሰድ አለባቸው።

ሰባት፤ ህወሓትና ደጋፊዎቹ ሰላምና እርጋታ ከፈለጉ የትግራይ ድንበር ተከዜ መሆኑን መቀበል አለባቸው። ሆኖም፤ ህወሓቶች ይህን አማራጭ ይቀበላሉ የሚል ግምትና እምነት የለኝም። ሕዝብ ይህ አማራጭ ይሰራል ብሎ እንዳይሞኝ አሳስባለሁ።

ስምንት፤ ይህ ሰባተኛ አማራጭ የኢህአዴግን እውቅና እስካላገኘ ድረስ ሕዝባዊ አመጹ ይቀጥላል የሚሉ ታዛቢዎች ብዙ ናቸው። ለዚህ የሚሰጡት መረጃ ወጣቱ ትውልድ ከአሁን በኋላ በቃኝ፤ ድንበሬንና ጥቅሜን መስዋእት እየከፈልኩ አስከብራለሁ ብሎ መነሳቱ ነው። ይህን አመለካከት ሙሉ በሙሉ እጋራለሁ።

ዘጠኝ፤ ከላይ እንደመረጃ በቀረበው መሰረት፤ ምሁራንና ሌሎች የሚሉት ወያኔዎች ይህን ተከዜን አልፈው የመሬት ማጠቃለል ሲያደርጉ አዲስ ታሪክ፤ አዲስ መረጃና አዲስ ካርታ በማውጣት፤ የዐማራውን ሕዝብ ከቀዩ በማባረርና የትግራይን ሕዝብ በቁልፍ ቦታዎች በማስፈር ነው። የዐማራው ሕዝብ ተከዜን ተሻግሮ የትግራይን መሬት አልነጠቀም የሚለውንም ይቀበላሉ።

አንድ ታዋቂ ግለሰብ ባደረገው ጥናት እንዲህ የሚል ዘገባ አቅርቧል። "ምርምሮችና ጥናቶች የሚያሳዩት ሃቅ አንድ ነው። ወያኔ በረሀ ከነበረበት ዘመን ጀምሮ የአማራን ዘር ባሕልና ማንነት ከአካባቢው በማጥፋት በማፈናቀልና በማሳደድ፣ የትግራይ ተወላጆችን በገፍ በማስፈር፤ ብዙ የዐማራ፤ የቅማንትና ሌሎች ዜጎችን በማሳደድ፤ በድብቅ በመግደል፤ እንዲሰደዱ በማድረግ እየተስፋፋ ከሄደና ሥልጣን ከያዘ በኋላም የትግራይ ተወላጆችን በማስፈር የአካባቢውን ዲሞግራፊ (ነባራዊ ምኅዳር) ሙሉ ለሙሉ ሊባል በሚያስችል ደረጃ ቀይሮታል። የአካባቢው የዐማራና ሌሎች ነዋሪዎች ከቤታቸው፤ ከንብረታቸው፤ ከመሬታቸው በገፍና በግፍ ተፈናቅለዋል.... የመሬት ነጠቃና የነዋሪዎችን ባህል፤ ልምድ፤ ታሪክ፤ ምሳሌዎች፤ ስሞች ወዘተርፈ እንዳልነበሩ ማድረግና በሚፈለገው ዘዴ መተካት የተለመደ የዘር ማጥፋት ሂደት ነው።"

ይህ ትክክክል መሆኑን በመረጃዎች አረጋግጫለሁ። አንዱና ዋናው የህወሓቶች እቅድ የአማራውን ሕዝብ ማዋረድ፤ ዘሩንና ባህሉን ማጥፋት፤ መሬቱን መንጠቅ፤ ከቀዩ በገፍ ማባረር ሆኗል። ከዚህ የደመደምኩት ጎንደሬው፤ ወሎየው፤ ጎጃሜውና ሌላው የአማራና ሌላ ብሄር የዘር ማጥፋት ዘመቻ እንደተካሄደበትና ወደፊትም እንደሚካሄድበት ብዙ መረጃዎችን አይቻለሁ፤ አመሰካሬአለሁ። ችግሩ፤ የመኖር! አለመኖር! የህልውና ጥያቄ ነው የሚለው አግባብ አለው።

አስር፤ የመረምርኳቸው ጥናቶችና መጽሃፍት ያረጋገጡት የትግራይ ድንበር ተከዜ መሆኑን ነው። ጥናቶች የሚያሳዩት፤ ህወሓት አዲስ ታሪክ መፍጠሩን ነው። ይህን ያደረገበት ዋና ምክንያት የነጠቀውን መሬት ህጋዊ ለማድረግ ነው።

ይህን የሃሰት ፋብሪካ በሚመለከት፤ በNovember 2016, የኢሳቱ ጋዜጠኛ ሲሳይ አጌና በሜልበርን አውስትራሊያ ከአቶ ፈረደ መብራቱና ከአቶ ደሳለኝ ታየ ጋር ባደረገው ሰፊ ቃለ መጠይቅ "የወልቃይት ጠገዴና የሌሎች በዐማራው ክልል የሚገኙ፤ አሁን የተነጠቁ አካባባቢዎችን የአስተዳደር፤ የነዋሪሮዎች ብሄር፤ የመሬት ባላቤትነት፤ የጎበዝ አለቃዎች፤ የድንበር ይዞታና የግብር ክፍያ" ወዘተርፈ ታሪክ በማያሻማ መረጃ አቅርበውታል።

ለማጠናከር፤ መረጃው የሚያሳየው "የትግራይ ክልል ተከዜ" መሆኑን ነው። ህወሓቶች "ነጩን ጥቁር ነው፤ በሬ ወለደ፤ የዳሽን ተራራ የትግራይ ነው ወዘተርፈ" ካሉ በኋላ ሃቁን የማይቀበሉት ህወሓትና ደጋፊዎቹ አዲስ ታሪክ ፈጥረው፤ "የትግራይን ሕዝብ እንዲሰለፍ አድርገው፤ አዲስ ካሪኩለም ጸንሰው፤ መሬቱ ከጥንት ጀምሮ "የእኛ ነው" ይላሉ።

ይህን የፈጠራ ታሪክ (Make Believe) እኔም ሆነ ሌሎች የአካባቢው ተወላጆች አንቀበልም። የምከራከርበት መሰረታዊ ወይንም የፖሊሲ ልዩነት ይኼው ነው። ሕዝብ ለማንነቱና ለመሬቱ፤ ለህይወቱ፤ ለህልውናው፤ ለመብቱ፤ ለነጻነቱ በገፍ እየሞተና እየተሰደደ የሚሞትበትን ምክንያት በሰከነ አእምሮ መመርመር፤ ቢቻል መቀበል አስፈላጊ እየሆነ ሄዷል። የምደመድመው የዚህን አስደንቂ ሕዝብ ጩኸት እንስማው፤ ድጋፍ እንለግስ በሚል ነው።

በማስረጃ እንዳሳየሁት፤ በግፍ የተፈናቀሉት የተሰደዱትና እንዲጠፉ የተደረጉት፤ በአብዛኛው፤ የዐማራው ሕዝብ ወገኖች በጅምላ ያጡትንና ለሰፋሪ ተላልፎ የተሰጠባቸውን ቤት ንብረትና መሬት መልሰው እንዲያገኙ ሳይደረግ ጎንደሬውና ሌላው ዐማራ፤ ቅማንቱና ሌላው መስዋእት እየሆነ ባለበት ሁኔታ "ይህ ጉዳይ በሕዝበ ውሳኔ እልባት ያግኝ!" ብሎ ማለት ኢፍትሐዊ፤ ግፈኛና ጭካኔነትን የሚያሳይ ብያኔ ነው፡፡

አግባብ የሚኖረው መፍትሄ ነባር ተወላጆቹን ብቻ የሚያሳትፍና ድምጻቸውን የሚሰጡበትን ሁኔታ ለመፍጠር የሚያስችል ፖሊሲና ውሳኔ ነው። ድምጽ የነዋሪው ሕዝብ እንጂ የሰፋሪዎች ሊሆን አይችልም። ኤርትራ እንድትገነጠልና የኢትዮጵያ የባህር በር እንዲዘጋ ያመቻቸው ህወሓት አሁንም መሬት ነጥቆ ኢትዮጵያን እያፈራረሳት ነው። ችግሩ በሬፈረንደም ይፈታ የሚለው ከኤርትራው ሁኔታ አይለይም።

ህወሓቶች እረሱት እንጅ፤ ኤርትራን ሲያስገነጥሉ ድምጽ እንዲሰጥ ያመቻቹት ኤርትራዊውንን ብቻ ነው።

በቅርቡ፤ የማስተር ፕላኑን ተስፋፊነት ያስለወጠው የኦሮሞው ሕዝብ ድምጽና፤ ግፊትና አመጽ ነው። ህወሓት ፈቅዶ ያደረገው አይደለም። ህወሓት ፈቅዶና ወዶ የነጠቀውን መሬት፤ ከሕግ ውጭ ያካበተውን ኃብት ለሕዝብ አይመልስም።

አስራ አንድ፤ በዐማራው ክልል የመሬት ነጠቃ ጉዳይ የሚያገባው የዐማራውንና ሌላውን ነዋሪ ሕዝብ ነው። የሕግ የበላይነት የለም እንጅ ቢኖር፤ መሳተፍና ድምጽ መስጠት የሚችለው ነዋሪው ሕዝብ ብቻ ነው። ሁለት አይነት ፍትህ ሊኖር አይችልም። አንዱ ለኤርትራዊያን/ኦሮሞ፤ ሌላው ለጎንደሬው፤ ለወሎየው፤ ለጎጃሜው፤ ለአፋሩ!!!!

አስራ ሁለት፤ በስድስት መሰፈርቶች እንዳሳየሁት፤ የህወሓት የመሬት ነጠቃና የትግራይ ተስፋፊነት ሕገ-ወጥ ነው። በመረጃ የተደገፈ አይደለም። የትግራይ ድንበር ተከዜ ነው። የተነጠቀው መሬት ለነዋሪው ሕዝብ ካልተመለሰ፤ ሰላምና እርጋታ፤ ብሄራዊ አንድነት አይኖርም። በትግራይ ሕዝብና መሬታቸውን በተነጠቁት ነዋሪዎች መካከል ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍ ጥላቻና ግጭት ይቀጥላል። ስለሆነም፤ ሁሉንም ኢትዮጵያዊያን ይመለከታል።

አስራ ሶስት፤ ህወሓት ያካሄደው የ1994 የሕዝብ ቆጠራና ዘገባ በህወሓት ተመርጦ እንደ መረጃ የሚቀርበው በህወሓት በተነተቁት ለም መሬቶች፤ ማለትም i) በሰቲት ሁመራii) በጠለትምት iii) በወልቃይት iv) በጠገዴ የሚኖረው "አብዛኛው ሕዝብ ትግሬ" መሆኑን ዘግቧል። የአማራውና የሌላው ሕዝብ ቁጥር በማይታመን ደረጃ እንዲቀንስና በራሱ መሬት አናሳ እንዲሆን፤ በአንዳንድ አካባቢዎች ፈጽሞ እንደማይኖር ተደርጎ እንደተበየነበት ያሳያል። ይህ የፖለቲካ ስልጣን ተጠቅሞ በኃይልና በጫና የተደረገ ውሳኔ ነው። ይህ በፖለቲካ የተወሰነ የሕዝብ ቆጠራ የተካሄደው ህወሓት ስልጣን ከመያዙ በፊት አካባቢውን ስለተቆጣጠረው ሰፊ የትግራይ ሕዝብ፤ የቀድሞ ታጋዮችን ጨምሮ አስፍሮበታል። የአካባቢውን ነዋሪዎች በሚዘገንን ደረጃ ገድሏል፤ እንዲሰወሩ አድርጓል፤ እንዲሰደዱ አስገድዷል።

እነዚህን ጥንታዊ ነዋሪዎች በገፍ አስወግዶ፤ የገደለውን ገድሎ፤ በምትካቸው ስልጣን ከመያዙ በፊትና ስልጣን ከያዘ በኋላ በዝቅተኛ

500,000 ትግሬዎች አስፍሮበታል። ካሰፈረ በኋላ መሬቱ “የትግሬዎች ነው፤ አካባቢው የትግራይ ክልል አካል ነው” ማለቱ አያስደንቅም።
ዋናው ነጥብ ግን ለብዙ ሺህ አመታት በአካባቢው የኖረውና ህወሓት በትጥቅም መሬቱን ከመንጠቁ በፊት እነዚህ መሬቶች የትግራይ ክልል ሆነው አያውቁም የሚለው በብዙ መረጃ የተደገፈው ነው። አብዛኛው ነዋሪም የትግራይ ብሄር አባል አልነበረም።
አስራ አራት፤ ስለዚህ የወልቃይትና የሌሎች የተነጠቁ መሬቶች ጉዳይ በአሁኑ የሕዝብ ስርጭት ቆጠራ ይወሰን ከተባለ፤ ህወሓት ያካሄደው በፖለቲካ ውሳኔና በመሳሪያ ኃይል ጫና አግባብ አለው የተባለው የ1994 የሕዝብ ቆጠራና የብሄር ስርጭት ተቀባይነት የለውም። በኃይል የተያዘ ይዞታ ነው (Occupation and Annexation of Lands By Force). አግባብ የሚኖረው በደርግ መንግሥት የነበረው የሕዝብ ስርጭትና እውቅና ያለው ድንበር ነው።
አስራ አምስት፤ በመጨረሻ ለማሳሰብ የምፈልገው፤ የወልቃይት ጠገዴና ሌሎች የጎንደር፤ የወሎ፤ የጎጃም፤ የአፋርና ሌሎች የተነጠቁ መሬቶችና የነዋሪዎች ችግር የአስተዳደር አይደለም። የህወሓት የመሬት ነጣቂነትና ተስፋፊነት ችግር ነው። የጠባብ ብሄርተኛው፤ ጎጠኛውና ዘረኛው የህወሓት የስርዓት የበላይነትና አዛዢነት ችግር ነው። የአምባገነንነት ችግር ነው። ወልቃይት ጠገዴ “የትግራይ” ነው የሚለውን አዲስ ብሂልና ታሪክ የጎንደር ሕዝብ መስዋእት እየሆነ፤ “ይህን አዲስ የፈጠራ ታሪክ አንቀበልም” ብሎታል።
ያቀረብኩት ሰፊ ትንተና የነዋሪዎቹንና ከቀያቸው የተባረሩትን ጎንደሬዎች ብሶትና የሰብአዊ የመብት አግባብነት ጥያቄ ይደግፈዋል። ዛሬ የወልቃይት የማንነትና የመሬት ባለቤትነት ጥያቄ የመላው ዐማራ ብቻ ሳይሆን፤ የመላው ኢትዮጵያዊያን የሰብአዊ መብት መታፈን ጥያቄ ሆኗል። ጎንደሬው “የኦሮሞ ወንድሞቻችን ደም ደማችን ነው” እንዳለው ሁሉ፤ የወልቃይት የማንነትና የመሬት ባለቤትነት ጥያቄና እንቅስቃሴ የመላው ኢትዮጵያዊያን የነጻነት፤ የፍትህ-ርትእ፤ የሕግ የበላይነት፤ የዲሞክራሲ ጥያቄ ሆኗል።

Copyright@Semegnyahoo.com 2017 የደራሲው ሙሉ መብት የተጠበቀ ነው።

ማስታወሻ፤ ይህ ትንተና ረዘም የሆነበት ዋና ምክንያት ጉዳዩ ከባድ፤ አወዛጋቢና ብዙ መረጃዎች ስላስፈለገው ነው። መረጃዎችን የሚፈልግ አንባቢ በ Ssemegn@yahoo.com ለመጠየቅ ይችላል።

በተጨማሪ፤ ደራሲው ይህ ትንተና መሰረት አድርጎ በመጽሃፍ መልክ ለማሳተም እቅድ ስላለው መጽሃፉ ሲገባደድ በድህረ ገጾች ግልጽ ይሆናል።
This paper cannot be copied or cited in publications without the written permission of the author

## የመሬት ነጠቃና የትግራይ ተስፋፊነት ስእሎች ይህን ይመስላሉ





ሀ- ዓላማውና ሥራው።
የትግራይ ህዝብ ብሔራዊ ትግል ፀረ-የአማራ ብሔራዊ ጭቆና፣ ፀረ-ኢምፔርያሊዝም እንዲሁም ፀረ-ንኡስ ከበርቴያዊ. ጠንቋ ሰውኛ ነው። ስለዚህ የአብዮታዊው ትግል ዓላማ ከበጎባታዊ ሥርዓትና ከኢምፔርያሊዝም ነፃ የሆነ የትግራይ ዲሞክራሲያዊ ሪፓብሊክ ማቋቋም ይሆናል።

